## የኛ ስልጣኔ ካልሰማኸኝ እንካ ጥይት

ሁሴን ከድር

## መፈንቅለ መንግስት ወይስ!?

ተስፉ (ኢትዮጵያ) አልታሰብ




መለያችን ኢትዮጵያዊነታችን!

# ግዮን

በየሳምንቱ ቅዳሜ

ግዮን ቅጽ 2 ቁጥር 62 ሰኔ 2011 ዓ.ም

ዋጋ 14.99


## “ሞት ባያስደስትም አስገዳዩ ፅዋውን እንኳን ቀመሰው”

ወ/ሮ የሹሜ ደምሳሽ የዶ/ር አምባቸው ባለቤት

## “አላመንኩም! አባቴ ይመጣል የሚል ተስፋ ነው ያለኝ”

ነፃነት አምባቸው የዶ/ር አምባቸው ልጅ








# የጀነራሉ አመጽ እና ግብታዊው እርምጃ

# ባህር ዳር ያቺን ሰዓት !









ልዩ ዕትም

የጀነራሉ አመጽ እና ግብታዊው እርምጃ
መላክ ቢ.

2

ባህር ዳር ያቺን ሰዓት!
ከአንድ ማህበረሰብ ወጥተው፣
በሁለት መንገድ የተጠፋፉ
ሹማምንት
በሮቤል ምትኩ

5

የአዲሱ የለውጥ አስተዳደር
ቀይ መብራት

10

ዶ/ር አምባቸው መኮንን
ከ1963-2011

11

አቶ እዘዝ ዋሴ
ከ1957-2011

12

አቶ ምግባሩ ከበደ
ከ1966-2011

13

ሜ/ጄነራል ገዛኢ አበራ
ከ1953-2011

14

ጀነራል ሰዓረ መኮንን
ከ1954-2011

15

"ጥፋቱ እንዳይደገም የሕገ ወጥ
ቢሯችንን ሁሉ እንዘጋለን"
ጠ/ሚ/ር ዐቢይ አሕመድ

16

"ለለውጡ ሲሉ ቤተሰባቸውን፣የግል
ሕይወታቸውን የረሱ ጀግኖችን
አጥተናል"
ም/ጠ/ሚ/ር ደመቀ መኮንን

17

"ሠራዊታችንን በብሄርና በጎሳ
ለመከፋፈል የተወሰደ ዕርምጃ
ነው"
አቶ ለማ መገርሳ

17

"ቤተሰቤ ይበተናል እንጂ
ኢትዮጵያዊነቴን አሳልፌ
አልሰጥም በማለቱ ከሀዲ ተብሏል"
ጄነራል አበባው ታደሰ

18

"ሰዓረ ለአገር በለፋ፣ ምን በድሎ
ነው የሚገደለው?"
ጀነራል ብርሃኑ ጁላ

19

የኛ ስልጣኔ
ካልሰማኸኝ እንካ ጥይት
ሁሴን ከድር

20

ቀጣይ ዕትም

ቅዳሜ

ሰኔ 29

ይጠብቁን!




ቁጥር 61 ዕትም



"ሞት ባያስደስትም አስገዳዩ
ፅዋውን እንኳን ቀመሰው!!"
ወ/ሮ የሹሜ ደምሳሽ የዶክተር
አምባቸው ባለቤት

7

"አላመንኩም! አባቴ ይመጣል
የሚል ተስፋ ነው ያለኝ!"
ነፃነት አምባቸው፣
የዶ/ር አምባቸው የመጀመሪያ ልጅ

8

"ሰው ለአገሩ እየሰራ የሚገደል
ከሆነ እንዴት እንደሚቀበለው
አላውቅም!"
ወ/ሮ ምክር ጌትነት የዶ/ር
አምባቸው መኮንን የወንድም ልጅ

9

ሽንቁሮች
ፍቅርተ ተሾመ

21

መፈንቅለ መንግስት ወይስ!?
ተስፉ (ኢትዮጵያ) አልታሰብ

23

የተሰዉት የአዴፓ ጀግኖችና
የማህበራዊ ሚድያው መዘጋት
ጃፈር ስዩም

25

ያታን መሰረት ያደረገን
ጥቃት ለመከላከል ሁላችንም
የየድርሻችንን ኃላፊነት
መወጣት አለብን
ከእሸቱ ደስታ

27



# የጀነራሉ አመጽ እና ግብታዊው እርምጃ

**መላክ ቢ.**

## የዐቢይ አህመድ “ለሞት ሩብ ጉዳይ”

ያኔ ገና የለውጡ ትኩሳት እና ስሜት ግለት ላይ በነበረበት ወቅት ፣ በመላው ኢትዮጵያ ህዝብ ከአራት አስርተ ዓመታት በኂላ ለመጀመሪያ ጊዜ እንደልቡ ማውራት እና በየጓዳው በሃገር ፍቅር ስሜት መናጥ በጀመረበት አፍላ የለውጥ ወቅት፣ “ኢትዮጵያ” የሚለው ቃል ለመጀመሪያ ጊዜ የተፈጠረ እስኪመስል ድረስ በሁሉም አፍ “ኢትዮጵያ፣ ኢትዮጵያ” ይባል በነበረበት ወቅት፣ ይህ የስሜት ግለት ሳይበርድ ለውጡን እና ጠ/ሚ/ር ዐቢይን ለመደገፍ በመስቀል አደባባይ ድብልቅልቅ ያለ ሰላማዊ ሰልፍ ተዘጋጀ። ሰኔ 16 ቀን 2010 ዓ.ም። በዚያ ሰላማዊ ሰልፍ ላይ ለመካፈል ከመላው ሃገሪቱ ቁጥሩ ከፍተኛ የሆነ ህዝብ አዲስ አበባ ላይ ከተተ። ይህች ቀን ደርሳ ዐቢይ አህመድን “አብረንህ ነን” ለማለት የቸኮለው ህዝብ ሌሊቱን ሙሉ አውላላ ሜዳ ላይ አድሮ ጠቅላይ ሚኒስትሩን ጠበቀ። ሰዓቱ ደርሶ መስቀል አደባባይ በህዝብ ጎርፍ እስኪጥለቀለቅ እና ፕሮግራሙ ተጀምሮ ስልጣን ላይ ከወጣ ሶስት ወራት እንኳን ያልደፈነው ዶክተር ዐቢይ አህመድ እስኪመጣ ድረስ መታገስ አቅቶት ሲቁነጠነጥ የነጋለት ህዝብ፣ በዚያ የደስታ ስሜቱ እንደተሞላ ወደቤቱ እንዳይሄድ የደስታ ውርዴ ገጠመው። በሚሊዮኖች ሆኖ ድምጹ እስኪዘጋ ድረስ እየጮኸ “አብሬህ ነኝ” ያለውን ጠቅላይ ሚኒስትር ግድያ ሲሞከርበት በአይኑ ተመለከተ። ይህ ህዝብ በዚያ ሳቅና ደስታው ላይ ውሃ የቸለሱበትን እኩዮች እየረገመ ፣ ከሞት ያመለጠውን ጠቅላይ ሚኒስትሩን “አይዞህ” እያለ ፣ ግድያ በሞከሩት “ያልታወቁ ሃይሎች” ላይ ጥርሱን ነክሶና ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከሞት መንጋጋ ስለተረፈለት አምላኩን አመስግኖ ተቀመጠ።

“ይህች ሃገር እውነትም ሰው አይውጣልሽ” ተብላ ተረግማ ይሆንን? እውነትም “ሞልተሽ ደስ አይበልሽ፣ ጎድለሽ አታልቅሺ ተብላ ለስሜት ግራ ሆና እንድትኖር ተፈርዶባትስ ይሆንን?” ብሎ የሚጠይቅም በዝቶ ነበር የዛሬ ዓመት። ኮሎኔል መንግስቱ ሃይለማርያም ከኢህአፓ የግድያ ሙከራ መትረፉን ለህዝብ ለማሳየት ቁጭ ብድግ በሰራበት መስቀል አደባባይ ላይ ኮሎኔል ዐቢይ አህመድ ህዝብ እያየው ከሞት ድግስ አመለጠ። በዚያ የስሜት ግለት፣ በዚያ የቁጭት እና የበቀል ፍላጎት ፣ በዚያ ከጨለማ ወደ ብርሃን የመምጣት አይነት የማይታመን የደስታ ጊዜ ጠቅላይ ሚኒስትሩ በዚያ ንግግር ባደረገበት መድረክ ላይ ተመትቶ ቢወድቅ ኖሮ ዛሬ እየተባላንም ፣ ያሞገስነውን ጠቅላይ ሚኒስትር እየሰደብንም፣ ለድጋፍ የጮህንለትን ለውጥ እያንኳሰስንም፣ ስሜታችን እና አቋማችን በ360 ዲግሪ ተሽከርክሮም ቢሆን ከሞላ ጎደል በድጋፍና በተቃውሞ እየኖርንባት ያለችው ሃገር እጣ ፈንታ ምን ይሆን ነበር ብሎ መገመት ከባድ ይሆን ነበር። “እግዚአብሄር ከዘመናት ዝምታ በኂላ ለኢትዮጵያ የሰጠው ሰው ነው” ብሎ ፍጹም ባልጠበቀው መንገድ ከኢህአዴግ መሃል ያገኘውን፣ በኢትዮጵያ ፍቅር ያበደ ባለስልጣን “ጠቅላይ ሚኒስትሬ” ብሎ የማምለክ ያህል በሙሉ ልቡ የተቀበለ ህዝብ ድንገት በዚያ መድረክ ላይ ይህ ሰው ቢገደል ኖሮ ጣቱን ወደማን ይቀስር እንደነበርና ውጤቱስ ምን ይሆን እንደነበር መገመት በእርግጥም ከባድ ነው። ከባድ የስጋት ደመና ከላይዋ ሲገፈፍ ዘመን ያስቆጠረችው ኢትዮጵያ ይህንን ከባድ ቀንም እንዲሁ ተሻገረችው። እነሆም ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አህመድም የምርቃት እድሜያቸውን ሲኖሩ ፣ ለሞት ሩብ ጉዳይ ላይ ደርሰው ሞትን ያመለጡበትን ቀን ሊያከብሩ፣ በዚያው መድረክ ላይ “የፍቅር ቀን” ብለው የሰየሙትን ሰኔ 16 ቀን ሊዘክሩ፣ ህዝብም የመሪውን ሙት አመት ከማክበር ተርፎ ቀኑን በ “ነበር” ሊያሳልፈው ዋዜማው ላይ ደረሰ። ሰኔ 15 ቀን ።

## “ቀኑ እንዳይረሳ ብሎ...”

እንደታሰበው አልሆነም። ሞት መውጊያው የተሰበረበት ቀን ሊታሰብ አልቻለም። አንድ ያልተጠበቀ ሞት መጥቶ ፣ ዋነኛ ግዳዩን መጣል ቢያቅተውም ጥቂቶችን አቆሳስሎ እና ሁለት ቀናቸው የተቆረጠላቸውን ምስኪኖች ገድሎ በተመለሰበት የዓመት ቀን ሌላ ያልተጠበቀ ሞት መጥቶ አንዱንም ሳያስተርፍ አምስት ሰዎችን ቅርጥፍ አድርጎ በልቶ ሄደ። ሚሊኒየም አዳራሽ በተካሄደው የአስከሬን ሽኝት ስነስርዓት ላይ የተገኙ አንዲት እናት እንዳሉት “ሞት አቂሞና ቀኑ እንዳይረሳ ብሎ ተመልሶ መጣ” ። ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አህመድ ሞትን ባመለጡበት ቀን መታሰቢያ ዋዜማ ላይ የለውጡ እጅና እግሮች በሞት ተቀጠፉ። “የፍቅር ቀን” ተብላ ትዘከር የተባለችው ሰኔ 16 ቀን የሃዘን ቀን ሆና ተዘከረች። በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ አንድ ጥቁር ነጥብ ጠብ አለ። ይህች ሃገር ሲሰሩላት የነበሩ፣ ለዚህ ለውጥ አለመደናቀፍ ሲሉ ራሳቸውን ሰውተው ይታትሩ የነበሩ፣ ለውጡን ተከትለው የመጡትን ብዙ ፈተናዎቿን ለማስቆም እረፍት አልባ ሆነው የከረሙ ታላላቅ ባለስልጣናቷን በሰዓታት ልዩነት ውስጥ አጣች። ከትግራይ እና ከአማራ ህዝብ ማህጸን የወጡ፣ ኢትዮጵያዊነት ያጋመዳቸው ሁለቱ የመኮንን ልጆች ወደቁ። ዶክተር አምባቸው መኮንን እና ጄኔራል ሰዓረ መኮንን። የለውጡ ጉዞ መንገድ ጠራጊዎች እዘዝ ዋሴ እና ምግባሩ ከበደ፣ እናም የአንድ ዘመን የኢትዮጵያ የቁርጥ ቀን ልጅ ብ/ጀ ገዛኢ አበራ፤ ሁሉም ተያይዘው በሰዓታት ልዩነት በአንድ ቀን አለቁ። ለአንድ ሰው ሲል መጥቶ ሳይሳካለት የተመለሰው ሞት አመት ቆጥሮ ተመልሶ መጣና አምስት ሰው ይዞ ሄደ። ሃገሩን ማቅ ያለበሰ ክፉ ዜና።

## አሳምነው ጽጌ “በማን ላይ ቆመሽ ...”

አሳምነው ጽጌ ያኔ ወታደር ነበር። ከወታደርም መሪ ወታደር። እንደሚነገረውም ጀግንነት አለው። እንደሚባለውም ጦርነቶች ላይ ተሳትፏል። ደግሞም አሸንፏል። እንደተወራውም ፊት መውጣቱን ሕወሓቶች አልወደዱለትም። የሃገር መከላከያ ውስጥ በየመስመሩ የሚሰለፈው ወታደር ከየብሄሮቹ ተውጣጥቶ ተሰላፊውን ሁሉ የሚመራው ግን የትግራይ ታጋይ ብቻ ሆኖ በተዋቀረበት በዚያ ጊዜ አሳምነውን የመሰሉ ከሌላ ብሄር ተገኝተው በወታደራዊ ማዕረግ ከፍ ያሉ ወታደሮች ላይ ዐይን ቢጣል የሚገርም አይሆንም። እውነት ሆኖ ይሁን ወይስ ለፕሮፓጋንዳ ባይረጋገጥም እንደተወራው

▶





አማራው አሳምነው የአማራ ህዝብ ግፍ የሚያንገፈግፈው፣ የአማራ ህዝብ ችግር የሚቆረቁረው ወታደር ነበርና በሕወሓቶች ቀለበት ውስጥ ገባ:: ከዚያም ወደእስር ቤት ተወረወረ:: ከዚያ በኂላ የአሳምነው ወታደርነት እና ጀነራልነት አከተመ:: ከፍርግርግ ብረቶች ጀርባ ተከንችሮበት ቀረ:: በጊዜው ስለዚህ ሰው የሚያውቅም ብዙም አልነበረምና መታሰሩም ያን ያህል የጎላ ዜና ሆኖ አልቀረበም:: የኢትዮጵያ ህዝብ በህሊና እስረኞች የጠበበውን ከርቸሌን ሲያነሳ "ውጦ አይጠግቤ" ብሎ ተስፋ ቆርጦበታልና የእስርን ዜና ተላምዶታል:: የአሳምነውም ጉዳይ እንዲሁ ቀን የሚያነሳው ሊሆን ተዘነጋ:: ብዙው ሰው ቢረሳውም የአሳምነው እንደወንጀለኛ በእስር ቤት መበስበስ አንድ የምሬት እና የትግል መነሻ የሆናቸው የአማራ ልጆች ግን አሳምነውን በልባቸው ይዘው የነጻነቱን ቀን እያፋጠኑለት ነበር:: "አማራ በመሆኑ ታሰረ፣ ለአማራ ህዝብ በመቆርቆሩ እንደተራ ሰው ተከረቸመበት፣ አሳምነውን ማሰር የአማራን ህዝብ ከማሰር በምን ይለያል" የሚሉ የቁጭት ድምጾችም በውስጥ እየተቀጣጠሉ የብሶት ባሩድ ሆነው የፍንዳታውን ቀን አቀረቡት:: እናም ሕወሓት/ኢህአዴግ በኢህአዴግ ውስጥ በተነሳው የለውጥ ሃይል ተሸንፎ ከመንገዱ ገለል ሲል በዚሁ መንገድ አሳምነው ከእስር ቤት ወጣ::

እነተስፋዬ፣ እነገዱ፣እነ አምባቸው፣ እነእዘዝ፣ እነ ምግባሩ የታገሉለት ለውጥ አሳምነውን ከእስር አውጥቶ የነጻነት አየር እንዲተነፍስ አደረገው:: አሳምነው መፈታት ብቻ አይደለም፣ ስራ ተሰጠው:: ሃላፊነት ተጣለበት:: ወታደርነቱ እና የቀደመው ስርዐት ተገፊነቱ የአማራን ህዝብ በሰላም እና ደህንነት ዙሪያ ለማገልገል ብቁ አድርጎ ለስልጣን እጩ አደረገው:: የአማራ ክልል የለውጡ አመራር ያለምንም ማቅማማት አሳምነው የአማራን ህዝብ ጥቃት ይመክታል፣ በወታደራዊ ሙያው ህዝብን ያገለግላል፣ የክልልን ሰላም ያረጋግጣል ብሎ እጁን አውጥቶ መረጠው:: ከምክትል አስር አለቃ ጀምሮ ወደላይ ከተቆጠረ 12ኛ ደረጃ ላይ የሚገኘውን የብርጋዴር ጀነራል ማዕረግ ይዞ የነበረውን አሳምነውን አመራሩ "የአማራ ክልል ሰላምና ደህንነት ቢሮ ሃላፊ" አድርጎ ሾመው:: እሱን ብቻ ሳይሆን እንደርሱው ሁሉ "በአማራነታቸው ብቻ ሴራ ተሸርቦባቸው እስር ቤት ተወርውረዋል " የተባሉትንና ለውጡ ያስፈታቸውን የአሳምነው የማዕረግ እኩያ የሆኑትን ብ/ጀነራል ተፈራ ማሞንም ካሉበት ጠርቶ የክልሉ ልዩ ሃይል ሃላፊ አድርጎ ሾማቸው:: የአማራ ህዝብም አጨበጨበ:: ልጆቹን ጥሎ እንደማይጥል አሳየ:: እነአሳምነው አማራነታቸው ክብራቸው እንጂ ውርደታቸው እንዳልሆነ እንዲያውቁት እና በዚህም ስርዓቱን መቃወማቸው ትክክል ስመሆኑ ለራሳቸው እንዲያረጋግጡ እድል ሰጣቸው:: የክልሉ አመራር የሰላሙን እና የጸጥታውን ነገር ለነኚህ ሁለት ከእስር ቤት የወጡ ጄኔራሎች በተለይም ለአሳምነው ሰጥቶ ፊቱን ወደአስተዳደራዊ ጉዳዮች አዞረ::

ይህ ግን ብዙ መዝለቅ አልቻለም:: እንደግለሰብ ህልውናው በለውጡ ላይ የተንጠለጠለው አሳምነው፣ እንደውለታም የስራ ግንኙነት "በአልታዘዝም" መንፈስ የተቃኘ እንዲሆን ምክንያት ሆኖታል የሚል ነው ተብሏል::

## አጀጋኙ አለመረጋጋትና ተፈላጊው አሳምነው

"ለሆዳም በሬ ጭድ ያዝለታል" እንዲሉ ጊዜ ደግሞ ለወታደሩ አሳምነው ጠመንጃ እና ሃይል አዘዘለት:: በርግጥም ብዙዎች እንደሚናገሩት አሳምነው ጽጌ በእጁ የገባው ታጣቂ ብዛት ፣ የአማራ ክልል ከትግራይ ክልል ጋር ያለው የተካረረ የወሰን ችግር፣ በክልሉ ያለው "የጎበዝ አለቃ" ልምምድ በህዝብ ሰላም ላይ የፈጠረው እንቅፋት እና ስጋት ፣ በየቦታው የሚፈነዳው የርስ በርስ ግጭት ሁሉ ተዳምረው የርሱን የዕለት ከዕለት ትዕዛዝ መፈለጉ ግድ ሆነ:: ጊዜው የአማራ ክልል ቁልፍ ችግር የሰላም እና ደህንነት ጉዳይ ሆኖ የጎላበት መሆኑ ከአሳምነው ሞገደኛ ባህሪ ጋር ተዳምሮ "እኔን ብቻ ስሙኝ" አይነት የበላይነት ውስጥ ከተተው:: አሳምነው እንደወታደር የሚያጀግነው ምቹ ሁኔታ በክልሉ ከሚፈልገውም በላይ የሞላለት መሆኑ ብቻ ሳይሆን እሱንም ለዚህ ክልል ችግር መፍትሄ አምጪ ነው በሚል በቦታው ተፈላጊ ሰው ከእሳት መካከል ፈልቅቀው ያወጡት የአማራ ክልል የዛሬ ሃላፊዎች ከባድ ውለታ ያለበት አሳምነው፣ ከዚያም ባለፈ በሙያህ ህዝብህን አገልግል ብለው እንኳን ራሱ ሌላ ሰው በማያምነው "ሰርፕራይዝ" ከእስረኝነት ወደባለስልጣንነት ያሸጋገሩት አሳምነው "በማን ላይ ቆመሽ ማንን ታሚያለሽ" እንደሚለው ተረት፣ እሱን ለዚህ ባደረሰው ለውጥ እና በክልሉ የለውጥ ሃይሎች ላይ ፊቱን ማዞር ጀመረ:: በአማራ ክልል የአስተዳደር መዋቅር ውስጥ ከሚገኙ ክፍሎች በአንዱ ሃላፊ የሆኑ ባለስልጣን በግምገማ ላይ አሳምነውን በተመለከተ ሲናገሩ "አሳምነውን የሚመራው የክልሉ ህዝብም፣ የክልሉ ህግም፣ የክልሉ አመራርም ሳይሆን ማህበራዊ ሚዲያ ነው" ብለውት እንደነበርም ይነገራል:: የዚህ መነሻ ደግሞ አሳምነው የክልሉ ዋነኛ ችግር የሆነውን የሰላም እና ደህንነት ማረጋገጥ ጉዳይ በሃላፊነት መያዙ፣ ይህም በግጭት ሃይሎች በኩል ስሙን ያገነነለት መሆኑ ፣ በየጊዜው ለመገናኛ ብዙሃን የሚሰጠው ሞገደኛ መግለጫ የራሱን ደጋፊ ያበረከተለት መሆኑ ተዳምሮ ከክልሉ አመራር ጋር ያለው እንዲሆን አድርጎታል:: የማህበራዊ ሚዲያ በተለይም የፌስቡክ ጦስ ከሌሎች ክልሎች ሁሉ በባሰ ተጽዕኖ ያሳረፈበት እና ያም በሚፈጥረው ችግር የሚታመሰው የአማራ ክልል አሳምነው ጽጌንም ይኸው ተጽዕኖ ሳይቆጣጠርበት እንዳልቀረ ይገመታል:: ፌስቡክ ላይ የአማራን ጉዳይ የሚያቀነቅኑ አክቲቪስቶች፣ሁሌም አሳምነው ለአማራ ህዝብ ብሄርተኝነት ከፍታ ወሳኝ ሰው እንደሆነ አድርገው ሲስሉና ከሺህዎች ጋር ሃሳብ ሲለዋወጡ መዋላቸውም የተለመደ ነው:: "አሳምነው በዚህ ተሰማራ፣ በዚያ ጦር አሰማራ፣ ይህንን አደረገ፣ እነእከሌን አፋችሁን ያዙ አላቸው፣ እነእከሌ ላይ ጥቃት ከፍቶ ልክ አስገባቸው" አይነት መልዕክቶች መብዛታቸው ፌስቡክ ላይ ተተክሎ የሚውለውን ወጣት አስተሳሰብ ወደጭፍን ድጋፍ መምራቱም ብዙ የሚያስገርም አይሆንም:: እናም በማህበራዊ ሚዲያ ተጠቃሚዎች ዘንድ አሳምነው ጎልቶ እንዲወጣ እና "ጀግና" እንዲባል ምክንያት የሆነው የክልሉ ወቅታዊ ሁኔታ የርሱን ተፈላጊነትም በዚያው መጠን አጎላው::

**...ከትግራይ እና ከአማራ ህዝብ ማህጸን የወጡ፣**
**ኢትዮጵያዊነት ያጋመዳቸው ሁለቱ የመኮንን ልጆች ወደቁ።**
**ዶክተር አምባቸው መኮንን እና ጄኔራል ሰዓረ መኮንን።**
**የለውጡ ጉዞ መንገድ ጠራጊዎች እዘዝ ዋሴ እና ምግባሩ ከበደ፣**
**እናም የአንድ ዘመን የኢትዮጵያ የቁርጥ ቀን ልጅ ብ/ጀ ገዛኢ**
**አበራ፤ ሁሉም ተያይዘው በሰዓታት ልዩነት በአንድ ቀን አለቁ...**

## አዲሱ አዴፓ እና አሳምነው

በአማራ ህዝብ ትግል ሁለተኛው ትውልድ ፓርቲ አዴፓ ነው:: አማራ በፖለቲካ ውስጥ ተሳታፊ ከሆነ ከዚህ ቀደም ይወከልበት የነበረው ቅኝት ኢትዮጵያዊነት ብቻ ነበር:: በኢትዮጵያ ከሚገኙ ብሄሮች ሁሉ ኢትዮጵያዊነትን እንደማህተሙ ይዞ ሲሳደድበት እና ሲያሳድድበት የኖረ ህዝብ ካለ ያለማጋነን የአማራ ህዝብ ነው:: በአንድ በኩል ይህ ኢትዮጵያዊ ትርክቱ የብሄሮችን መብት ጨፍላቂ አድርጎታል፣ "ለኢትዮጵያ ካለእኔ …" አይነት ስሜት ውስጥ ከትቶታል የሚሉ አስተያየቶች ሲኖሩ በሌላ በኩል አማራ በብሄር ሳይደራጅ ኢትዮጵያዊነትን ማህተሙ አድርጎ በመኖሩ ተጎጂ ሆኗል እንጂ አልተጠቀመም የሚሉ አስተያየቶችም ይሰነዘራሉ:: በዚህ ሳቢያም ከ40 ዓመታት በፊት ትግሉ ሲጀምር በአብዛኛው አማሮች የተሰባሰቡበት የኢትዮጵያ ህዝቦች ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ኢህዴን) የድል ጮራ መታየት ስትጀምር ወደብሄርተኝነት ዝቅ እንዲል እና አማራውን የሚወክል ፓርቲ እንዲሆን በሕወሓት ስትራተጂስትነት የኢትዮጵያ ህዝቦች የሚለው ቃል ወደ ብሄረ አማራ ተቀናበረና ብሔረ አማራ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ብአዴን) ተባለ:: ይህ▶



ፓርቲ የአማራ ነው ሲባል አብዛኞቹ አመራሮቹ አማርኛ ተናጋሪ እንጂ አማራ አልነበሩም፡፡ ይህም ሕወሃት በአማራ ህዝብ ላይ በነበራት የኖረ ቂም የማይቀየሙ "ስጋ የማይስባቸው" አይነት ባለስልጣናትን ማፍራት ችሏል፡፡ በዚህ ሳቢያም ኤርትራዊው በረከት ስምዖን፣ ኦሮሞው አዲሱ ለገሰ፣ ደቡቡ ተፈራ ዋልዋ ወዘተ አማራን የመሩበት "ብአዴን" እንደፓርቲ ከህዝብ ጋር ሳይስማማ በቁሙ ፈረሰ፡፡ የአማራ ህዝብ የማይወክለኝ ብሎ ቂም የቋጠረበትን እና በተለይ ለአማራ ህዝብ መብት መረገጥ፣ መገፋት፣ መበደል፣ባይተዋር መሆን ምክንያት ነው የተባለው ብአዴን ላይ ፊቱን ሲያዞር ዛሬ ፊት የወጡት እዚሁ ፓርቲ ውስጥ የነበሩ የአማራ ልጆችም ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ወንድሞቻቸው ጋር ያንን ትግል አቀጣጥለው ዛሬ በለውጡ ሁለተኛውን ትውልድ የአማራ ፓርቲ (አዴፓ) ፈጥረው ህዝቡን መምራት ጀምረዋል፡፡

እንዲያም ሆኖ አዴፓ ጠንካራ ፓርቲ መሆን አልቻለም፡፡ ህዝብ እምነት ሊጥልበት የሚችል፣ የአማራን ህዝብ ጥያቄ ለማስመለስ የሚታትር እና እንደጎርፍ የሚግተለተሉትን ጥያቄዎች ደረጃ በደረጃ መመለስ የሚችል ፓርቲ አልሆነም፡፡ ይህ ደግሞ አብንን የመሳሰሉ ፍጹም ብሄርተኛ የሆኑ ንቅናቄዎችን ወልዷል፡፡ አብን ገና ብቅ ያለ ፓርቲ ሆኖ ከፍተኛ የአማራን ህዝብ ድጋፍ ያገኘውና የ40 ምናምን አመቱን ፓርቲ የተገዳደረው በዚህ ምክንያት ነው፡፡ አሳምነው አዴፓን እንደፓርቲ፣ አስተዳደሩን ደግሞ እንደስራ አስፈጻሚ ተቀብሎ በእርከን እየተመካከረ የጸጥታ እና ሰላም ማስከበር ስራ መስራት ላይ ክፍተት ማሳየት የጀመረው ገና በጠዋቱ ነው ይባላል፡፡ እንደመዋቅር እርሱ ለፓርቲው ማዕከላዊ ኮሚቴ ብቻ ሳይሆን ራሱም ላለበት ስራ አስፈጻሚ ውሳኔዎች መገዛት ሲገባው አሳምነው ግን በራሱ የሚመራ እና እኔ ያልኩት ብቻ ይሁን የሚል ግትር ሰው ሆኖ ወጣ፡፡ በድርጅታቸው ባህል ይህንን ከመርህ ውጪ መንቀሳቀስ የማይደግፉት አመራሮችም የአሳምነው እንቅስቃሴዎች የሚያሳድሩትን ተጽዕኖ እየገመገሙ ስህተቶቹን ለራሱ መንገር እና እንዲያስተካክል መምከር ላይ አተኮሩ፡፡

የክልሉ ኮሙኒኬሽን ዳይሬክተር አሰማኸኝ አስረስ እንደሚናገሩት አሳምነው ከአመራሮቹ ውሳኔ ጋር ከማይጣጣምባቸው ልዩነቶች አንዱ ታስረው ለውጡ ነጻ ባደረጋቸው ነገር ግን አሁንም ታጥቀው ሰፈር እንምራ እያሉ ያሉትን የፋኖ እና የአማራ ተጋድሎ ንቅናቄ አባላትን ወደስርዓት ማስገባት አንዱ ነው፡፡ አመራሩ ህዝቡን አቤቱታ መሰረት በማድረግ ከመንግስት ውጪ ማንም የታጠቀ ቡድን በክልሉ ሊገኝ አይገባውም የሚል አቋም ሲያራምድ አሳምነው በሌላ በኩል በነዚህ አካላት ላይ የተለሳለሰ አቋም ይዟል፡፡ ይህ መለሳለስ ደግሞ በነዚህ ቡድኖች ከፍ ያለ ድጋፍ እንዲያገኝ በአንጻሩ ከክልልሉ አመራር ጋር እንዲቃቃር ሳያደርገው እንዳልቀረ ይገመታል፡፡ በአማራ ክልል እየሰፋ የመጣው የሰላም እጦት በክልሉ ህግና ስርዓትን በአስቸኳይ ተግባራዊ በማድረግ የህግ የበላይነትን ለማረጋገጥ የፈጠረው የተጣደፈ ፍላጎት አሳምነው ጋር ሲደርስ የሚፈጸም አልመስል አለ፡፡ በዚህ ሳቢያም ይህ አቋም አሳምነው ከያዘው ተቃራኒ አቋም ጋር ታይቶ ሰፊ ጊዜ ተወስዶ ግምገማ ተካሂዶበት የነበረ ቢሆንም አሳምነው ግን የተሰጡትን ሂሶች መቀበል ሳይፈልግ፣ ስህተት ናቸው ያላቸውን ብቻ አጉልቶ በስራ አስፈጻሚው ውሳኔ ሳይስማማ ተለያይቷል፡፡ ብዙዎች እንደሚገምቱት የአሳምነው አካሄድ የፓርቲውንም ሆነ የክልሉን መስመር የሚያንጋድድ፣ ክልሉ ከጎረቤት ክልሎች ጋር በሚኖረው መስተጋብር ላይ አሉታዊ ስዕል የሚፈጥር፣ የማንአለብኝነት ውጤት የሆነና ከድርጅታዊም ሆነ ክልላዊ የስራ ሂደት ያፈነገጠ ነው በሚል አሳምነውን ከጸጥታ ዘርፍ ሃላፊነቱ ለማንሳት እቅድ ነበረው፡፡ ይህ ደግሞ ለአሳምነው ባህሪ የማይዋጥ ከባድ አደጋ ሆኗል፡፡ ይህ ጉዳይ ጀነራሉን ለአመጽ አነሳስቶታል ተብሎም ይታሰባል፡፡

ርዕሰ መስተዳድሩ ዶክተር አምባቸው የአሳምነውን አካሄድ በጽኑ የሚቃወሙ እና ህግና ስርዓት በክልሉ ተከብሮ አማራ ሳይከፋፈል በአንድ ስሜት ለልማት እንዲሰራ የማድረግ አቋም ነበራቸው ይባላል፡፡ በዚህ ሳቢያ በተደጋጋሚ ጊዜ ከአሳምነው ጋር የነበራቸው ውይይት ከመግባባት ርቆ ግልጽ ጸብ መሰል ነገር ውስጥ ገብቶም እንደነበር ይነገራል፡፡ የዶክተር አምባቸው አቋም የክልሉ ባለስልጣናት አቋም መሆኑን የተረዳው አሳምነው ከዚህ በኋላ የደረሰበት ውሳኔ ከባድ እንደነበር ከሆነው ነገር ለመገመት አያስቸግርም፡፡

## የአመጹ አሳዛኝ መጨረሻ

አሳምነው ድሮ ወታደር ነበር፡፡ ወታደር ማለት ስሜቱን ሳይሆን አላማውን የሚከተል፡ ፡ ግን አሳምነው ስልጣን ላይ ከወጣ በኋላ ወታደር መሆን አልቻለም፡፡ አሳምነው ከኋላው ያለው ከፍ ያለ የማህበራዊ ሚዲያ ተሳታፊ ወጣት ድጋፍ እና "ጀግና፣ ጥቃት መካች" ወዘተ የሚለው ሙገሳ ፣ በሌላ በኩል ወጣቱ በአዴፓ እና በአመራሮቹ ላይ ያለው "አይጠቅሙንም" አይነት ምልከታ ብቸኛና አስፈላጊ ሰው እንደሆነ እንዲያስብ ሳያደርገው አልቀረም፡፡ ስለሆነም ህዝብ አለልኝ በሚል መነሳሳት ጭፍን ስሜት ውስጥ ገባ፡፡ እናም ከአላማው ይልቅ በስሜቱ ተነዳ፡፡

ግደለው፣ ጥረገው፣ አጥፋው፣ በለው በሚሉ ቃላት የሚጠቀለሉ ጀግንነቶች የተጠና ዒላማ እና የታቀደ ግብ ስለሌላቸው ውጤታቸው ሁሌም አንገት ማስደፋቱ አይቀሬ ነው፡፡ አሳምነው ህዝብ አገልግል ተብሎ የተሰጠውን ስፍራ በራሱ ስሜት ለውሶ "ተው ይህንን አታድርግ" ያለውን አመራር እንደ እንቅፋት እና የአማራ ጠላት አድርጎ ማሰቡ ለደረሰበት የተሳሳተ ድምዳሜ መሰረት ሳይሆነው እንዳልቀረ ይገመታል፡፡ እናም ቀጣይ ፍላጎቱ ምን እንደሆነ እስካሁን ባልታወቀ ሁኔታ ሙሉ የአዴፓን አመራር ለማጥፋት ወሰነ፡፡ የአሳምነው ድርጊት የመንግስት ግልበጣ ሙከራ ነው የሚለው አገላለጽ ከፖለቲካ ትርጉም አንጻር ለፕሮፓጋንዳ ይውል ካልሆነ በቀር በባህሪውም ይሁን በአፈጻጸሙ ሁኔታ እንዲሁም ድርጊቱ የተፈጸመው በክልል አስተዳደር ላይ ከመሆኑ አኳያ ተቀባይነት የለውም፡፡ በብዙዎች አስተያየት የአሳምነው ድርጊት ግብታዊ እና ውጤቱ ያልተመዘነ ጥቃት ወይም የቀቢጸ ተስፋ እርምጃ ነው፡፡ የአሳምነው ጥቃት ተራ ቂም በቀል ነው፡፡ ግብ አልባ ጥቃት ነው፡፡ ሌሊት ሰው ቤት እንደገባ ሌባ የክልሉን ከፍተኛ አመራሮች በአሰቃቂ ሁኔታ ገድሎ ክልሉን እንደተሰረቀ ንብረት ተሸክሞ ሊሄድ? የዶክተር አምባቸውን ወንበር ይዞ ክልሉን በፕሬዚዳንትነት ሊመራ? አማራ ክልልን ከኢትዮጵያ ሊገነጥል? ምን ሊያደርግ?

ድርጊቱን ሲፈጽም የሚገዳደረው ሃይል እንዳይገጥመው የጸጥታ መዋቅሩን በክልሉ ፖሊስ ኮሚሽን አዳራሽ ስብሰባ ጠርቶ ፣ ቆይ ጠብቁኝ ብሎ፣ በቅርቡ ያስመረቃቸውን የልዩ ሃይል አባላት ይዞ ርዕሰ መስተዳድር ቢሮን አስከብቦ በቀን ተኩስ አስከፍቶ እና አስገድሎ ወደባለስልጣናት መኖሪያ ገስት ሃውስ መመለስ ትርጉሙ ምንድነው? ሚዲያውን ሳይነካ፣ ስብሰባ "መጣሁ" ብሏቸው ወደሄደው የጸጥታ ዘርፍ አመራሮች ሳይመለስ ፣ ያስማራቸው አባላቱ ተኩስ ከፍተውና እርሱን የተቃወሙትን ሁሉ መትተው ሲያበቁ እሱ መሸሹ ትርጉሙ ምንድነው? አሳምነው ጽጌ ስሜት እና ጠመንጃ ተዳምረው ከስብዕና ያወጡት፣ ማንም ያልጠበቀውን ምናልባትም የአማራ ክልል ፖሊስ ኮሚሽነሩ እንዳሉት "የዕብደት" ተግባር ነው የፈጸመው፡፡

በዚህ ሳቢያም አዴፓን ሰው አልባ አድርጎታል፡፡ አማራን ጠንካራ መሪ አሳጥቶታል፡፡ ክልሉን ቶሎ በማይተካ ባለልምድ የሰው ሃይል ክፍተት ውስጥ ጨምሮታል፡፡ በርግጥም ጠመንጃ በእጅ ላይ ስላለ ብቻ፣ የሚታዘዝ ወታደር በእጅ ላይ ስላለ ብቻ፣ ከስልጣን ልነሳ ነው የሚል ብስጭት በዚህ ላይ ስለተጨመረ ብቻ እንዲህ አይነት ፍጅት ውስጥ መግባት ተራነት እንጂ ክብር የሚያሰጥ በታሪክ የሚወሳ ድርጊትም አይደለም፡፡

## ጀነራሎቹን ጀነራሉ አስገደላቸው?

ከላይ ካነሳነው ሃሳብ አንጻር ጀነራል ሰዓረን ያህል ታላቅ የጦር ሰው እና የድሮ የስራ ባልደረባቸው ጀነራል ገዛኢን በጠባቂያቸው ማስገደል ለአሳምነው ምን ይበጀዋል ብሎ ማሰብ ብዙ ርቀት ወስዶ ከአንድ ድምዳሜ ላይ ለመድረስ አያበቃም፡፡ ስለሆነም ይህንን ለሴራ ትንተና የማይመች ኢ-ተዛማጅ ጉዳይ ለምርመራው ትተን ውጤቱን መጠበቅ የተሻለ አማራጭ ይሆናል፡፡ በዚያም ወጣ በዚህ ፣ ይህ ለውጥ ወሳኝ ሰዎችን አጥቷል፡፡ በነዚህ አመራሮች ህልፈት ወድቆ ባይሞትም ክፉኛ የቆሰለው ግን ለውጡ ነው፡፡ ለውጥ ያመጣው አሳምነው የለውጡን አምፖል ሰብሮ የራሱንም ብርሃን አጠፋ፡፡ አምባቸው እና ጀነራል ሰዓረ የሃገሪቱ ቁስሎች ባሉበት ስፍራ ላይ የተቀመጡ ፍቱን መድሃኒቶች ነበሩ፡፡ አሁን ቁስሉ ተገልጧል፡፡ የዝምብ ማዕድ ከመሆኑ በፊትም መሸፈን ይፈልጋል፡፡



ልዩ ዕትም

# ባህር ዳር ያቋጀን ሰዓት !

## ከአንድ ማህበረሰብ ወጥተው፣ በሁለት መንገድ የተጠፋፉ ሹማምንት

### በሮቤል ምትኩ

ሰኔ 15 ቀን 2011 ዓ.ም ሰሜናዊቷ የአማራ ክልላዊ መንግስት መዲና የሆነችው ባህርዳር ያልተጠበቁ አሳዛኝ ትዕይንቶችን አስተናገደች። በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ታይቶ በማይታወቅ መልኩ ጭካኔ የተመላበት፣ለአንድ ማሕበረሰብ መብት ቆመናል ያሉ ኹለት ቡድኖች "አንዱ በአጥፊ ሌላው በተጠፊነት" ጎራ ተመደቡ። ከምንም በላይ ደግሞ ከትቢያ ያነሳውን፣ የተገፈፈ ክብርና ሞገሱን የመለሰለትን አካል ረስቶ፣ አጥፊው አንገት የሚያስደፋ ድርጊት በመፈፀም፤ በሰላማዊ ትግል የተመለሰለትን እምነትና ተስፋ አሽቀንጥሮ ጣለው።

በአማራ ክልል ርዕሰ መስተዳድርና የካቢኔ አባላት ላይ የተደረገው ስልጣንን የመንጠቅና የመቆጣጠር መከራ አድማሱን አስፍቶ፣ አስቀድሞ በተዘረጋ ወጥመድ መሰረት ማዕከላዊ መንግስት ዙሪያ በመድረስ፤ "የቁርጥ ቀን ልጅ" የሆኑትን የጦር ኤታማዦር ሹም ሕይወት ቀጥፏል። አስቀድመው ከጡረታ የተሰናበቱት ነባሩ የሕወሓትና "የሎጀስቲክስ መሐንዲስ" ተብለው የሚሞካሹት ታጋይም፣ ከ"ኑግ ጋር የተገኘህ ሰሊጥ..." ዓይነት ዕጣ ገጥሟቸዋል። ለመሆኑ ይህ አሳዛኝ ክስተት፣ በተለይም በባህርዳር ምን ዓይነት ገፅታ ነበረው? አሸማቃቂውና አንገት አስደፊው ድርጊትስ እንዴት? በማንና ለምን? ተቀነባበረ? የሚሉትን ጉዳዮች እንመልከት።

ቅዳሜ ሰኔ 15 ቀን 2011 ዓ.ም የቀድሞው ብ.አ.ዴ.ን የአሁኑ አዴፓ ሥራ አስፈፃሚ የአስተባባሪ ኮሚቴ አባላት ስብሰባ ከቀኑ 10 ሰዓት ላይ ይካሄድ ነበር። በዚህ ስብሰባ ላይ ሰባት አባላት በመስተዳድሩ ሕንፃ ባለ የክልሉ ፕሬዝዳት ጽ/ቤት የመሰብሰቢያ አዳራሽ (ፕሬዝዳንቱ ዶ/ር አምባቸውን ጨምሮ) በሰዓታቸው ተገኝተዋል።

ለአማራ ክልል ሕዝብ እንታገላለን ያሉ አካላት፣ (በአቋምና አካሄድ ረገድ ከጀነራል አሳምነው ውጪ ሁሉም አንድ ናቸው) በተለይም ከትግራይ ክልል የፅጥታ ኃይሎች ይደርሳሉ ተብለው በሚገመቱ ጥቃቶች፣ ወልቃይትና ራያን በመሳሰሉ ጉዳዮች ከሚነሱ ውዝግቦች አኳያ አንዳንድ አለመግባባቶች ቢኖሩም, ብዙዎቹ ችግሮች መፍትሄ ሊበጅላቸው ፤በሰከነ አስተሳሰብ ሊፈቱ መቋጫ እየተፈለገላቸው ነበር። የዶክተር አምባቸው አመራር የአማራ ሕዝብን የሚወክል ቢሆንም፣ የማሕበረሰቡን ጉዳይ ኪትዮጵያዊነት ጋር አቆራኝቶ ሲንቀሳቀስ፣ "የአማራ ሕዝብ በደል እየበዛ ነው። ለዚህ ደግሞ የማንንም ትዕዛዝ አልጠብቅም" ያሉት፣ የክልሉ የፀጥታ ዘርፍ ቢሮ ሀላፊ ብ/ጀነራል አሳምነው ጽጌ ደግሞ በዘውጌ ፖለቲካ ተጠምደው፣ ከአገራዊነት ይልቅ በብሔርተኝነት ጠባብ መንገድ መንጎድ የጀመሩት በአዲሱ ሹመታቸው ማግስት ነበር።

በዕለቱ ስብሰባ ተቀምጦ ከነበረው አስተባባሪ ኮሚቴ አቅጣጫ በተለየ መንዝን የመረጡት፤ በቅርቡ ባስመረቁት የክልሉ ልዩ ኃይል አባላት ዝግጅት ላይ "ተከበናል፣በማንነታችን የተነሳ ልንጠፋ ከጫፍ ደርሰናል፤ይሄን ማክሸፍ የእናንተ ስራ ነው" በማለት የተናገሩትና ይፋዊ የሆነ ቅስቀሳ ያደረጉት ጀነራል፤ የሚሮጡለትን የከረረ የብሔርተኝነት ዕርምጃ የሚያሳካላቸው ታጣቂ ቡድንን ደግሞ በተለያዩ ዙሮች አሰልጥነው ካስመረቁት የልዩ ኃይል አባላት ውስጥ መልምለው ሲያዘጋጁ ነበር የሰነበቱት። "የአማራውን ሕዝብ እንወክላለን" የሚሉ የፖለቲካ ሰዎችና አንዳንድ የ"ፌስ ቡክ አብዮተኞች"፣ እንደክፉ ደዌ በክልሉ ልክፍት እንዲሆን አብዝተው የጮሁበት የአማራ ብሄርተኝነት መንፈስ ቅጥ ባጣ ሁኔታ መንሰራፋቱ የልብ ልብ የሆናቸው ብ/ጀነራል አሳምነው ጽጌ፣ ከቀኑ 10.30 አካባቢ "የእኔ ዕንቅፋት ናቸው" ያሏቸውን የክልሉን ከፍተኛ አመራሮች ሊያስወግዱ፣ ሁለት ኤፌ ኤስ አር መኪና ሙሉ የታጠቁ፣ የልዩ ኃይል ልብስ የለበሱ ታጣቂዎችን ይዘው ወደ መሰብሰቢያ ስፍራው ነጎዱ።

ለዘጠኝ ዓመታት በላይ በሕወሓት ላይ በሞከሩት አስፈላጊና ትክክለኛ መፈንቅለ መንግስት፣ በመለስ ዜናዊ ትዕዛዝ ዘብጥያ ወርደው የነበሩት ጄነራል "የአማራ ልጆች እርስ በርሳቸው የተበላሉበትን" አስቆጪ ተግባር ከመፈፀማቸው በፊት፤ ያለፈው ስህተታቸው እንዳይደገም በመስጋት፣ እቅዴን ያሰናክሉብኛል ያሏቸውን የተለያዩ የፖሊስ፣ የደህንነትና የመንግስት ባለስልጣናትን በየቢሮአቸው በታማኝ ታጣቂዎቻቸውአሳገቱ። ሁሉንም ነገር በሚፈልጉትና በሚያስቡት መንገድ ፀጥ ረጭ አደረጉ።

በተለይም የክልሉ ርዕሰ መስተዳድሩ ቢሮ ፊትለፊት የሚገኘው የእንግዳ ማረፊያ (ገስት ሀውስ) ውስጥ የሚኖሩ ባለስልጣናትን የክልሉ ኮሚኒኬሽን ጉዳዮች ቢሮ ኃላፊ፣ ኮ/ል አለበልና በአምላኩን፣ እንደ ጀነራል ተፈራ ማሞ ዓይነት የልዩ ኃይልና የፖሊስ ኮሚሽኑን ኃላፊዎች ባሉበት እንዲታገቱ፣ ትጥቅ እንዲፈቱ፣ በቢሮአቸው ያሉ ቢሮአቸው እንዲቀመጡ፣ በመኝታ ክፍሎቻቸው የተገኙም በር ከፍተው እንዳይወጡ በአሰማሯቸው ወታደሮች አማካኝነት ያልታሰበ ድንገተኛ የሆነ ጥብቅ መመሪያ አስተላለፉ።

ጀነራል አሳምነው ጽጌ ሁሉን ነገር ካስተካከሉ በኂላ በሁለት ግዙፍ መኪናዎች የጫኑትን ታጣቂዎች ይዘው በቅድሚያ ዶ/ር አምባቸው የሚመሩት ስብሰባ የሚካሄድበትን ሕንፃ ወረሩ። የታጣቂዎቹን አመጣጥ ጥቂት የባለስልጣናቱ አጃቢዎች ቢመለከቱትም፣ ሰዎቹ አስቀድመው የሚያውቋቸውና አለቆቻቸውን ያቀፈ ከመሆኑ አኳያ ቅጽበታዊውን ድርጊት በክፋት አልተመለከቱትም። በርግጥ ከባለስልጣናቱ ጠባቂዎች መሀል በዛን ቀን አስቀድመው ፍቃድ ጠይቀው የወጡ እንዳሉም ተሰምቷል።

በመሪያቸው የተሰጣቸውን ግዳጅ ለመፈፀም የተቅለበለቡ ሶስት የልዩ ኃይል አባላት ታጣቂዎች በፍጥነት እየተምዘገዘጉ የዶ/ር አምባቸውን ቢሮ ወረሩ። ታጣቂዎቹ በኃል በሩን ለመክፈት ያደረጉት ሙከራ ከውስጥ ሆነው ዶክተሩና እነ አቶ እዘዝ ላለማስገባት ባደረጉት ግብግብ ባለመሳካቱ፣ የጥፋት ተልዕኮ የተሰታቸው ታጣቂዎች በሌላኛው በር ዞረው ለመግባት አማራጭ ሲጠቀሙ፣ የክልሉ አመራሮች ደግሞ በሁለተኛው በር ለመውጣት ተሯሩጠው በመሄድ ካገኙት አንድ ክፍል ውስጥ እንደገቡ፣ ገዳዮች ደርሰውባቸው ተኩስ ጀመሩ።

የተኩስ ድምፁን የሰሙ የባለስልጣናቱ አጃቢዎች ወጥተው ምላሽ ለመስጠት ያደሩት ሙከራ አልተሳካም፡ ጀነራል አሳምነው ጠባቂዎቹ ሉበት ክፍል በር እንዲቆለፍና ባሉበት እንዲታገቱ አድርገው ለነበር። ታጣቂዎቹ ዶ/ር አምባቸው፣ አቶ እዘዝ ዋሴና አቶ ምግባሩ ከበደን ከመቱ በኂላ በተፈጠረው የሩጫ ክፍተት ሌላ ክፍል ውስጥ መደበቅ የቻሉትን አራት ከፍተኛ አመራሮች ትተው፣ ተጨማሪ ግዳጅ ለመቀበል ከፎቁ ወደ ምድር በፍጥነት ወረዱ።

አጋጣሚውን ለመጠቀም ያላመነቱት አራቱ ከፍተኛ ሹማምንት የጓዶቻቸውን ▶



መጨረሻ ለማወቅ ጥይት ወደሰሙበት ክፍል ሲደርሱ፣ የለውጡ አጋፋሪ፣ ብልህ፣ ደፋሩና ቁጡው ዶ/ር አምባቸው መኮንን እንዲሁም በአማራ ክልል የአደረጃጀት አማካሪ የሆኑት አቶ እዘዝ ዋሴ  ሳይመለሱ እስከ ወዲያኛው አሸልበዋል፡፡ ሌላኛው ባልደረባ የአማራ ክልል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ አቶ ምግባሩ ከበደ ደግሞ ክፉኛ ቆስለው፣ ደም እንደዥረት እየፈሰሳቸው በመሆኑ የተረፉት ጓዶች መጋረጃ ቀድደው ቁስላቸውን ከአሰሩላቸው በኋላ የሚሆነውን መጠባበቅና የደጅ እንቅስቃሴውን በመስኮት መቃኘት ጀመሩ፡፡

በኹለት ኤፍ.ኤስ.አር መኪኖች ተጭነው የመጡት የልዩ ኃይል አባላት፣ ሕንፃውን ዙሪያውን ወርረውት ከነበረበት ቦታ እየተነሱ መኪናቸው ላይ ተጭነው ከሕንፃው ፊት ለፊት ወደሚገኘው የክልሉ ሹማምንት ማረፊያ ገስት ሐውስና ሌሎች ቦታዎች አመሩ፡፡ ጀነራል አሳምነው ፅጌ ግዳጃቸው እዚህ ጋር የሚቆም አልሆነም፡፡ አመራሮች መሳሪያቸውና ሞባይላቸውን ተነጥቀው ባሉበት እንዲቀመጡ በማድረግ፣ ሙሉ የኃይል ሚዛኑን በቁጥጥራቸው ስር ለማድረግ የሞከሩት ጀነራል በተለይም በገስት ሀውሱ (እንግዳ ማረፊያው) ግቢ ወስጥ በወታደሮቻቸው ተከበው ከላይ ታች ሲወርዱ፣ መመሪያ ሲሰጡ ፣የጥፋት ድርጊቱን ሲያስተባብሩና በበላይነት ሲመሩ በግልጽ ታይተዋል፡፡

እስከ ምሽቱ አራት ሰዓት ድረስ አንዴ የዶ/ር አምባቸው ቢሮ የሚገኝበት የክልሉ መስተዳድር ሕንጻ፣ ሌላ ጊዜ ወደ እንግዳ ማረፊያው ሲመላለሱ የነበሩት፣ የአላስፈላጊው ዕርምጃ መሪ ብ/ጄነራል አሳምነው ከ13ቱ የአዴፓ ወሳኝ የስራ አስፈጻሚዎች ወይም ከዶክተር አምባቸው ካቢኔ አባላት አንዱ ቢሆኑም፣ እንደ ወረርሽኝ በተዛመተው የአማራ ብሔርተኝነት መንፈስ የሚናወዙ ጥቂት የማይባሉ ታጣቂዎችን በመመልመል ከዕስር እንዲፈቱ ታላቅ ትግል ባደረጉላቸው የክልሉ ፕሬዝዳንትና ባልደረቦቻቸው ላይ ከወሰዱት ዕርምጃ ባሻገር በውስጣቸው  ያለው ሃሳብ እውን እንዲሆን በተለያየ አቅጣጫ ሲባዝኑ፣ በሌላ በኩል የእሳቸው እሳቤ፣ የጥፋት ቡድኑ ዕርምጃ፣ የከረረ የብሔርተኝነቱ እንቅስቃሴ ያልጣማቸውና ትክክለኛው መንገድ የገባቸው፤ የክልሉ ልዩ ኃይልና የፖሊስ አባላት አመራሮች ዘንድ ከባድ ትንቅንቅ ገጠማቸው፡፡

በወታደራዊ ዕውቀታቸው የማይታሙት፣ “ንቁ ጀነራል” ናቸው የሚባሉት አሳምነው ጽጌ ከሚሰሩበት ካቢኔ፣ ከወከላቸው ሕዝብና መንግስት ፍላጎት አፈንግጠው የሄዱበት መንገድ ሙሉ በሙሉ ትክክል  ነው ብለው እንደሚያምኑበት በቂ ማረጋገጫና አንዱ ማሳያ ጀነራሉ ታላላቅ አገራዊ ግዴታዎችን በመሩበት ወኔ የተመላ ቀደምት ስራዎቻቸው ልክ፣ በ”ቅዠት የታጀበው ተራ  ኦፕሬሽናቸውን”ም የመሩት በድብቅና በስውር ሳይሆን በይፋ ነበር፡፡

በዕለቱ ሰማያዊ ሸሚዝና ስኩዌር ኮት የለበሱት የላስታው ተወላጅ አሳምነው ጽጌ፣ ተቀናቃኞቻቸውን በሙሉ በያሉበት ቢያስከብቡም ያልጠበቁት ኃይል ከመሀል አፈንግጦ በመውጣት፣ በእርሳቸው ምልምሎች ላይ ጥቃት ሰንዝሯል ፡፡ ይህን ተከትሎም ጄነራሉ “በለው”  “እሱም ይመታ” እያሉ ትዕዛዝ ሲሰጡ እንደነበር በር ተዘግቶባቸው ሁኔታውን በቀዳዳ ሲከታተሉ የነበሩ የአይን አማኞች ምስክርነት ሰጥተዋል፡፡

የተቀነባበረ ገፅታ እንዳለው የሚያሳየው በአዲስ አበባው የተፈጸመው የጠቅላይ ኢታማዦር ሹም የነነራል ሰዓረ መኮንን ግድያ የባህርዳሩ ተቀጥላና ሚዛን መጠበቂያ ድርጊት እንደሆነ ጉዳዩ የሚመለከተው አካል ከሰጠው መግለጫ መረዳት ይቻላል፡፡ ይሁን እንጂ ድንገተኛው የባህርዳሩ ጥቃት የደረሳቸው ጄነራል ሰዓረ መኮንን በሕገ ወጥ መንገድ ስልጣን ለመቆጣጠር የተንቀሳቀሰው ኃይል ሩጫን የሚገታና አጥፊዎቹን በቁጥጥር ስር የሚያውል በቂ ኃይል ወደ ስፍራው ከላኩና የሚሆነውን ነገር በመኖሪያ ቤታቸው ሆነው እየተከታተሉ ባለበት ሰዓት ነበር ከአጥፊው ቡድን መመሪያ ተቀብሏል ተብሎ በተጠረጠረ የግል ጠባቂያቸው ሕይወታቸው ሊያልፍ የቻለው፡፡

ጠቅላይ  ኢታማዦር ሹሙ የሰጡት መመሪያ ተግባር ላይ በመዋሉ፣ አዲሱ ጦር ከክልሉ ልዩ ኃይልና ፖሊስ ጋር በመቀናጀት የሚወስደው ዕርምጃ በመጠንከሩ ለሰዓታት ባህርዳርን የናጧት  ብ/ጀነራል አሳምነው ጽጌ ከምሽቱ አራት ሰዓት አካባቢ በገስት ሀውስ ውስጥ ሆነው የመጨረሻውን ትዕዛዝ ከሰጡ በኋላ፣ በታጣቂዎቻቸው ታጅበው ቦታውን ለቀው ሲወጡ ታይተዋል ሄደዋል፡፡ በተወሰነ ርቀት የደረሱባቸውን ጥቂት የክልሉ ፖሊስ አባላት ላይ በበርካታ ታጣቂዎቻቸው ታጅበው ተኩስ ከከፈቱ በኋላ፣ ለጊዜው ያዋጣኛል ብለው በመረጡት ቦታ በመሸሽግ ሳይወዱ በግድ ለአራትና አምስት ሰዓታት ብቻ ተቆጣጥረውት የነበረውን የኃይል ሚዛንና ከተማዋን የሽንፈት ካባ ላከናነባቸው የመከላከያ፣ የፌደራል ፖሊስና የአማራ ክልል ልዩ ኃይል አባላት አስረክበው በመጨረሻ ወደ ዘንዘልማ ከተማ ሸሽተዋል፡፡

## ከባህርዳር - አዲስ አበባ

በባህርዳር ከተማ ከቀኑ 10 ሰዓት ተኩል አካባቢ የጀመረው አሳዛኝ ድራማ ከፌደራል መንግስቱ ወሳኝ የፀጥታ ኃይሎች ጋር እንዳይደርስ የተለያዩ እንቅፋቶች በዚህች ከተማ ተፈጽሟል፡፡ የጠቅላይ ሚኒስትሩን መግለጫ በገደምዳሜው ከተመለከትነው የአማራ ክልል ርዕሰ መስተዳድርና መንግስታቸው ላይ የደረሰውን እገታና ጥቃት ለማክሸፍ አጋዥ ኃይል በፍጥነት እንዳይደርስ፣ ሆን ብለው የማጓተት ተግባር የፈፀሙ አካላት እንዳሉ መገንዘብ ይቻላል፡፡

ብ/ጀነራል አሳምነው ጽጌ የቀየሱት መንገድ ግቡን ቢመታ፣ የአማራ ክልልንና የፀጥታ ኃይሉን ሙሉ በሙሉ የመቆጣጠር ዕድሉ ቢገጥማቸው፣ የጦሩ ጠቅላይ ኤታማዦር ሹም ተገድለው የፌደራል መንግስቱ ውጥረት  ውስጥ ከገባ፣ እርሳቸው የአማራ ክልልና ሕዝብን በመወከል (ምናልባትም ሌሎች አክራሪ የአማራ ድርጅቶች በሂደት ሊዋሀዷቸው ይችሉ ይሆናል) ለመንግስትነት እንደ ብቸኛ አማራጭ በመቅረብ፣ በሽግግር መንግስት አልያም በጥምር መንግስት ስም ስልጣን የመጨበጥ ሕልምና ምኞት እንደነበራቸው አንዳንድ የፖለቲካ ተንታኞች ሂደቱን በማገናዘብ ግምታቸውን ያስቀምጣሉ፡፡

ከሶስት ቀን በፊት ችግኝ ሲተክሉ የታዩት፣ እውነተኛው የኢትዮጵያ የጦር አዛዥ ጀነራል ሰዓረ መኮንን ቅዳሜ ሰኔ 15 ቀን ትንሽ አመም አድርጓቸው በመኖሪያ ቤታቸው ነበሩ፡ ፡ ወደ ማምሻው አካባቢ በባህርዳር ከተማ ታጣቂ ቡድኑ ያደረሰው አላስፈላጊ ጥቃትን በተመለከተ ቆፍጠን ያለ ትዕዛዝ ያስተላለፉት የጦር አዛዡ፣ ሁኔታው ያስደነገጣቸው በተለያዩ የአገሪቱ ክልሎች የሚገኙ የጦር መኮንኖች፣ የፌደራል መንግስት ባለስልጣናት ወደ እጅ ስልካቸው በተደጋጋሚ በመደወል ለሚያቀርቡላቸው ጥያቄዎች በቂ ምላሽ እየሰጡ፣ ዝርዝር ሁኔታውን ከሰዓታት በኋላ እንደሚገልጹላቸው፤ በውጤቱ ረገድ ግን የነውጠኞቹን እንቅስቃሴ  እንደተቆጣጠሩና የሚያሰጋ ነገር አለመኖሩን ሲያበስሩ ነበር፡፡

በተለይም ጀነራሉ የሚኖሩበት አካባቢ የሚገኙ የተለያዩ ሹማምንት የሁኔታውን መረጋጋት ከጦር አዛዡ ከሰሙ በኋላ ፣ለደቂቃዎች መረጋጋት ቢችሉም በብርሃን ፍጥነት የተሰማው ተደጋጋሚ የተኩስ ዕሩምታ፣ የጀነራል ሰዓረ መኮንንን መገደል የሚያውጅ ይሆናል ብለው አልጠበቁም ነበር፡፡ በተመሳሳይ ዘወትር ከጎናቸው በማይለዩዋቸው “ታማኝ” ጠባቂዎቻቸው ቁጥጥር ስር በዋለው ግዙፉ መኖሪያ ቤታቸው መኝታ ክፍላቸው ውስጥ ሆነው፣ በተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎች የባህር ዳሩን እንቅስቃሴ እየተቆጣጠሩና መከላከያ ሰራዊቱን እየመሩ የነበሩት ምርጡ የጦር ሰው የሞት ጥላ እያንዣበባቸው መሆኑንም ፈጽሞ አልገመቱም፡፡

ከደቂቃዎች በፊት ሊጠይቋቸው በመጡት፣ በአስራ ሰባት ዓመቱ የበርሃ ትግል ዘመን አብረዋቸው ከነበሩትና በጡረታ ከተሰናበቱት ጀነራል ገዛኢ አበራ ጋር እየተጨዋወቱ ባለበት ሰዓት፣ በሐሜት ደረጃ የባህር ዳሩ “አላስፈላጊ ጦርነት” መሪ የትውልድ መንደርና የቅርብ ሰው ነው የሚባለው አጃቢ፣ ድንገት ወደ ጄነራሉ መኝታ ቤት ዘው ብሎ በመግባት የጥይት ናዳውን አወረደው፡፡ “ሻይ ቡና”እያሉ ሊጨዋወቱ የመጡት ጡረተኛው ጄነራልም እግረ መንገድ የግዳጁ ሰላባ በመሆን ከኢታማዦሩ ጎን ተሰው፡፡

ያፈነገጠውና ነውረኛውን ድርጊት የፈጸመው የግል ጠባቂ ተኩስ መከፈቱን ተከትሎ፣ ወደ እሱ ጥቃት የሰነዘሩትን ቀሪዎቹን አጃቢዎች ሸሽቶ በአንድ ከፍል ውስጥ ገብቶ ቢቆልፍም፣ ዙሪያውን እንደተከበበና መውጫ አማራጭም እንዳጣ ሲረዳ፤ ከእነ ሚስጢሩ ራሱን አጠፋ፡፡ ለውጡን በማስቀጠል ረገድ ከበረሃ ጓዶቻቸው የብሔርተኝነት ስሜት ይልቅ ኢትዮጵያዊነታቸውን በማስቀደማቸው ወያኔዎች “ከሃዲ” ያሏቸው የጦር መሪም በዚህ መልክ ፍጻሚያቸው ዕውን ሆነ፡፡ አራት ሰዓት ባልሞላ የዕብደትና የቅዠት ተግባር አገር ሊጠቅሙ የሚችሉ፣ የተለያዩ ታላላቅ ሰዎች በባህርዳርና በአዲስ አበባ የሞትን ፅዋ ተጎነጩ፡፡ ድርጊቱን አቀነባብረዋል የተባሉት የጦር ሰውም ከኹለት አስጨናቂ ሌሊቶች በኋላ፣ በእለተ ሰኞ ዕኩለ ቀን ከተደበቁበት ስፍራ ወደ ሌላ ቦታ ሲሸሹ ተገደሉ፡፡ ከአንድ ማህበረሰብ የወጡ ልጆች በሁለት መንገድ፣ (በዜግነት ፖለቲካና በብሄር ፖለቲካ) ተጉዘው ያለምንም ውጤት ተጠፋፉ፡፡



ልዩ ዕትም

# “ሞት ባያስደስትም አስገዳዩ ፅዋውን እንኳን ቀመሰው ! ! ”

## ወ/ሮ የሹሜ ደምሳሽ የዶክተር አምባቸው ባለቤት

*ወ/ሮ የሹሜ ደምሳሽ ከዶ/ር አምባቸው ጋር የአንድ አካባቢ ተወላጆችናቸው። በትዳር ለረጅም ጊዜ አብረው አብረው ኖረዋል። የወ/ሮ የሹሜ ደምሳሽ ትውልድ ሥፍራቸው፣ታች ጋይንት ልዩ ቦታው ቀንጠፍት ማዳ አካባቢ ማዳ መድኃኔዓለም ሲሆን፣ የባለቤታቸው የትውልድ ቦታ ደግሞ ላይ ጋይንት ቀንጠፍት ሥላሴ ነው። ከዶክተር አምባቸው ጋርሦስት ጉልቻ የመሠረቱትበ1989 ዓ.ም ነው ። ከወ/ሮ የሹሜ ደምሳሽ ፣ከመጀመሪያ ልጃቸው ከነፃነት አምባቸውና ከአጎታቸው ልጅ ምክር ጌትነት ጋር በመኖሪያ ቤታቸው ተገኝተን ልዩ ቃለ ምልልስ አድርገናል።*

**ግዮን፡- በጥቂቱ ስለቤተሰበዎ ቢነግሩን?**

ወ/ሮ የሹሜ፡- ከዶክተር አምባቸው ጋር የተጋባነው በቤተሰብ ነው። እርሱ ወደ 12ኛ ክፍል እንዳለፈ እኔ ደግሞ ከ8ኛ ወደ 9ኛ ክፍል እንዳለፍኩ፤ ኢህአዴግ አገራችንን ሲቆጣጠር ትምህርት ተቋርጦ ስለነበር ተጋባን። ይሁንና እርሱ ወዲያው ብዙም ሳይቆይ ወደ ትግሉ ሄደ። እኔ በወቅቱ አርግዤ ቀረሁ። በአጠቃላይ በአሁኑ ሰዓት አንድ ወንድ እና 4ሴቶች ልጆችን አፍርተናል።

**ግዮን፡- በባለቤትዎ ላይ የደረሰውን የሞት አደጋ እንዴትና መቼ ሰሙ?**

ወ/ሮ የሹሜ፡- በቤቴ ውስጥ ከእንግዳ ጋር ቁጭ ብዬ እያወራሁ እያለ የአክስቴ ልጅ ስልክ ደውሎ ‹‹ ባህርዳር ምክር ቤት አካባቢ ተኩስ ይሰማል አሉ፣ አምባቸው ያለው የት ነው?›› አለኝ። እኔም ስመልስለት ‹‹ እዚያው ነው እንጂ የት ይሆናል!? ››አልኩት፡ ፡ወዲያው መንፈሴ ተጨነቀ። ስንረባበሽ አንዱ ደውሎ ‹‹ እግሩን ነው የተመታው!! ›› ይለኛል። የእኔ ምላሽ ደግሞ ‹‹ እግሩም ተቆረጠ እጁ፣ በህይወት ብቻ ይምጣልኝ፣ ለልጆቹ ከነህይወቱ ይኑርልኝ!! ›› አልኩ። እንደዚያ እያሉ ሲያታልሉኝ አደሩና ‹‹ አሁን ይመጣል፣ የአጥንት ስፔሻሊስት ጋር ጥቁር አንበሳ ሊመጣና ሊገባ ነው … ›› እያሉኝ ስጠብቅ ቆየሁ። ጠዋት ግን ማረፉን አረዱኝ።

**ግዮን፡- ባለቤትዎ ከመሞቱ በፊት ለመጨረሻ ጊዜ የተገናኛችሁት መቼ ነበር?**

ወ/ሮ የሹሜ፡- እዚሁ አዲስ አበባ ሰንብቶ የሄደው ረቡዕ ዕለት ነበር። ወደ ጎንደር ሄዶ ከዚያም ወደ ባህርዳር መሄዱን ነው



የማውቀው። በስልክ ምንም ያለኝ ነገር የለም። እርሱ የሚሰራው ሥራውን ብቻ ነው።

**ግዮን፡- ቤተሰባዊ ሕይወታችሁ ምን ይመስል ነበር?**

ወ/ሮ የሹሜ፡- ያምር ነበር… በጣም!! መጫወት መዝፈን ለልደትም፣ ለክርስትናም እንዲሁ በአዘቦቱ ቀን አምባቸው ‹‹ እንብላና እንጠጣ እንጫወት፣ ደግሺና ሰው እንጥራና እንብላ… ›› ይላል። ለማስመሰል ሳይሆን ጊዜ ካገኘን በጨዋታ ጓደኞቹን ሰብስቦ ማሳለፍ ነው የሚፈልገው።ለልጆቹ በጣም ትሁትና አንድም ቀን ተቆጥቶና ገርፎም አያውቅም፡ ፡ እኔን እንዲያውም ልጆቹን ስቆጣ ‹‹ ተይ!! አትንኪያቸው ልጆቼን!!… ›› ይላል።

**ግዮን፡- ከዚህ ቀደም ያሳለፋችሁት የመከራ ጊዜ ነበር?**

ወ/ሮ ሹምዬ፡- የመከራ ጊዜ እስካሁን አልገጠመኝም። የእኔን ከዚህ ቀደም እናቴን ነው በህይወት ያጣሁት፣ (ያረፈችው) እርሱ (አምባቸው) ደግሞ ስለ አባቱ አውርቶ አይጠግብም። እኔን ሳያገባ ነው ወላጅ አባቱ የሞቱበት። ሕይወቱ እስከላፈበት ጊዜ ድረስ ወላጅ አባቱንና ተስፋዬን ያነሳል። (ተስፋዬ ጌታቸው አምና የሞተውን) እርሱን በማሰብ ዓመቱን ሙሉ እንዳለቀሰ ነው። ምንጊዜም ማታ ማታ ያለቅሳል። ‹‹ ተስፋዬን!! ተስፋዬን አጣሁት!! ተቆረጥኩ ›› እያለ ነው።አባቱን ሳይታሰብ ኢህአዴግ ገብቶ ታመው ህክምና ተቋርጦ ስለነበር የትርፍ አንጀት ህክምና ሳያገኙ ጠዋት ታመው ማታ ነው የሞቱበት፡ ፡ ‹‹ ህክምና ቢያገኝ ኖሮ አባቴ ይተርፍልኝ ነበር!!…›› ይል ነበር። ጓደኛው በ45 ዓመቱ ነው የሞተው፣ ሁልጊዜ የሚያለቅሰው ለእርሱ ነው። ተስፋዬ የትግል አጋሩ ነው፣ የእህቱ ባል ነው፣ ጓደኛው ነው።

**ግዮን፡- ስለ ዶክተር አምባቸው ፀባይ የጓደኞቹ አመለካከት ምን ይመስል ነበር?**

ወ/ሮ የሹሜ፡- እኔ እንደማውቀው በጣም ይወዱታል፣ ያከብሩታል። አምባቸው አይዋሽም፣ አምባቸው ደፋር ነው፣ አምባቸው ጀግና ነው፣ እኔ ስላልኩኝ አይደለም፣ አገር ይናገር። አምባቸው ሁሉም ያከብረዋል፣ አምባቸው በመድረኮችና በቤት ውስጥ ይለያያል ›› ነው የሚሉት ጓደኞቹ። እቤት ውስጥ ከቤተሰቦቹ ጋር ይጫወታል፣ በሥራ ወቅት ደግሞ ሥራ ነው።

**ግዮን፡- አምባቸው ስለ ለውጡ ሂደት ያለውን አቋም እንዴት ይገልጹታል?**

ወ/ሮ የሹሜ፡- አምባቸው እኔ እንደማውቀው አምባቸው የለውጡ ዋናው ሰው ነው፤ እርሱና ተስፋዬ ለለውጡ ዋጋ ከፍለዋል። ለውጡን ዳር ለማድረስ ሳይታክት እየሰራ ነበር።

**ግዮን፡- የዶክተር ዐቢይ አሕመድን የትግል ጉዞ አስመልክቶ ዶ/ር አምባቸው ያደረጋቸው ነገሮች ምንድን ናቸው?**

ወ/ሮ የሹሜ፡- ሁሉም እንዳሉ ቢሆንም (ብአዴኖች) እንደማውቀው እነርሱ ናቸው ለውጡን ያመጡት የምለው። ተፋትገው፣ ተዋግተው ዶክተር ዐቢይን ለመምረጥ ትልቅ አስተዋፅኦ ያደረጉት እነርሱ ናቸው።

**ግዮን፡- የባለቤትዎ በህይወት መለየት የመላው ኢትዮጵያ ሕዝብ ሀዘን ከመሆኑ በተጨማሪ በእርስዎውስጥ ምን ዓይነት ጠባሳ ጥሎ አለፈ?**

ወ/ሮ የሹሜ፡- እንደእኔ እንደእኔ በመጀመሪያ የሞትነው በዋነኝነት እኔና ቤተሰቦቼ ነን!! እኔና ቤተሰቦቼ በጣም ተጎድተናል። እኔን ብቻ አይደለም የጎዳው ልጆቼን፣ ቤተሰቤን፣ ወገኔን፣ ዘመዴንና ቀጥሎም ኢትዮጵያን!! ተጎድተናል፡ ፡ ሁሉም ሰው ተጎድቷል። አምባቸው ምንም ▶

ልዩ ዕትም



የማይገኝ ሰው ነው። አምባቸው እንደ አንድ ሰው አይጠራም!! አምባቸው ብዙ ነው። ግን ምን አደርገዋለሁ?!

**ግዮን፡- ዶክተር አምባቸው የነበረው የትግል ጉዞ በምን መልኩ እንዲቀጥል ትፈልጋላችሁ?**

ወ/ሮ የሹሜ፡- በትግሉ ውስጥ ያሉትን አራት ጀግኖች በአንድ ቀንቢጠፉም፣ አሁንም ትግሉ ይቀጥላል!! አለ!! የኢትዮጵያ ሕዝብ፣ የአማራ ሕዝብ ደሙን ይመልስልኛል ብዬ ነው የማስበው። የአማራ ህዝብ እነርሱን ማሰር ሳይሆን ያጠፋልኛል ነው የምለው!!እነርሱ ባለቤቴን ቢሮ ላይ የገደሉት እነርሱ መጥፋት አለባቸው። ሌላ ምንም የምለው የለም። ይመልስልኛል!! የአገሬ ወጣት!! የአገሬ ህዝብ ይመልስልኛል። የአምባቸው ደም እንዲሁ ፈስሶ አይቀርም!! (ይህንን ቃለ ምልልስ ያደረግነው በ17/10/2011 ጧትሲሆን ምሽት ላይ ያደረግነውን ቃለ ምልልስ እነሆ፡- )

**ግዮን፡- በአሁኑ ሰዓት ከመገናኛ ብዙሃን የሰማነው ዜና የወንጀል አቀናባሪ የተባሉት ‹‹ የፀጥታና የደህንነት ኃላፊው አሳምነው ፅጌ መሞታቸው እየተነገረ ነው ምን አስተያየት አለዎት?!**

ወ/ሮ የሹሜ፡- አኩርቶኛል..... የሀገሬ ህዝብ፣ የአማራ ህዝብ ተበቅሎልኛል!! ምንም እንኳ ባለቤቴን ባላገኘውም የእርሱን ፅዋ ማግኘቱ ተደስቻለሁ አመስግኛለሁ። ህዝቡንም ሰራዊቱንም አመስግኑልኝ። በጣም ደስ ብሎኛል!!

**ግዮን፡- ወ/ሮ የሹሜ ባለቤትዎትን ህልፈት(ሞት) እንዴት አመኑ?**

ወ/ሮ የሹሜ፡- አሁንም አላመንኩም!! አሁንም አሟሟቱ ህልም ነው የሚመስለኝ፣ ቅዠት ነው የሚመስለኝ!! እስከ አሁን አላመንኩም!! ላልቅስ?! ልበድ እንጂ እውነት አላመንኩም!!

**ግዮን፡- ባለቤትዎ ለትዳሩ የነበረው መስዋዕትነት ምን ይመስል ነበር?**

ወ/ሮ የሹሜ፡- ለትዳሩ ትልቅ ክብር ነበረው። ትዳሩን በጣም ይወዳል በጣም!! እንዲያው ምን ልበል?... በጣም ያከብራል። ጊዜ የለውም ሁልጊዜ ለትምህርትም ለስራም ይሮጣል፣ ሥራውን ያጠብቃል፣ ትምህርቱን ያጠብቃል። ትዳሩን አክባሪ ነው።

**ግዮን፡- ቀደም ሲል 5ልጆች እንዳላችሁ ነግረውናል፤ ስማቸውን ከዕድሜያቸው ጭምር ቢነግሩን?**

ወ/ሮ የሹሜ፡- ልጆቻችን አምስት ናቸው። የመጀመሪያ ልጃችን ነፃነት አምባቸው 28 ዓመቷ ነው። 2ኛዋ መዓዛ አምባቸው 25 ዓመቷ ፣ 3ኛው ዮሴፍ አምባቸው 12ዓመቱ፣ 4ኛው አፎሚያ አምባቸው 6ዓመቷ፣ 5ኛ የማሪያም አምባቸው ሶስት ዓመት ተኩል ዕድሜ ላይ ይገኛሉ።

**ግዮን፡- ሀዘኑን አስመልክቶ ከቅርብም ሆነ ከርቀት በአጠገብዎ ያሉ በምን መልኩ እያፅናኑዎት ነው?**

ወ/ሮ የሹሜ፡- እስከአሁን አብረውን የሚበሉ፣ አብረውን የሚጫወቱ፣ በቤተሰባዊ አቀራረብ ብዙዎች ቀርበው እያስተዛዘኑኝ ነው። ዘመድ ጓደኞቹና የሃይማኖት አባቶችም አልተለዩኝም። በደስታም የነበሩት አሁንም በሀዘንም አሉ። እዚሁ ናቸው።

**ግዮን፡- አሳምነው ጽጌን ቀደም ሲል እርስዎ ያውቋቸው ነበር?**

ወ/ሮ የሹሜ፡- አላውቃቸውም!! እርሱ ሲነግረኝ ተከራክረው እንዳስፈቱት አውቃለሁ። እነርሱ ናቸው ባለው ነገር ታግለው ነው ያስፈቱት። ፍቅር እንደነበሩና ጓደኛ እንደነበሩ ነው የማውቀው፣ ከእዚያ ውጪ ያለውን አላውቅም።

**ግዮን፡- ለህዝብ የቆመን ሰው ቀደም ሲል ተከራክረው እስከማስፈታት የደረሱለትን ሰውጀርባ ሰጥቶ መግደል እንዴት አገኙት?**

ወ/ሮ የሹሜ፡- እብደት ነው!! በሽታ ነው የምለው እንጂ በሌላ በምንም አልገልፀውም!! በሽታ ነው ወይም ታመዋል ወይም አብዷል እንጂ ተከራክረው አስፈትተውት መድረክ ላይ ቢሮ ላይ ጤነኛ ሰው አጋሩን የሚገል አይመስለኝም!! የሰይጣን ሥራ እንጂ ከዚያ ውጭ የምገልፅበት ቃል የለኝም። ሰው የሆነ ሰው እንደዚህ ዓይነት ሥራ አይሰራም!!

**ግዮን፡- በድጋሚ ማስተላለፍ የሚ ፈልጉት መልዕክት ካለ?**

ወ/ሮ የሹሜ፡- የባህርዳርን ሕዝብ፣ የኢትዮጵያን ህዝብን እና ሁሉንም ዘመድ ወገን ዘመዱን እንኳን ደስ አላችሁ። እርሱም የእነርሱን ፅዋ እንኳን አገኘ!! ምንም እንኳን ሞት ባያስደስትም አስገዳዩ ፅዋውን እንኳን ቀመሰው። ግን ይህ የእግዚአብሔር ሥራ ነው።

**ግዮን፡- ስለነበረን ቆይታ በእኛና በግዮን መጽሔት ዝግጅት ክፍል አንባቢያን ስም እናመሰግናለን።**

ወ/ሮ የሹሜ፡- እኔም አመሰግናለሁ።

# “አላመንኩም! አባቴ ይመጣል የሚል ተስፋ ነው ያለኝ!”

## *ነፃነት አምባቸው፣*

## *የዶ/ር አምባቸው የመጀመሪያ ልጅ*



*የዶ/ር አምባቸው የመጀመሪያ ሴት ልጅ ነች። በአሁኑ ሰዓት ትምህርቷን ጨርሳ በስራ ላይ እንደምትገኝ ነው የገለፀችው። የማስተርስ ዲግሪዋን ዘንድሮ በ ‹‹ ፐብሊክ ሄልዝ ›› ትይዛለች፤ ያላትን የኃዘን ጊዜ ተሻምተን በቤታቸው ውስጥ ያደረግነውን አጭር ቆይታ እነሆ።*

**ግዮን፡- ይህንን የአባትሽን የዶ/ር አምባቸውን አስደንጋጭ ሀዘንና መርዶ መቼና እንዴት ሰማሽ?**

ነፃነት፡- በስልክ ተደውሎ ‹‹ ክልል ምክር ቤት አካባቢ ተኩስ አለ!!... ›› ነው የተባልነው። ይህንን እንደሰማን ወዲያውኑ አንዳንድ የምናውቃቸው ሰዎች ጋር ስንደውል ስልክ አይነሳም። የስልክ ጥሪያችንን የሚመልስልን ሰው የለም!! .... ቆይቶ ‹‹ ትንሽ ችግር ተፈጥሮ ነበር። አባታችሁ ትንሽ ጉዳት ነው የደረሰበት እንጂ ደህና ነው!! ›› አሉ። እኛም ደህና ነው ብለን በተስፋ ስንጠብቅ ምንም የምናገኘው ወሬ የለም!! ከዚያም ስንጠብቅ አንዴ ‹‹ ሆስፒታል ገብቷል... ፣ ይድናል፣ ወደዚህ እየመጣ ነው... ›› ሲሉን ተስፋ ነበረን። ሆስፒታል ገብቷል ብለን ነበር። እያሰብን አደርን። ጧት ላይ ግን ማረፉን ነገሩን።

**ግዮን፡- ወላጅ አባትሽን ዶ/ር አምባቸውን እንዴት ነው የምትገልጪው?**

ነፃነት፡- እርሱን የምገልፅበት ቃላት የለኝም!! (ለቅሶ) ከአባት በላይ ነው፣ እንደ አባት እንኳን ቆንጥጦኝ አያውቅም። እንደ አባት ተቆጥቶኝ አያውቅም። እንደ ጓደኛዬ ነው። እንደ ጓደኛዬና





ከዚያ በላይ ነው።

**ግዮን፡- አባትሽ ለቤተሰቡ ምን ያህል ቅርበት ነበረው?**

ነፃነት፡- እርሱ እንደሚታወቀው ሁሌም ሥራ ቢበዛበትም ያለችውን ጊዜ አብቃቅቶ የተለየ ፍቅር ለቤተሰቡ ነበረው፡ ፡ ለሁላችንም የሚያሳየን ፍቅር ነበረው። ለሁላችንም ለቤተሰብ ፣ ለወዳጅ ዘመድ፣ ጎረቤት የአባትነት ፍቅር ነበረው። እርሱ የሁሉም ሰው አባት ነው፣ የተለየ ፍቅር ነው ያለው።

**ግዮን፡- በባህርዳር የመፈንቅለ መንግስት ያስተባበሩትን አካል አባትሽ በደንብ ያውቋቸው ነበር?**

ነፃነት፡- እኔ ምንም የማውቀው ነገር የለም። እርሱ እንደሚያውቅም አላውቅም፡ ፡ እርሱ ሰው አማኝ ነው። የሚያውቅ አይመስለኝም። ይኖራልም ብሎ የሚገምት አይመስለኝም እርሱ አምኗቸው ነው የገባው እንጂ እንደዚህ ዓይነት ነገር ይፈጠራል ብሎ ከመጀመሪያ ቢጠረጥር ጥንቃቄ ማድረጉ አይቀርም ነበር። እርሱ ግን በሙሉ ልቡ አምኖ ነው የገባው ብዬ ነው የማስበው።

**ግዮን፡- በአሁኑ ሰዓት በአባትሽ ላይ አደጋውን አስተባብሯል የተባለው አካል ተወግዷል ተብሏልና ምን ይሰማሻል?**

ነፃነት፡- ምንም የምለው ነገር የለኝም። እግዚአብሔር የሚሆነውን ነው ያደረገው እንግዲህ። እግዚአብሔር የፈቀደው ሆኗል።

**ግዮን፡- የአባትሽን የዶክተር አምባቸውን ህልፈት አምነሽ ተቀብለሻል?**

ነፃነት፡- አላመንኩም!! እስከ አሁንም አላመንኩም!! አባቴ ይመጣል የሚል ተስፋ ነው ያለኝ።

**ግዮን፡- ማስተላለፍ የምትፈልጊው መልዕክት ምንድን ነው? ለሀገር የተሻለ የሚያደርጉ ሰዎችን አደጋ የሚያደርሱባቸውን ከመምከር አኳያ?**

ነፃነት፡- እራሳቸውን እየጠበቁ ሥራቸውን እንዲሰሩ ነው። እርሱ አገሬ አገሬ ብሎ ‹‹ አትሂድ ቢያንስ እኛ እንፈልግሃለን ›› ስንለው ‹‹አገሬ ይበልጥብኛል!! ›› ብሎ ሄዶ በሀገሩ ሰው ነው የተገደለው። ባመነው ሰው፤ ስለዚህ ማንም ቢሆን ማንንም ማመን የለበትም። ሰው ራሱን ብቻ ነው ማመን ያለበት እላለሁ።

**ግዮን፡- ሀዘንሽን ግለጪ ብትባይስ?**

ነፃነት፡- የደረሰብኝ ከባድ ሀዘን ነው!!

**ግዮን፡- ቤተሰቦችሽ እየተፅናኑ ይሆን?**

ነፃነት፡- እግዚአብሔር የበለጠ ያፅናናን ሌላ የምለው ነገር የለም?

**ግዮን፡- እግዚአብሔር ለቤተሰቡ መፅናና ትን ይስጣችሁ።**

ነፃነት፡- አሜን!!

# "ሰው ለአገሩ እየሰራ የሚገደል ከሆነ እንዴት እንደሚቀበለው አላውቅም!"

## ወ/ሮ ምክር ጌትነት የዶ/ር አምባቸው መኮንን የወንድም ልጅ



ወ/ሮ ምክር ጌትነት፣ የአባቷ የታናሽ ወንድም ልጅ የሆነው ዶክተር አምባቸው መኮንን የአጎቷ ልጅ መሆኑን ትናገራለች። የእኔ አባት ታላቅ የእርሱ አባት ታናሽ ናቸው ትላለች ወ/ሮ ምክር ስለደረሰባቸው ሀዘን ለግዮን መፅሔት ስትገልጽ፣ ሐዘንዋን ተጋፍተን ለትንሽ ደቂቃ ሀሳብዋን ተጋርተናል።

**ግዮን፡- የዶክተር አምባቸውን ዜና እረፍት እንዴት ሰማሽ?**

ወ/ሮ ምክር፡- ሰዎች ሰምተው ለባለቤቴ ደወሉለት። ለማጣራት ሞክሬ ግራ ሲገባኝ ቤቴን ትቼ ምሽት ውጭ አደርኩ። ሲነጋልኝ የምይዘውና የምጨብጠው ሳጣ ወደ ባለቤቴ ቤት ዝም ብዬ መጣሁ። ምክንያቱም ደግሞ ለቅሶውን (አሟሟቱን) በትክክል የሚገልፅልኝ በማጣቴ ነው። ከቤተሰቡ ጋር ስቀላቀል ሁሉም እያለቀሱ ነው የደረስኩት፡ ፡ ማመን ነው ያቃተኝ እስካሁንም ማመን አልቻልኩም። እኔ እንጃ!! ... እንዴት እንደምችለውም አላውቅም። የአባቴ መሳይ ነው። እንዴት እንደምረሳውም አላውቅም።

በሀዘኑ ዙሪያ ላስተላልፍ የምፈልገው፣ ለሀገር መስራት እንደዚህ ከሆነ ባይሰራ ቢቀር!! በእርግጥ ለሀገር ብሎ ነው የሞተው፡ ፡ ሌላው ሰው በሀገር መሞት ሊያስደስተው ይችላል፤ ያለጥፋትህ ‹ አገሬን ላልማ…፣ ወገናችንን አንጉዳ!!... › የሚለውን ሀሳብ ሲናገር ነው የማውቀው። ወንድሜ ስለሆነ ሳይሆን ከአፉ የሚወጣው ‹‹ እንተጋገዝ!!... ›› በማለት እየሰራ ባለበት ሰዓት ከቤቱ ወጥቶ ወንድሜ በማለፉ በጣም አዝናለሁ፡ ፡ እኔ እንጃ አገሩ በላው!! እንዲህ ሊደረግ አይገባም። ለሀገሩና ለኢትዮጵያ ሁሉ ነው እርሱ የሚሰራው። እኔ እንጃ !! ምን እንደምል አላውቅም!!

**ግዮን፡- አሟሟቱን (የዶ/ር አምባቸው መኮንን) የኢትዮጵያ ህዝብ እንዴት ሊቀበለው ይችላል? ብለሽ ታስቢያለሽ?**

ወ/ሮ ምክር፡- ሰው ለአገሩ እየሰራ የሚገደል ከሆነ እንዴት እንደሚቀበለው አላውቅም!!... ለሀገር መሥራት የሚያስገድል ከሆነ የኢትዮጵያ ህዝብ ይፍረድ። ለግልህ እየሰራህ ብትሞትም ምንም አይደለም፡ ፡ ይህ ሰው ለሀገሩ ነው የሰራው። ለሀገሩ የሰራ ሰው ደግሞ ‹‹በርታና ላግዝህ ›› ነው የሚባለው እንጂ በራሳቸው መሳሪያ ስብሰባ ላይ ሲገሉት በመቻላቸው በጣም ነው የማዝነው። ሀገሪቷ እንድታድግ የሚፈልግ ዜጋ ቢሆን እንደዚህ አያደርግም፤ ገዳዮቹ አገሪቷ እንድትለማ አይፈልጉም። ሰዎቹ ሰዎችም አይመስሉኝም።

**ግዮን፡- በቅንብሩ ላይ የተሳተፉት ተገድለዋል ተብሏልና ያንን የሞትን ፅጣ መቅመሳቸውን እንዴት አገኘሽው?**

ወ/ሮ ምክር፡- የሰው ልጅ መሞቱ ባያስደስተኝም እንደእኔ እንደግሌ በጣም ነው ደስ ያለኝ፡ ይህ ሰው ታስሮ ነበር፡ ፡ ከእስር ቤት አስፈቱት ከተፈታ በኋላ አብሮ እየሰራ ነው ያለው። አብረሀ እጅና ጓንት ሆነህ መስራት እየቻልክ እያለ በተቃራኒው እርሱን ሌላ ሴራ ተጠንስሶ ሕይወቱ እስከሚጠፋ በመደረጉ በጣም ነው የማዝነው። አስገዳዩ በመሞቱ በጣም ነው ደስ ያለኝ። ‹‹ ለምን?!!.. ›› ቢባል ሌላም ሰው ገሎ እስር ቤት ከሚገባ፣ እንደዚሁ ቢገደል ነው የምመርጠው። እስካሁንም ብዬ አላውቅም። ለሀገሩ የሰራ የሚገደል ከሆነ አስገዳዩ መሞቱ በጣም ነው ደስ ያለኝ። ግን እኔ እንጃ !! ምን ልበል?

**ግዮን፡- ሀዘኑን እንዴት ትገልጪዋለሽ?**

ወ/ሮ ምክር፡- ሀዘኑን አልችለውም፤ የእርሱ ሀዘን ለእኔ ብቻ አይደለም፤ ወንድምነቱን ለኢትዮጵያ ህዝብ ነው የሚሰራውና የሚያገለግለው። ሁሌም ሀዘኑ መቼም አይወጣልኝም ፤ግራ ገባኝ በስመአብ (ለቅሶ)።

**ግዮን፡- እግዚአብሔር ለአንቺና ለቤተሰቡ መጽናናቱን እንዲሰጣችሁ የግዮን መፅሔት ዝግጅት ክፍል ይመኛል።**

ልዩ
ዕትም



ርዕሰ አንቀጽ

# የአዲሱ የለውጥ አስተዳደር ቀይ መብራት

ሰሞኑን በባህርዳር እና በአዲስ አበባ የተከሰተው አሸማቃቂ እልቂት፣ ሁሉንም ኢትዮጵያዊ ቆፈን ውስጥ የከተተ ክስተት ነበር፡፡የተወሰደው የኃይል እርምጃ በብዙ መለኪያ እጅግ ኋላ ቀር፣ በሐሳብ ልእልና ከማያምኑ ለሕገ-አራዊት ልቦናቸውን ከሰጡ መናጆዎች የመነጨ ነው፡፡ በጅምላ ርሸናው፣ በለውጡ ሒደት ላይ ፊት ለፊት የተሰለፉት ቱባ ሹማምንቶች ጭዳ ሆነዋል፡፡ ኀልፈታቸው እንደ ሀገር መስቀልያ መንገድ ላይ መቆማችንን የሚጠቁመን ነው፤በተለይ ቅጥ ያጣው የክልሎች የፀጥታ መዋቅር፣ ውሎ አድሮ ማጣፊያው ከሚያጥር ችግር ውስጥ ሊከተን እንደሚችል፣ምልክት ትቶልን አልፏል፡፡

የባህርዳሩ አይነት የተዘረከረከ የፀጥታ እና የደህንነት መዋቅር ሊወለድ የቻለው ገደብ ካልበተጀለት እና የልኡላዊ ሀገር መከላኪያን ገጽታን እየተላበሰ ከመጣው የልዩ ኃይል አደረጃጀት ነው፡፡ለጤና፣ለመንገድ እና ለትምህርት መዋል ከሚገባው በጀት እየተቀነሰ፣ ለልዩ ኃይል የሚፈሰው መዋእለ ንዋይ፣ ውስን በሆነው የሀገሪቱ ሀብት ላይ ከፍተኛ ኪሳራ እያስከተለ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ፣ የልዩ ኃይል አደረጃጀቱለቁጥጥር የማይመች እጅግ ወደ ጎን የተለጠጠ እና ተጎራባች ክልሎች እርስበርሳቸው በሥጋት የሚጠባበቃቁበትን አጥፊ የፖለቲካ ድባብን ፈጥሯል፡፡ ልክ እንደ ዘመነ መሣፍንት፣በማእካለዊው መንግሥት ላይ የበላይ ለመሆን የሚዳዱ ጠንካራ የዳር ኃይሎችን እያፋፋ ይገኛል፡፡ የሰሞኑ የባህር ዳር ክስተት ይኸን ጨረፍታ እውነታ የሚያንጸባርቅ ነው፡፡

በአማራ ክልል የተከሰተው የመንፍቅለ-መስተዳድር ሙከራ ለሀገር የሚተርፍ ዳፋ እንደነበረው መታዘብ ችለናል፡፡የተፈጠረውን ድንገተኛ የፀጥታ እና የደህንነት ምስቅልቅል ኹነት በጊዜ አደብ ማስገዛት ባይቻል ኖሮ፣ሀገሪቱ በአራቱም ማእዘን የምትናጥበትን የግጭት ማእበሉን መወለዱ አይቀርም ነበር፡፡ ትኩሳቱ ወደሌሎች የሀገራችን ክፍሎች እንዳይዛመት፣ በክልሉም ሆነ በማእከላዊው መንግሥት የተወሰደው እርምጃ በአዎንታዊነት የሚወሰድ ነው፡፡

የመንግሥት ቀጣይ ፈተና፣ የግጨትን እውነተኛ ዳናከጥንስሱ መርምሮ ለሕዝብ ይፋ ማድረግ ይሆናል፡፡በዚህ ረገድ የሚታየው ዝንጉነት ዋጋ ያስከፍላል፡፡የሰሞኑ የፖለቲካ ምስቅልቅል፣ ለውጡን ለሚቃወሙት ኃይሎች ከወደቁበት ቀና ብለው የጥፋት ተልእኮዋቸውን ለመፈጸም የሚያነሳሳቸው እንደሚሆን እሙን ነው፡፡ በየአቅጣጫ አስፍስፈው የሚጠብቁት አክራሪ የዘውጌ ኃይሎች፣አደጋውን ሌላ መልክ እና ጠባይ ለማሲያዝ ፣የሴራ ንድፈ ሀሳባቸውን ከመቀመር እንደማይቦዝኑ በቅጡ መረዳት ይኖርብናል፡፡ በተለይ የማኅበራዊ ሚዲያን በመጠቀም፣ በአዲሱ የለውጥ አስተዳደርላይ ተጨማሪ ጫና ማሳደር የሚችሉበት አጀንዳ ቅቡል እንዲሆን እንደ መልካም አጋጣሚ ሊወስዱት ይችላሉ፡፡ስለዚህ መንግሥት የግጭቱን ተፈጥሮ ፍትሓዊ እና የሕግ የበላይነትን ታሳቢ ባደረገ መልኩ ሊመረምረው ይገባል፡፡በሕወሓት/ኢሕአዴግ የአገዛዝ ዘመን ዓይነት ሐጣኑንም፣ጻዲቁም አብሮ የሚደቆስበት የሕግ አሠራር መከተል ለዳግም አዙሪት ይዳርገናል፡፡አጥፊዎችን በመለየቱ ሒደት የመንግሥት ጥበብ እና ሆደሰፊነት በእጅጉ የሚጠበቅ ነው፡፡

ባጠቃላይበየአካባቢው ብልጭ ድርግም የሚሉት ሥርዓት አልበኝነት የአዲሱ የለውጥ አስተዳደር ፈተና ሆነው ቆይተዋል፡፡የሰሞኑ ክስተት ግን በተጀመረው በተስፋ ሒደት ላይ የተደነቀረ የማስጠንቀቂያ ቀይ መብራት ነው፡፡ይኽንን የሥጋት ደመና ለመግፈፍ በሚደረገው ጥረት ውስጥ የሁለም ድርሻ አስፈላጊ ነው፡፡ ከምንም በላይ ሀገር ይቀድማል እና፣ አሁን ከገባንበት ቅርቃር ውስጥ መውጣት አለብን፡፡ ለዚህ ደግሞ የለውጡን አስተዳደር ኂሳዊ በሆነ መልኩ እየደገፍን መቀጠል እጃችን ላይ ያለ ብቸኛ አማራጭ ነው፡፡


**ግዮን መጽሔት**
**ኢትዮ ሐበሻ ኅትመትና**
**ማስታወቂያ ኃ/የተ/የግ/ማኀበር**
**በየሳምንቱ ለኅትመት የምትበቃ መጽሔት**

**ማኔጂንግ ዳይሬክተር**
ፍቃዱ ማ/ወርቅ

**ዋና አዘጋጅ**
ሮቤል ምትኩ
አድራሻ፡- የካ ክ/ከተማ
ወረዳ 2 የቤት ቁጥር 475

**ከፍተኛ አዘጋጅ**
ብሩክ መኮንን
ፍቅርተ ተሾመ
ሙሉጌታ አክሊሉ

**ተባባሪ ዘጋቢያችን**
ቶማስ አያሌው(ከአሜሪካ)

**አምደኞች**
ወንድሙ ነጋሽ(ኢ/ር ከለንደን)
ተረፈ ወርቁ
ሁሴን ከድር

**ክርኤቲቭ ዲዛይን**
ፍፁም ንጉሴ

**ጸሐፊ**
ሠላም ግርማ

**የዝግጅት ክፍሉ አድራሻ**
አራዳ ክ/ከ ወረዳ 09
የቤት ቁጥር 552/1
አምባቸው ህንፃ 2ተኛ
ፎቅ ቢሮ ቁ. 207
ፖስታ ቁ. 676 ኮድ 1029
ስልክ ፡ +251 911 22 76 61
+251 912 165606
+251 118 12 2333
ኢ-ሜይል፡
enqu2013@ gmail.com
Ghion2011meg@gmail.com
**Facebook**
Gihon-meg Fekadu
www. facebook.com/enqu2013



በዚህ መጽሔት ላይ የሚወጡ ጽሑፎች በሙሉ ማተሚያ ቤቱን አይመለከትም



**አታሚ**
ቴዎድሮስ ገብሩ ማተሚያ ቤት ፤ አራዳ ክፍለ ከተማ
ወረዳ 10 የቤ.ቁ. 066/ሀ
0911223335/ 0911420506



ልዩ
ዕትም

# ዶ/ር አምባቸው መኮንን
# ከ1963-2011



ዶ/ር አምባቸው መኮንን ከአባታቸው መኮንን ሲሳይና ከእናታቸው ///// .......... በጎንደር ክ/ሀገር ጋይንት አውራጃ፣ በአሁኑ ደቡብ ጎንደር ዞን ታች ጋይንት ወረዳ፣ ልዩ ስሙ አጤቱ ኪዳነማርያም ተብሎ በሚጠራው ቀበሌ ተወለዱ። ዕድሜያአቸው ለትምህርት ሲደርስ፣ የአንደኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በአጤቱ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት፣ የ2ኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በንፋስ መውጫ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት እየተከታተሉ ባለበት ወቅት፣ በጊዜው የነበረው ስርዓት የሚያደርሰውን የሕዝብ ጭቆና በመቃወም ወደ ትግል በመግባት፣ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ከሰላምና መረጋጋት በኋላ ለማጠናቀቅ ችለዋል።

ዶ/ር አምባቸው መኮንን የከፍተኛ ተቋም ትምህርታቸውን በኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩንቨርስቲ፣ በምጣኔ ሀብት ሳይንስ ኢኮኖሚክስ በዲግሪ፣ የማስተርስ ትምህርታቸውን ደግሞ በሁለት የውጭ አገራት፤ በደቡብ ኮርያ ስኩል ኦፍ ፐብሊክ ፖሊሲ ኤንድ ማኔጅመንት፣ በእንግሊዝ ኬንት ዩንቨርስቲ ማስተር ኦፍ ሳይንስ ኢንተርናሽናል ፋይናንስ ኤንድ ኢኮኖሚክ ዴቨሎፕመንት በ"እጅግ ከፍተኛ" ማዕረግ ተመርቀዋል። የፒ.ኤች.ዲ ትምህርታቸውን በእንግሊዝ ኬንት ዩንቨርስቲ በምጣኔ ሐብት ሳይንስ በመከታተል በከፍተኛ ማዕረግ አግኝተዋል።

ዶ/ር አምባቸው መኮንን፤ በትምህርት ክትትላቸው ፈጣን ተማሪ የነበሩ ሲሆን፣ ትምህርታቸውን በተከታተሉባቸው ሁሉም ዩንቨርስቲዎች ተሸላሚና ተወዳዳሪ ተማሪ ነበሩ። የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን እየተከታተሉ በነበረበት ወቅት የነበረውን ጭቆና በመቃወምና የሕዝባዊ ትግሉ አካል በመሆን፣ በለጋ ዕድሜያአቸው የቀድሞውን ኢህዴን፣ የአሁኑን አ.ዴ.ፓ ከ1982 ዓ.ም ጀምሮ በመቀላቀል በትጥቅ ትግሉ ወቅት ወሰኝ የሆነ አስተዋእጾ አበርክተዋል። የትጥቅ ትግሉ ተጠናቆ በሽግግር መንግስቱ ወቅትና ሕዝባዊ መንግስት ከተመሰረተ በኋላ በድርጅትና በመንግስት የተሰጣቸውን ኃላፊነቶች በቁርጠኝነትና በታማኝነት ተወጥተዋል።

ባለፉት 29 ኣመታት ከክልል እስከ ፌደራል መንግስት ከፍተኛ ኃላፊነት ያለመታከት አመራር ሰጥተዋል። አመራር ከሰጡባቸው ዋና ዋና ኃላፊነቶች፡- ከ1982 እስከ 1988 ዓ.ም ድረስ፣በሰሜን ጎንደር ዞን ላይ ጋይንትና ፋርጣ ወረዳዎች፣ በሰሜን ሸዋ ዞን ጣርማ በርና ሀገረማርያም፣ ከሰም ወረዳዎች ሕዝብን በማደራጀትና ከማንቃት ባሻገር ለመብቱና ለጥቅሙ እንዲታገል አድርገዋል።

ከ19 91 ዓ.ም ጀምሮ ለሁለት ዓመታት የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የስራ አመራር ተቋም ዋና ዳይሬክተር በመሆን በብቃት አገልግለዋል። በወቅቱ ፈታኝ የነበረውን የክልሉን መንግስት የመፈፀም አቅም ለማሳደግ፣ የአስፈፃሚዎችን አገልግሎት አሰጣጥ ብቃት ከፍ ለማድረግ ስልጠናና አመራር ሰጥተዋል። ዶ/ር አምባቸው በደቡብ ኮርያና እንግሊዝ ዩንቨርስቲዎች የማስተርስ እና የዶክትሬት ዲግሪያአቸውን ከተከታተሉ በኋላ፣ አቅማቸውን ይበልጥ በማሻሻል በክልልና በፌደራል መንግስት የተለያዩ ከፍተኛ የኃላፊነት ቦታዎች ሰርተዋል።

በ1993 ዓ.ም ከደቡብ ኮርያ እንደተመለሱ፤ የአማራ ክልላዊ መንግስት ንግድ ቢሮ ኃላፊ በመሆን የክልሉ የንግድ ስርዓት ዘመናዊነት እንዲላበስ በማስቻሉ ረገድ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አበርክተዋል። ከ1994 — 1995 ዓ.ም የቀድሞው ብአዴን ማዕከላዊ ኮሚቴ ጽ/ቤት ኃላፊ በመሆን፣ ወቅቱ የሚጠይቀውን አመራር ሰጥተዋል። ለአንድ ዓመት ያክልም የጥረት ኮርፖሬት ም/ስራ/አስፈፃሚ በመሆን አመራር ሰጥተዋል።

ከ1993 ዓ.ም እስከ 1998 ዓ.ም ድረስ የአማራ ክልላዊ መንግስት ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ ኃላፊ በመሆን፣ በክልሉ የተጀመረው የንግድ ሪፎርም ተጠናክሮ እንዲቀጥልና በክልሉ ለኢንቨስትመንት ምቹ ሁኔታዎች እንዲፈጠሩ የሚያስችሉ አሰራሮች እንዲዘረጉ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አበርክተዋል። የዶክትሬት ዲግሪያቸውን በምጣኔ ሀብት አጠናቀው ከተመለሱ በኋላም፣ ከ2003 ዓ.ም እስከ 2005 ዓ.ም ድረስ የአማራ መልሶ ማቋቋም ድርጅት ዋና ዳይሬክተር በመሆን በክልሉ የግብርናና የተፈጥሮ ሀብት ልማት ስራ እንዲፋጠን፣ እንዲሁም የምግብ ዋስትና ችግር ያለባቸው ስፍራዎች በልዩ ድጋፍ ከችግር እንዲወጡና አርሶ አደሩ ጤናውን ጠብቆ እንዲያመርት የሚያስችሉ፣ ልዩ ልዩ ልምዶችን በማስፋፋት ረገድ ከስራ ባልደረቦቻቸው ጋር በመሆን አመርቂ ስራ በመስራት ውጤታማ ለመሆን ችለዋል።

ከ2006 እስከ 2008 ዓ.ም በምክትል ርዕሰ መስተዳድር ደረጃ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ ልማት መንግስት የከተማ ልማትና ቤቶች ኮንስትራክሽን ቢሮ ኃላፊ ሆነው አመራር ሰጥተዋል።

ዶ/ር አምባቸው መኮንን የክልሉን ከተማ ልማት ቢሮ በመሩበት ወቅት፣ ዛሬ በአማራ ክልል ከተሞች ተሞክሮ የሚሰድባቸው በማሕበር የተደራጁና የየከተማውን ፕላን ጠብቀው የተሰሩ የመኖሪያ ቤቶች፣ ዕውን እንዲሆኑ በማድረግ አሻራቸውን አሳርፈዋል። ዶ/ር አምባቸው መኮንን ከዚህ በኋላ በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የከተማ ልማት ሚኒስቴር ሚንስትር፣ የኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ሚኒስትርና በሚኒስትር ማዕረግ የጠቅላይ ሚኒስትሩ የመሰረተ ልማት አማካሪ በመሆን የሚወዷት ኢትዮጵያንና ሕዝቦቿን በታማኝነት አገልግለዋል።

ከየካቲት 29 ቀን 2011 ዓ.ም ጀምሮ የክልሉን ሕዝብ ጥያቄ በመቀበል፣ የአማራ ክልላዊ መንግስት ርዕሰ መስተዳድር ሆነው በመሰየም የሚወዱትን ሕዝብ በቅንነትና በታማኝነት በማገልገል ላይ ነበሩ። ዶ/ር አምባቸው መኮንን የታች ጋይንት ወረዳን ሕዝብ በመወከል የአማራ ክልላዊ ም/ቤት አባል፣ የአማራን ሕዝብን በመወከል የኢፌድሪ ፌደሬሽን ም/ቤት አባል በመሆን የተጣለባቸውን ሕዝባዊ አደራ በታማኝነትና በብቃት ተወጥተዋል።

ዶ/ር አምባቸው መኮንን ከመንግስት ኃላፊነታቸው በተጨማሪ ላለፉት ዓመታት የአማራ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ ማዕከላዊ ኮሚቴ አባልና ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባል፣ የኢህአዴግ ም/ቤት አባልና የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባል በመሆን እንዲሁም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ የአማራ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (አዴፓ) ም/ሊመንበር በመሆን በከፍተኛ የድርጅት ኃላፊነት ሲያገለግሉ ቆይተዋል።

ዶ/ር አምባቸው የክልሉ ሕዝብ ከድህነቱ እንዲላቀቅና ፍትሐዊ ተጠቃሚነቱ እንዲረጋገጥ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያላቸው የተለያዩ የልማት ድርጅቶችን፣ ማለትም የአማራ መልሶ ማቋቋም ልማት ድርጅት፣ የቤቶች ልማት፣ የአማራ ቧንቧና ፕላስቲክ ፋብሪካን በቦርድ ሰብሳቢነት አመራር ሰጥተዋል። በፌደራል ተቋማት የኢትዮጵያ ምድር ባቡር፣ ኢትዮ ቴሌኮምና መብራት ኃይልን በቦርድ አባልነት በተጨማሪም የጎንደር ዩንቨርስቲና የደብረታቦር ብረታ ብረት ኢንጅነሪንግ ኮርፖሬሽንን ደግሞ በቦርድ ሰብሳቢነት መርተዋል።

በተለይም አሁን በምንገኝበት የለውጥ ምዕራፍ በብረታ ብረትና በኢንጅነሪንግ ውስጥ ▶



▶የነበሩ ብልሹ አሰራሮች እንዲስተካከሉና እንዲወገዱ ከሌሎች የትግል ጓዶቻቸው ጋር ሆነው ከፍተኛ ቁርጠኝነትን ተላብሰው አገራዊ ግዴታቸውን በብቃት ተወጥተዋል፡፡ ዶ/ር አምባቸው በአሁኑ ወቅት በአገሪቱ እየተካሄደ ባለው የለውጥ እንቅስቃሴ ከትግል ጓዶቻቸውና ከሕዝቡ ጋር በመሆን የአገራቸውንና የአማራ ሕዝቦች እኩል ፍትሃዊ ተጠቃሚነት እንዲረ ጋገጥ፣ የዜጎች ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብት እንዲከበር የታገሉ የሕዝብ ልጅ ናቸው፡፡ ዶ/ር አምባቸው መኮንን ቆራጥ የአማራ ሕዝብ ምልክትም ነበሩ ማለት ይቻላል፡፡

ባለፉት ዓመታት በገጠሙን የፖለቲካ ብልሽቶች ምክንያት ያጋጠሙ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች እንዲታረሙ፣ በፅናትና በከፍተኛ ሕዝባዊነት ስሜት ከትግል አጋሮቻቸው ጋር በመሆን ጀነራል አሳምነው ፅጌና ጀነራል ተፈራ ማሞ የመሳሰሉት የነጻነት ታጋዮች ከእስር እንዲፈቱ ትልቅ አስተዋፅኦ አበርክተዋል፡፡ ዶ/ር አምባቸው መኮንን ያለምንም ልዩነት የሰውን ልጆች እኩል የሚወዱ፣ አገራቸውን ሕዝባቸውን ከራሳቸው በላይ የሚወዱና የሚያስቀድሙ፣ ሁሉንም የሰው ዘሮች በወንድምና በእህትነት የሚመለከቱ፣ ለዛ ባለው አንደበታቸው "እህት ዓለም" " ወንድም ዓለም" በሚሉ ሰዎችን የሚገለጹ ሰው አፍቃሪ ናቸው፡፡

ከቤተሰባቸው ይልቅ ሕዝባቸውንና አገራቸውን የሚያስቀድሙ፣ ንፁህ ልቦና ያላቸው፣ ሕዝብንና አገርን በሙሉ ታማኝነት፣ በአገልጋይነት፣ በሀቀኝነትና ላመኑበት ነገር ሁሉ የግንባር ስጋ ሆነው ሲሰሩ የኖሩ ታላቅ ሰው ናቸው፡፡ ዶ/ር አምባቸው መኮንን ውሸታምነትን የሚፀየፉ፣ የተሟላ ስብዕና ባለቤት ነበሩ፡፡ በተልዕኳቸው በተሰማሩባቸው ሁሉም ቦታዎች ለጓዶቻቸው አርአያ መሆን የቻሉ፣ የእውነት ታጋይና አመራር ነበሩ፡፡ ዶ/ር አምባቸው መኮንን ማህበራዊ ሕይወታቸው የተሟላና የሰመረ ሲሆን፣ ትዳራቸውን አክባሪ፣ ለልጆቻቸው ታማኝ አባት፣ ታናሽ ታላቆቻቸውን የሚያከብሩ እርሳቸው የተገኙበት ቦታ ሁሉ በጨዋታ የሚደምቅ፣ ድሆችን የሚረዱ በስራ ባልደረቦቻቸውና ለቤተሰቦቻቸው ፍቅርን በመስጠት ተወዳጅነትን ያተረፉ መሪ ነበሩ፡፡

የሕዝቡን የለውጥ ፍላጎትና ጥያቄ ተቀብለው ከነበሩበትና ሀላፊነት፣ የክልሉን ሕዝብ ለማገልገል ከየካቲት 29 ቀን 2011 .ም ጀምሮ በርዕሰ መስተዳርነት ተሰይመው፤ በክልሉና በአገሪቱ የተጀመረውን ለውጥ አጠናክረው ለማስቀጠል ያለምንም ዕረፍት ሌት ተቀን፣ እየሰሩ ባሉበት፤ የክልሉን መንግስት በኃይል በማስወገድ፣ ክልሉንና አገራችንን የከፋ አደጋ ላይ ለመጣል ታስቦ በተቀነባበረውና ተሞክሮ ሙሉ በሙሉ በከሸፈው የመፈንቅለ መንግስት ሴራ ቅዳሜ ሰኔ 15 ቀን 2011 ዓ.ም ከቀኑ 11 ሰዓት ገደማ በክልሉ መንግስት ርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤት፣ የርዕሰ መስተዳድሩ (በራሳቸው ቢሮ) መሰብሰቢያ አዳራሽ ውስጥ፣ ከክልሉ ከፍተኛ አመራሮች ጋር ስብሰባ ላይ በነበሩበት በተደረገ ጥቃት፤ ከሌሎች ሁለት የስራ ባልደረቦቻቸው ማለትም ከአቶ ምግባሩ ከበደና ከአቶ እዘዝ ዋሴ ጋር በጥይት ተመትተው በ48 ዓመታቸው ተሰውተዋል፡፡ ዶ/ር አምባቸው መኮንን ባለትዳር እና እንዲሁም የአራት ሴቶችና የአንድ ወንድ ልጅ አባት ነበሩ፡፡

# አቶ እዘዝ ዋሴ
# ከ1957-2011



አቶ እዘዝ ዋሴ መንግሥቱ ከአባታቸው አቶ ዋሴ መንግሥቱ ከእናታቸው ወ/ሮ የውብዳር በመጣ በ1957 ዓ.ም በቀድሞው ጎንደር ክ/ሀገር በደብረታቦር አውራጃ በአሁኑ ደቡብ ጎንደር ዞን እስቴ ወረዳ ያስኳ አበርጉት ቀበሌ ተወለዱ፡፡ አቶ እዘዝ ዋሴ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህ ርታቸውን በተወለዱበት አካባቢ የቅዳሜ ገበያ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በመካነ ኢየሱስ የ2ኛ ደረጃ ት/ቤት ተከታትለዋል፡፡ የመደበኛ ትምህርታቸውን ከማጠናቀቃቸው በፊት በወቅቱ የነበረውን የደርግ አገዛዝ በመቃወም ትምህርታቸውን አቋርጠው ከ1982 ዓ.ም ጀምሮ ከመሰል ጓደኞቻቸው ጋር ሕዝባዊ ትግሉ ዳር እንዲደርስ የበኩላቸውን አስተዋፅኦ አበርክተዋል፡፡

በሽግግሩ ወቅት በክፍለ ሕዝብነት በሰሩባቸው የእስቴ ወረዳ የተሰጣቸውን ሕዝባዊ ኃላፊነት በቁርጠኝነትና በታማኝነት በመወጣት በወቅቱ ደፍርሶ የነበረውን የአከባቢ ሰላም እንዲረጋጋ በማድረግ ከፍተኛ ሚና ተጫውተዋል፡፤ የአገራችን ሰላም ተረጋግጦ፣ መደበኛውን ስራ መስራት ሲጀመር ቀደም ሲል አቋርጠውት የነበረውን የመደበኛ ትምህርት በመቀጠል እስከ ማስትሬት ዲግሪ ድረስ ትምህርታቸውን ተከታትለዋል፡፡

አቶ እዘዝ ዋሴ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን በቢዝነስ ማኔጅመንት የማስተርስ ዲግሪያቸውን ከባህርዳር ዩኒቨርስቲ በቢዝነስ አድሚኒስትሬሽን ተመርቀዋል፡፡ በደቡብ ጎንደር ዞን አስተዳደር እስቴ ወረዳ በልዩ ልዩ የስራ ቦታዎች ሲያገለግሉ ቆይተው በነበራቸው የሕዝብ ተቀባይነት ከ1998 እስከ 2002 ዓ.ም ድረስ የእስቴ ወረዳን ሕዝብ ወክለው የኢፌድሪ የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤትን በአባልነት አገልግለዋል፡፡

የሚሰጣቸውን ተልዕኮ ለመፈፀም ቀን ከሌሊት የሚተጉ፤ ችግር ነው ብለው ያመኑበትን ነገር ያለ ምንም ፍርሃት ፊት ለፊት የሚታገሉ የቁርጥ ቀን የአማራ ሕዝብ ልጅ ነበሩ፡፡ በምርጫ 2002 ማግስት የክልሉን ሕዝብና አካባቢውን ለማገልገል በነበራቸው ቁርጠኝነት ከሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት አባልነት ተመልሰው ከ2003 እስከ 2004 ዓ.ም ድረስ የደቡብ ጎንደር አስተዳደር ዞን የብአዴን ጽ/ቤት ኃላፊ ከ2004 እስከ 2008 ዓ.ም ድረስ ደግሞ የደቡብ ጎንደር ዞን ዋና አስተዳዳሪ በመሆን አገልግለዋል፡፡

አቶ እዘዝ ዋሴ የደቡብ ጎንደር ዞንን በዋና አስተዳዳሪነት በመሩበት ወቅት የዞኑን ሕዝብ የሰላም የልማትና የዴሞክራሲ ተጠቃሚ ለማድረግ የሰሯቸውን አመርቂ ሥራዎች እንደተጠበቁ ሆነው በተለይም መላ የዞኑን ሕዝብ በማነቃነቅ የተራቆቱ አካባቢዎች እንዲያገግሙ በተፈጥሮ ሐብት ስራና በሌሎቹ ተቋማት አፈፃፀም ዞኑ የተሻለና ተሸላሚ እንዲሆን በማድረግ የራሳቸውን አሻራ ማሳረፍ ችለዋል፡፡ አቶ እዘዝ ደፋርና ጀግና ነበሩ፡፡ ታማኝ ታጋይም ነበሩ፡፡ አቶ እዘዝ ዋሴ ለዓላማቸው ጽኑ ታጋይ ነበሩ፡፡ የትግል ጓዶቻቸውን መቼም የማይረሱ ከወደቁበት ፈልገው የሚያነሱ የዓላማም ሰው ነበሩ፡፡ ለሚያምኑበት ዓላማም ሕይወታቸውን አሳልፈው የሰጡ ቆራጥ የሕዝብ ልጅ ነበሩ፡፡ ከ2008 ዓ.ም ጀምሮ በምዕራብና ማዕከላዊ ጎንደር አጋጥሞ የነበረውን የሰላም መደፍረስ ለማረጋጋት የሚወዷቸውን ቤተሰቦቻቸውን ጥለው ወደ አካባቢው በመሄድ ተልዕኳቸውን ከሥራ ባልደረባቸው አቶ ምግባሩ ከበደ ጋር በመሆን በብቃት የተወጡና በአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድም አክብሮት የተቸራቸው ታጋይ ነበሩ፡፡

አቶ እዘዝ ዋሴ በኢትዮጵያ አሁን ለታየው ለውጥ ከትግል ጓዶቻቸው ጋር በመሆን ፊትለፊት የሚሰማቸውን በግልፅ በአደባባይ የታገሉ ለውጡ መሬት እንዲነካ በየመኻሉ የሚያጋጥሙ ችግሮች መልክ እንዲይዙ በልበ ሙልነት ከትግል ጓዶቻቸው ጋር በመሆን ታግለዋል፡፡

ከ2009 ዓ.ም እስከ 2011 ዓ.ም ድረስ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የአስተዳደርና የፀጥታ ቢሮ ኃላፊ ሆነው እንዲያገለግሉ ኃላፊነት ተሰጥቷቸው ኃላፊነታቸውንም በታማኝነት በቆራጥነት በጀግንነት መርተዋል፡፡ መሪ ድርጅቱ አዴፓ ታሪካዊ የሆነውን 12ኛ ድርጅታዊ ጉባኤ ካካሄደ በኋላ የአዴፓን ማዕከላዊ ጽ/ቤት በጠንካራና በአማራ የአማራ ልጆች እንዲመራ በማሰብ በጥቅምት 2011 ዓ.ም ጀምሮ መስዋዕትን እስከከፈሉበት ጊዜ ድረስ የአማራ ዴሞክራሲዊ ፓርቲ የአደረጃጀት ዘርፍ ኃላፊና የርዕሰ መስተዳድሩ የአደረጃጀት አማካሪ በመሆን በተለመደው ሕዝባዊ ባህርያቸው ለአማራ ሕዝቦችና ለኢትዮጵያ ሕዝቦች ጥቅም መረጋገጥ ታግለዋል፡፡

አቶ እዘዝ ዋሴ በስራ እጅግ ታታሪ ከመሆናቸው የተነሳ ሙሉ ጊዜያቸውን በስራ የሚያውሉ ጧት ለስራ ሲወጡ የተኙ ልጆቻቸውን ማታ አምሽተው ከስራ ሲመለሱም ተኝተው ስለሚያገኟቸው ለልጆቻቸው እንኳን በቅጡ ጊዜ ሳይሰሰጡ መስዋዕትነት የከፈሉ አመራ ነበሩ፡፡ አቶ እዘዝ ዋሴ በአዴፓ ማዕከላዊ ጽ/ቤት ተመድበው በክልሉና በአገሪቱ የተጀመረውን ለማስቀጠል ያለምንም ዕረፍት ሌት ተቀን እየሰሩ ባሉበት የክልሉን መንግስት በኃይል በማስወገድ ክልሉንና አገራችን የከፋ አደጋ ላይ ለመጣል ታስቦ በተቀነባበረውና ተሞክሮ ሙሉ በሙሉ በከሸፈው የመፈንቅለ መንግስት ሴራ ቅዳሜ ሰኔ 15 ቀን 2011 ዓ.ም ከቀኑ 11 ሰዓት ገደማ በክልሉ መንግስት ርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤት የርዕሰ መስተዳድሩ መሰብሰቢያ አዳራሽ ውስጥ ከክልሉ ከፍተኛ አመራሮች ጋር ስብሰባ ላይ በነበሩበት በተደረገ ጥቃት፤ ከሌሎች ሁለት የስራ ባልደረቦቻቸው ከአቶ አምባቸው መኮንን እና አቶ ምግባሩ ከበደ ጋር በጥይት ተመትተው በ48 ዓመታቸው ተሰውተዋል፡፡ ዶ/ር አምባቸው መኮንን ባለትዳርና የአራት ሴቶችና የአንድ ወንድ ልጅ አባት ነበሩ፡፡ አቶ እዘዝ ዋሴ ባለትዳርና የሁለት ሴት ልጆችና የሁለት ወንድ ልጆች አባት ነበሩ፡፡



ልዩ ዕትም

# አቶ ምግባሩ ከበደ ከ1966-2011

አቶ ምግባሩ ከበደ ከአባታቸው ከአቶ ከበደ እውነቱ፣ ከእናታቸው ወ/ሮ የሺ ውቢቱ ሐምሌ 23 ቀን 1966 ዓ.ም በቀድሞው ጎንደር ክ/ሀገር በደብረታቦር አውራጃ በአሁኑ የደቡብ ጎንደር አስተዳደር ዞን ገርባ ወረዳ ልዩ ስሙ "ወፍ አርግፍ"፣ ታምሬ ልደታ ቀበሌ ተወለዱ፡፡

ዕድሜያአቸው ለትምህርት ሲደርስ "በወፍ አርግፍ" አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ የመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በአንበሳሜ መለስተኛ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት፣ የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በሐይቅ ከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት ተምረዋል፡ ፡ አቶ ምግባሩ ከበደ በጣም ፈጣንና ጎበዝ ተማሪ በመሆናቸው የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸውን በጣም ባጠረ ጊዜ (ደብል እየመቱ) ማጠናቀቅ የቻሉ ሰው ነበሩ፡፡

አቶ ምግባሩ ከበደ የከፍተኛ ትምህርታቸውን በባህርዳር ዩንቨርስቲ በሕግ የመጀመሪያ ዲግሪ ያገኙ ሲሆን፣ የማስተርስ ዲግሪያቸውን በተመሳሳይ ከባህርዳር ዩንቨርስቲ በሕግ የትምህርት ዘርፍ ተመርቀዋል፡፡ አቶ ምግባሩ ከበደ፣ በትምህርት ክትትላቸው ብቃት ያላቸውና ብልህ፣ ሕግ አዋቂ ሰው ነበሩ፡፡

የከፍተኛ ትምህርታቸውን እንዳጠናቀቁ በተማሩበት የሕግ ሙያ በምዕራብ ጎጃም ዞን የገላዳባትና ሰቀላ ወረዳዎች በዓቃቤ ሕግነት ሕዝባቸውን በብቃት፣ በቅንነትና በታማኝነት አገልግለዋል፡፡ አቶ ምግባሩ ከበደ በወረዳ ደረጃ በዓቃቤ ሕግነታቸው ባሳዩት ብቃትና ሙያዊ ችሎታ የሙያ ዕድገት አግኝተው፣ የምስራቅ ጎጃም ዞን ፍትህ መምሪያ ዓቃቤ ሕግ በመሆን በተመሳሳይ መልኩ ሙያዊ ኃላፊነታቸውን በብቃት ተወጥተዋል፡፡ ሕዝባቸውን በቅንነትም በታማኝነትም አገልግለዋል፡፡

አቶ ምግባሩ ከበደ በምዕራብ ጎጃምና ምስራቅ ዞኖች በሕግ ባለሙያነት ካገለገሉ በኂላ፣ በፖለቲካ ብቃታቸውም "አንቱ" የተባሉ በመሆናቸው የወቅቱ የክልሉ መሪ ፓርቲ የቀድሞው ብአዴን (የአሁኑ አዴፓ) የምስራቅ ጎጃም ዞን የአደረጃጀት ዘርፍ ኃላፊ ሆነው እንዲሰሩ በመመደባቸው፣ ከ1998 ዓ.ም ጀምሮ የዞኑ ሕዝብ ለመብቱና ለጥቅሙ መረጋገጥ ተደራጅቶ እንዲታገል፣ የአካባቢው ሰላም እንዲረጋገጥ፣ የክልሉ ልማት እንዲፋጠን ብቃት ያለው አመራር በመስጠት ትልቅ ሚና ተጫውተዋል፡፡

በፖለቲካው መስክም ከጊዜ ወደ ጊዜ ብቃታቸውን እያሳደጉና የሕዝብን ዕምነት እያተረፉ በመምጣታቸው፤ ከ1999 ዓ.ም እስከ 2000 ዓ.ም ድረስ የምስራቅ ጎጃም ዞን የአቅም ግንባታ መምሪያ ኃላፊ፣ ከ2000 ዓ.ም እስከ



2002 ዓ.ም ድረስ የደብረ ማርቆስ አስተዳደር ከንቲባ፣ ከ2003 ዓ.ም እስከ 2008 ዓ.ም የምስራቅ ጎጃም ዞን ዋና አስተዳዳሪ በመሆን ሕዝባቸውን በታማኝነት፣ በቅንነትና በሕዝብ አገልጋይነት መንፈስ መስረታት የቻሉ ጓድ ነበሩ፡፡

አቶ ምግባሩ ከበደ የምስራቅ ጎጃም ዞን ሆነው አመራር በሰጡበት ወቅት የዞኑን ሕዝብ ሁለንተናዊ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ፣ ሌት ተቀን አመራር የሰሩ ከመሆኑም በላይ በተለይም የዞኑን ልማት ለማፋጠን ባላቸው ፍላጎት፤ "የመንቆረር ኮንስትራክሽን ድርጅት" በአጭር ጊዜ ውስጥ የተሟላ ድጋፍ አግኝቶ፣ የዞኑን ልማት ማፋጠን እንዲችል ግንባር ቀደም አመራር ያረጋገጡ ሰው ነበሩ፡፡

በተመሳሳይ መልኩ የጎጃም ሕዝብ ቱባ ባህልና ጥበብ እንዲለማ፣ ለትውልድም እንዲሻገር ከልብ በማሰብ፣ የባህል ቡድኖች እንዲቋቋሙ የጎጃም ባህል ማዕከል በግንባታ ደረጃ፣ በሀሳብ ደረጃ መሬት እንዲነካ በማድረግ ፣ እንዲሁም በርካታ ስራዎችን የሰሩ ጓድ ነበሩ፡፡

አቶ ምግባሩ ከበደ ከ2008 ዓ.ም ጀምሮ በአገራችንና በክልሉ አስተማማኝ ዕድገትና ለውጥ ከመታሰቡ ጋር ከምስራቅ ጎጃም ዞን ዋና አስተዳዳሪነት በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የርዕሰ መስተዳድር አማካሪ ሆነው አገለግለዋል፡፡ በዚህ ወቅት በክልሉ የሰሜን ጎንደር ዞን የነበረውን አለመረጋጋት ወደ መደበኛ ሁኔታ ለመመለስ፣ ከጓዶቻቸው አቶ እዘዝ ዋሴ ጋር የተሰጣቸውን ተልዕኮ በቦታው ተገኝተው ከፍተኛ የሆነ መስዋዕትነት በመክፈል ዞኑ የተረጋጋ እንዲሆን ትልቅ ሚና ተጫውተዋል፡፡

አዴፓ የ12ኛ ድርጅታዊ ጉባኤውን ተከትሎ የተለያዩ ታሪካዊ ውሳኔዎችን በማሳለፍ ካጠናቀቀ በኂላ፣ የድርጅት ጽ/ቤቱን ብቃት ባላቸው ቁርጠኛ አመራሮች ለማደራጀት በነበረው ቁርጠኝነት አቶ ምግባሩ ከበደ በም/ርዕሰ መስተዳድር ማዕረግ የርዕሰ መስተዳድሩ የሕዝብ ግንኙነትና የአደረጃጀት አማካሪ፣ እንዲሁም የለውጥ መሪው አዴፓ፣ ማዕከላዊ ኮሚቴ ጸ/ቤት ኃላፊ በመሆን የሽግግር ወቅት የሚመጥን ብቃት ያለው አመራር ሰጥተዋል፡፡

ከየካቲት 29 ቀን 2011 ዓ/ም ጀምሮ በምክትል ርዕሰ መስተዳድር ማዕረግ የአማራ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ በመሆን መስዋዕት እስከሆኑበት ድረስ የፍትህ ተቋሙን ሪፎርም በመምራት መሰረት ጥለዋል፡፡ አቶ ምግባሩ ከበደ በክልሉና በአገሪቱ እየተካሄደ ያለውን ለውጥ ከትግል ጓዶቻው ጋር ተሰልፈው ብቃት ያላቸው መሪ በመሆን፣ የሕዝብን ጥቅም አስቀድመው ለአማራ ሕዝቦችና ለኢትዮጵያ ሕዝቦች መብት መከበር በግንባር ቀደምትነት የታገሉ ጓድ ነበሩ፡፡

አቶ ምግባሩ ከበደ ለውጡ በሂደት የሚያጋጥመውን ውጣ ወረድ ቀድመው በመተንተንና የመሸጋገሪያ ስትራቴጂዎችን በመንደፍ፣ የፖሊሲ ሀሳቦችንና ፖለቲካዊ አቋሞችን ለሕዝብ በማድረስ፣ አሳማኝ መሞገቻዎችን በማቅረብ ብቃት ያለው አመራር ያረጋገጡ ጓድ ነበሩ፡፡

ፈጣን፣ አዳዲስ የለውጥ ሀሳቦችን የሚያመነጩ፣ መፍትሄ ሰጪና ችግር ፈቺ አዕምሮ ባለቤትም ነበሩ፡፡ አቶ ምግባሩ ከበደ የሕግ የበላይነት መከበር ፅኑ አቋም የነበራቸው፣ ከሰሜን ጎንደር ዞን አካባቢያቸው በተጨማሪ ከኦሮሞ ብሔረሰብ አስተዳርና ከሰሜን ሸዋ ዞን አጎራባች ወረዳዎች አካባቢ ተፈጥሮ የነበረው ግጭት ወደ መደበኛ ሁኔታው እንዲመለስ፣ ግጭቶች እንዳይባባሱና የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነቱ እንዲሻሻል ብቃት ያለውና ቁርጠኛ አመራር ሰጥተዋል፡፡

አቶ ምግባሩ ከበደ ላመኑበት አቋም ግንባራቸውን የሚሰጡ ፅኑ እና ደፋር ታጋይ ነበሩ፡፡ ሙያዊ ብቃታቸው ከፍ ያለ፣ ሙያተኛ፣ ጠንካራ ተደራዳሪ፣ ፖለቲከኛ፣ ትሁት ሰው አክባሪና ተግባቢ፣ የመልካም ስነ ምግባር ባለቤት፣ የከፍተኛ ትዕግስት ባለቤት፣ ሰዎችን በአለቃና በሰራተኛ ግንኙነት ሳይሆን ሁሉንም እንደ ጓደኛ የሚያዩ፣ በመግባባትም ፈጣንና ውጤታማ አመራር ነበሩ፡፡ በክልሉና በአገሪቱ የተጀመረውን ለውጥ አጠናክረው ለማስቀጠል ያለምንም ዕረፍት ሌት ተቀን እየሰሩ ባሉበት፤ የክልሉን መንግስት በኃይል በማስወገድ፣ ክልሉንና አገራችን የከፋ አደጋ ላይ ለመጣል ታስቦ በተቀነባበረውና ተሞክሮ ሙሉ በሙሉ በከሸፈው የመፈንቅለ መንግስት ሴራ፣ ቅዳሜ ሰኔ 15 ቀን 2011 ዓ.ም ከቀኑ 11 ሰዓት ገደማ በክልሉ መንግስት ርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤት፣ የርዕሰ መስተዳድሩ መሰብሰቢያ አዳራሽ ውስጥ ከክልሉ ከፍተኛ አመራሮች ጋር ስብሰባ ላይ በነበሩበት በተደረገ ጥቃት፤ ከሌሎች ሁለት የስራ ባልደረቦቻቸው ከአቶ አምባቸው መኮንንና ከአቶ እዘዝ ዋሴ ጋር በጥይት ተመትተው በ48 ዓመታቸው ተሰውተዋል፡፡ አቶ ምግባሩ ከበደ ባለትዳር፣ የሶስት ወንድና የሁለት ሴት ልጆች አባት ነበሩ፡፡

ልዩ ዕትም



# ሜ/ጀነራል ገዛኢ አበራ
# ከ1953-2011



ሜጀር ጀነራል ገዛኢ አበራ የተወለዱት ከአባታቸው ከቀኝ አዝማች አበራ ደስታ እና ከእናታቸው ከወይዘሮ ሙሉ አብርሃ በትግራይ ክልል በማዕከላዊ ዞን አክሱም ከተማ ጥር 1953 ዓ.ም ነው፡፡ እድሜአቸው ለትምህርት እንደደረሰ አክሱም አብረሃ ወአፅብሃ ትምህርት ቤት ከአንደኛ እስከ ስድስተኛ ክፍል እንዲሁም ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በአክሱም ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እየተማሩ በነበሩበት ወቅት ከነበረው አስከፊ የደርግ ስርዓት በትጥቅ ትግል በ1969 ዓ.ም ጥር ወር በሕወሓት ወደሚመራው የትጥቅ ትግል ተቀላቅለዋል፡፡

ጀነራል ገዛኢ ወታደራዊ ሥልጠናቸውን ካጠናቀቁ በኋላ ከ1969 ዓ.ም እስከ ግንቦት 1970 ዓ.ም በሕወሓት 30ኛ ሻምበል በተዋጊነትና በተለያዩ ሀላፊነቶች ግዳጃቸውን ፈፅመዋል፡፡

ከ1976 እስከ 1978 ዓ.ም የሰራዊት ግልጋሎት አደራጃጀት ሲፈጠር የህወሐት ሰራዊት ከተለመደው በደጀን ከመገልገል ወጥቶ ሰራዊቱ የራሱን ሎጅስቲክ ድጋፍ ሰጪ አካል ኖሮት እራሱን ችሎ ተልዕኮውን እንዲወጣ ለማስቻል ታስቦ ሲደራጅ የቅድመ ግንባር አገልግሎት ሰጪ አመራሮች ከተመደቡት መካከል ሜጀር ጀነራል ገዛኢ አበራ አንዱ ነበሩ፡፡ አዲስ አስተሳሰብና አመለካከትን መልክ በማስያዝና በመምራትም ቀዳሚ ከነበሩና ድሉን በብቃት ከተወጡ አመራሮች አንዱ ነበሩ፡፡

በዝግጅት ምዕራፍ ብቁ የሎጀስቲክ አቅም ዝግጅት በማድረግ በውጊያ ምዕራፍ የሰራዊቱን ብቃት ድጋፍ በመስጠት ከውጊያም በኋላ በውጊያም የጎደሉ ማቴሪያሎችን አሟልቶ ዳግም ለቀጣይ ግዳጅ የተሟላ የትራንስፖርት አቅም ባልነበረበት ፋታ በማይሰጡ ተከታታይ የውጊያ ጫናዎች ተቋቁመው ሰራዊቱን ደግፈው ለድል ለማብቃት በሚጠይቀው የአመራር ብቃት ኃላፊነታቸውን በሚገባ ተወጥተዋል፡፡

ከ1977 እስከ 1980 ዓ.ም ድረስ የሕወሓት ሰራዊት ይመራበት የነበረው የሰራዊት ግንባታና የውጊያዎች አቅጣጫዎች ወታደራዊ ሳይንስና ጥበብ በሚቀመርበት ወቅት ሜጀር ጀነራል ገዛኢ ከሌሎች የክፍሉ አባላት ጋር በመሆን ከፍተኛ ሚና ነበራቸው፡፡

ይህ ወታደራዊና የሳይንስ ቀመር የትጥቅ ትግሉን ለድል ያበቃ የአስተሳሰብ ቀመር ነው፡፡ እነዚህ ድምር የሎጀስቲክስ ድጋፍ አሰጣጥ አካሄዶች ከየካቲት 1980 ዓ.ም እስከ የካቲት 1981 ዓ.ም ድረስ በተደረጉ ተከታታይ ውጊያዎች በትግራይ የነበረውን የደርግ ሰራዊት ጠራርጎ በማስወጣት መላው ትግራይን ነፃ እንዲወጣ ያስቻለ ነበር፡፡

ከግንቦት 1981 ዓ.ም እስከ 1983 ዓ.ም የውጊያ ቀጠናዎች ሰፍተዋል በማለት የኢህአዴግ ሰራዊት ከሀይቅ ጀምሮ እስከ ሰሜን ሸዋ ፣ ከደቡብ ወሎ እስከ ደቡብ ጎንደር የተዘረጋበትና የተሟላ ድጋፍ ያገኝበት ከነበረው ነባር ደጀን የራቀበት፣ አዲስ አካባቢ የገባበት፣ የውጊያ ድጋፍ ፍላጎት በአይነትና በመጠን የጨመረበት፣ በተወሳሰበ ሁኔታ ውስጥ በቂ የሎጅስቲክ ድጋፍ በመስጠት ሰራዊቱ ተልዕኮውን በድል እንዲወጣ ያስቻለ ብቁ አመራር በመስጠት ሜጀር ጀነራል ገዛኢ ከፍተኛ ሚና ነበራቸው፡፡

ከ1983 ዓ.ም እስከ 1985 ዓ.ም ድረስ ከደርግ ስርዓት ውድቀት በኋላ የሀገር መከላከያ ሰራዊት በአዲስ መልክ በተደራጀበት ወቅት በሀገር መከላከያ ሚኒስቴር በሎጀስቲክስ ዋና መምሪያ የስንቅና ንብረት ዋና ኃላፊ በመሆን በሙያቸው የተሰጣቸውን ተልዕኮ በብቃት በመወጣት በአዲስ መልክ በማደራጀትና በመምራት የአመራር ሚናቸው ከፍተኛ ነበር፡፡

ከ1985ዓ.ም እስከ 2005 ዓ.ም የሀገር መከላከያ የሎጀስቲክ መምሪያ ዋና ኃላፊ በመሆን የኢፌዴሪ መከላከያ ሰራዊት ሎጀስቲክ በአዲስ ሲደራጅ ዘመናዊ ሎጀስቲክ የሚጠይቀውን ሳይንስ የሚመራበት የፖሊሲ ሀሳቦች፣ ደንቦችና መመሪያዎች አዳዲስ አሰራሮችን በማውጣት ወቅቱ የሚጠይቀውን አደረጃጀት በመፍጠርና በየደረጃው የነበሩ የሎጀስቲክ አመራሮችን በስልጠና አዳዲስ ሀሳቦችን እንዲይዙ በማብቃት ወቅቱ የሚጠይቀውን ዘመናዊ የሎጀስቲክ አቅም እንዲገነባ ግንባር ቀደም ሚና ተጫውተዋል፡፡

# “ጀግኖቹ አይሞቱም ሕያው ናቸው”

***የጀነራል ገዛኢ አበራ ልጅ***

ክብርት ሳህለ ወርቅ ዘውዴ፣ ክቡር ዶ/ር ዐቢይ አሕመድ፣ ክቡር የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት አፈ ጉባኤ አቶ ታገሰ ጫፎ፣ የተከበራችሁ የክልል ርዕሰ መስተዳድሮችና የመንግስት ኃላፊዎች፣ የሀይማኖት አባቶችና የአገር ሽማግሌዎች፣ የተከበራችሁ የሀዘናችን ተካፋዮች፡፡

እጅግ አስደንጋጭ ልብ ሰባሪ የሆነውን፣ የቤተሰባችን ሁሉ ነገር የሆነው ሜ/ጀነራል ገዛኢ አበራን የሀዘን ፕሮግራም ለመካፈል እዚህ ስለተገኛችሁ፣ በመላው ቤተሰባችን ስም አመሰግናለሁ፡፡ ተግባቢ፣ ትጉ፣ ዘመን ተሻጋሪ የሆኑ ምክሮቹ በቃላት ተነግረው የማይገለፅ አባት ሲሆን፣ ለውድ ባለቤቱ ፍፁም የልብና የፍቅር ሰው ነበር፡፡

በግለ ስብዕናው ሰውን አክባሪ፣ ቁጡ፣ ታጋሽ፣ ብልህ፣ አስተዋይ፣ አርቆ አሳቢ፣ አንደበተ ርቱዕ፣ ጨዋነትን በምግባር የሚያሳይ፣ እግዚአብሔርን የሚፈራ ነበር፡፡ ገዛኢ ታታሪና ጠንካራ ሠራተኛ፣ አዲስ ዕውቀትን ለመጨመር ሁልጊዜ የሚያነብ፣ የአገሩና የሕዝቡ ሁኔታ እረፍት የሚያሳጣው ሰው ነበር፡፡

ጡረታ ከወጣም በኋላ ሕይወቱ እስከሚያልፍ እስከተሰዋበት ድረስ ደከመኝ፣ ሰለቸኝ ሳይል በአገርና በሕዝብ ጉዳይ የተጠመደ አባት ነበር፡፡ ገዛኢ ለእኛ ለልጆቹ የሁልጊዜ ምክሩ፣ እኔ የማወርሳችሁ ትምህርትና እውቀት ብቻ ነው በማለት በትምህርታችን ላይ ከፍተኛ ትኩረት እንድናደርግ፣ ምንም ዓይነት የልጅነት ባህሪይ ሳናሳይ የከፍተኛ ትምህርት እንድንከታተል ያደረገ ጀግና አባት ነው፡፡ ለወደፊት ሕይወታችን ሥርዓት እንዲኖረን ከሰው በታችም ሆነ ከሰው በላይ መሆን የለባችሁም እያለ ይመክረን ነበር፡፡

ገዛኢ የፍቅር ሰው ነበር፤ እሱ ባሳየን ፍቅር ሁላችንም በከፍተኛ ምግባር እንድንተሳሰር ያደረገ ልዩ አባታችን ነበር፡፡ ገዛኢ ለቤተሰቡ ምንም ያጎደለው ነገር የለም የሚባል ሰው ነው፡፡ ገዛኢ በሕይወት እያለህ በሰጠኸን ምክር እየኖርን ስለሆነ አናሳፍርህም፡፡ አሁንም በኋላም፣ ወደፊትም አናሳፍርህም፡፡ ቃላችንም፣ ቃልህም ሕያው ይሆናል፡፡ የምክርና የሕይወት ፍልስፍናህን በመከተል ያስጀመርከንን የሕይወት፣ የተስፋ፣ ጉዞ በእግዚአብሔር ብርታት እንቀጥላለን፡፡ በጣም እንወድሃለን፡፡

ቀጥሎ የሕዝብ አገልጋይና ትሁት የሆነው፣ በጀግንነት ለተሰዋው በአባታችንና በወንድማችን ጠቅላይ ኤታማዦር ሹም ጀነራል ሰዓረ መኮንን ሞት የተሰማንን ጥልቅ ሀዘን እየገለፅን ለቤተሰቦቻችን ልባዊ መፅናናትን እንመኛለን፡፡ በመጨረሻም በሀዘናችን ጊዜ ከጎናችሁ ላፅናናችሁን ለኢትዮጵያ መንግስት፣ ለሀይማኖት አባቶች፣ ለትግል ጓዶች፣ ለኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት አባላትና ለኢትዮጵያ ሕዝብ በሙሉ ልባዊ ምስጋናችንን እናቀርባለን፡፡ እነሱ ጀግኖች ናቸው፣ ጀግኖቹ አይሞቱም ሕያው ናቸው፡፡ ቃላቸውን እንጠብቃለን፡፡ ዘላለማዊ ክብር ለተሰው ሰማዕታት፡፡





# ጀነራል ሰዓረ መኮንን ከ1954-2011



ጀነራል ሰዓረ መኮ ንን፣ ከአባ ታቸው ከአስር አለቃ መኮ ንን ይመርና ከእናቸው ከወይዘሮ ሕይወት ይህ ደጎ፣ በትግራይ ክልል በሰሜን ምዕራብ ዞን "አስ ገደ ጽምብላ" ወረዳ፣ በእን ዳባጉና ወረዳ በ1954 ዓ.ም ነው የተወለዱት፡፡ እድሜ ያአቸው ለትምህርት ሲደርስም በተወለዱበት ወረዳ እንዳአባጉና አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከአንደኛ እስከ ስድስተኛ ክፍል፣እንዲሁም ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ሽሬ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መከታተላቸውን የሕይወት ታሪካቸው ያትታል፡፡ በዚህ ወቅትም የነበረውን የደርግ አስከፊ ስርዓት ለመገርሰስ በሕወሓት የሚመራው የትጥቅ ትግል ስለነበር፣ በወ ጣትነት ዕድሜያቸው በ1969 ዓ.ም የትጥቅ ትግሉን ተቀላቅለው ስልጠና መውሰዳቸው ይጠቀሳል፡፡

ከ1969 ዓ.ም እስከ ታህሳስ 1971 ዓ.ም በሕወሓት 91ኛ እና 73ኛ የሚባሉ ሻምበሎችን በተራ ተዋጊነትና በጓድ አመራርነት ተሳትፈዋል፡፡ በተለይም በ1970 ዓ.ም ደርግ ባካሄደው የሰሜን ዘመቻ፣ በተለምዶ 3ኛው ዘመቻ ተብሎ የሚጠራው ፀረ ደርግ ዘመቻን በመመከት በጀግንነት ተዋግተዋል፡፡ ከታህሳስ 1971 ዓ.ም እስከ ታህሳስ 1972 ዓ.ም በሕወሓት የተደራጁ፣ የታጠቁ ፕሮፓጋንዳ አህዱ በተለምዶ "ክብሪት" በሚባል የጋንታ አመራር በመሆንም የተሰጣቸውን ግዳጅ በብቃት ተወጥተዋል፡፡ ከ1974 ዓ.ም እስከ 1975 ዓ.ም በብርጌድ 43 ውስጥ የሻለቃ አመራር በመሆን፣ የደርግ ሰራዊት የሻዕቢያ ሰራዊትን ለመደምሰስ ባካሄደው የቀይ ኮከብ ዘመቻን ለመከላከልና ለመቀልበስ እጅግ አኩሪና አስደናቂ ጀግንነት ከፈፀሙ ታጋዮች ውስጥ ግንባር ቀደሙ እንደሆኑ ይነገርላቸዋል፡፡

በ1978 ዓ.ም የብርጌድ 77 ምክትል ብርጌድ አዛዥ በመሆን በራያ አካባቢ ደርግ ያካሄዳቸውን የነበሩ ተደጋጋሚ ዘመቻዎችን በመመከትና በልዩ ስምሪቶች፣ ማለትም የታጋዮችን ልዩ ጽናትን የፈተነ የሰርዶ ልዩ ስምሪትን መርተዋል፡፡ በጥር 30 ቀን 1978 ዓ.ም በመቐለ ከተማ የደርግ ወህኒ ቤት፣ አንድ ሺ 300 እስረኞችን ነፃ ባወጣው የአግአዚ ኦፕሬሽን የብርጌድ ምክትል አዛዥ በመሆን፣ ግዳጃቸውን በጀግንነት የፈፀሙ አርበኛ መሆናቸውን ታሪክ ከመዘገበላቸው የትግል ታሪካቸው መካከል ይጠቀሳል፡፡

የአምባአላጌ ውጊያን በብቃት በመምራት ግዳጃቸውን ለድል ያበቁ ታጋይ እንደነበሩም ተጠቅሷል፡፡ ከመስከረም 1981 ዓ.ም ጀምሮ የደርግ ስርዓት እስኪወድቅ ድረስ የአውሮራ ክፍለ ጦር አዛዥ በመሆንም፤ የደርግ ሰራዊት እንዲገረሰስ ከፍተኛ አስተዋፅኦ በማድረግ ታሪካዊ ኃላፊነታቸውን መወጣታቸውን ለማወቅ ተችሏል፡፡

ከደርግ ስርዓት ውድቀት በኂላ በኢህአዴግ የሰራዊት አደረጃጀት መሰረት የምስራቅ ዕዝ ዘመቻ ኃላፊ በመሆን፣ እንዲሁም ከየካቲት 1987 ዓ.ም ጀምሮ በኢፌድሪ የአገር አቀፍ የሰራዊት ምስረታ፣ የምስራቅ ዕዝ ምክትል አዛዥ በመሆን አገራዊ ተልዕኳቸውን በብቃት ተወጥተዋል፡፡

ታሪካቸው እንደሚያስረዳው፤ በግንቦት ወር 1990 ዓ.ም በኢትዮ - ኤርትራ ጦርነት ወቅት የቡሬ ግንባር አዛዥ በመሆን የኢትዮጵያን ዳር ድንበር አስክብረዋል፡፡ በየካቲት 1991 ዓ.ም ባድሜን ከኤርትራ ሰራዊት ነፃ ባወጣ ዘመቻ "ፀሃይ ግባት" የባድሜ ግንባር ግራ ክንፍ መሪ በመሆን ዘመቻው እስኪጠናቀቅ አኩሪ ገድል ፈጽመዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በሌሎች ዕዞች ሀላፊ በመሆን አገራቸውን በታማኝነትና በቅንነት አገልግለዋል፡፡

ያካበቱትን ወታደራዊ ግንባታ ያገኙትን ልምድ ተጠቅመው ሰራዊቱን በወታደራዊ ሳይንስና ጥበብ የተካነ እንዲሆን፣ የትምህርትና ስልጠና ተቋማት ሚናቸውን ይበልጥ እንዲጫወቱ ለማድረግ፣ ከ2006 ዓ.ም እስከ 2010 ዓ.ም ድረስ የመከላከያ ትምህርትና ስልጠና ዋና መምሪያ ሀላፊ በመሆን አገልግለዋል፡፡ ተቋማቱ በሰራዊት ግንባታ ሂደት ትልቅ አስተዋፅኦ እንዲያበረክቱ በብቃት የመሩ መሆናቸውም ተጠቁሟል፡፡

በነበራቸው ብቃት ምክንያትም ከመጋቢት 2010 ዓ.ም እስከ ግንቦት 2010 ዓ.ም የጦር ሀይሎች ምክትል ጠቅላይ ኤታማዦር ሹም በመሆን አገልግለዋል፡፡ ከግንቦት 2010 ዓ.ም እስከ መስዋዕት ቀናቸው ድረስ ደግሞ ጠቅላይ ኤታማዦር ሹም ሆነው አገልግለዋል፡ ፡ በእዚህ ወቅት በአገሪቱ አንዳንድ ከፍሎች የነበሩ አለመረጋጋቶችና የህዝብ መፈናቀሎች የነበሩበት ወቅት ሲሆን፤ ህዝቡ በሰላም ወጥቶ እንዲገባ በማድረግ ሂደት የመሪነት ሚናቸውን ተወጥተዋል፡፡

የለውጥ ክስተቱን ተከትሎ በርካታ ውስብስብ ሁኔታዎች ተፈጥረዋል፡፡ እርሳቸው የመከላከያ ጠቅላይ ኤታማዦር ሹም የመሆን መሪነት ደግሞ ኃላፊነታቸው ድርብ ያደርገዋል፡ ፡ የውስጥ የፀጥታ ሁኔታን ማስተካከልና ተቋማዊ ሪፎርም ሥራ ነበረባቸው፡፡ ይህንን በማቀድ በመምራት የመሪነት ሚናቸውንም ተወጥተዋል፡፡ በተፈለገው የሪፎርም ሥራ በውጤታማነት እንዲሄድ በማድረግም በብዙ ጫናና ተግዳሮት ውስጥ በማለፍ ለውጡ ለኢትዮጵያ ህዝብ ያለውን ፋይዳ በማስቀደም የበኩላቸውን ጉልህ ሚና የተጫወቱ ዕንቁ መሪ እንደነበሩም ታሪካቸው ያትታል፡፡

## "ጄነራል ሰዓረ ስለሞተ አገር ይፈርሳል ማለት አይደለም"

*የጄነራል ሰዓረ መኮንን ልጅ*

በመጀመሪያ ለእኛና ለጄነራል ገዛኢ ቤተሰቦች የኢፌዴሪ መንግስት ይሄንን ዕድል ስላዘጋጀልን ልባዊ ምስጋናችንን እናቀርባለን፡፡ የተሰዉ ቤተሰቦቻችን አክብሮ ለመጣው ለኢትዮጵያ ሕዝብ ክብር ምስጋናዬን ልገልፅ እወዳለሁ፡፡

አባቴ ጄነራል ሰዓረ መኮንን በአንድነት፣ በመቻቻል፣ አብሮ በመስራት የሚያምን ፍፁም ኢትዮጵያዊ ነበረ፡፡ ጄነራል ብርሃኑ ጁላ ቀደም ሲል እንደገለፁት ለእሱ ፈፅሞ ይሄ ዓይነት ነገር አይገባውም፡፡ ትልቅ ኢትዮጵያዊ ነበር፡፡

ጄነራል ሰዓረ ስለሞተ አገር ይፈርሳል ማለት አይደለም፤ አይፈርስምም፡፡ እኛ ጠንክረን ከሰራንና ከለውጡ ጎን ከቆምን ኢትዮጵያን አንድ እናደርጋታለን፡፡ ሕልሙም ዕውን ይሆናል፡፡ ሁላችሁንም ከልብ ኣመሰግናለሁ፡፡



# “ጥፋቱ እንዳይደገም የሕገ ወጥ ቢሯችንን ሁሉ እንዘጋለን”

## ጠ/ሚ/ር ዐቢይ አሕመድ



በቅድሚያ ከሁሉም በፊት በባህርዳር እና በአዲስ አበባ በሀገራችን ከፍተኛ የጦርና የሲቪል አመራሮች ላይ በተፈፀመው ሕገ ወጥና ዘግናኝ ፋሽስታዊ ግድያ የተሰማኝን ጥልቅ እና ልባዊ ኀዘን በራሴና በኢፌድሪ መንግሥት ስም እየገለፅኩ፤ ለሟቾች መንግስተ ሰማያትን፣ ለቤተሰቦች እና ለወዳጅ ዘመድ መጽናናትን፣ ለመላው የትግል ጓዶችና ለሥራ ባልደረቦች ደግሞ ብርታትን እመኛለሁ።

ታላቂቱን ሀገር ማሳነስ፣ የከበረውን ሕዝብ ማዋረድ፣ ለግስጋሴያችን ልጓም፣ ለመንገዳችን እንቅፋት ማኖር ሙያ የሚመስላቸው እዚህም እዚያም አሉ። ከዴሞክራሲ ሕዝብ ያተርፋል፤ እነርሱ ግን ይከስራሉ። ከሥልጣኔ ሕዝብ ይጠቀማል፤ እነርሱ ግን ይጎዳሉ። ከኅብረ ብሔራዊነት ሀገር ይበለጽጋል፤ እነርሱ ግን ይደኸያሉ። በፍቅርና በይቅርታ ኢትዮጵያ ትታከማለች፣ እነርሱ ግን ይታመማሉ። ይህ ነው የጠላቶቻችን ትልቁ መለያቸው።

ሐሳቡን ማሸነፍ ሲያቅታቸው፣ አሳቢን ለማጥፋት ተነሱ። አእምሮ ሲጎድላቸው ባለ አእምሮውን ለማጨናገፍ ቆረጡ። ጥበብ ሲሰፋባቸው ጠቢባኑን ለማስወገድ ፈጠኑ። ሀገር ወደ ዘመነ አብሮነት ስትጓዝ እነርሱ ተቃራኒውን መረጡ። በፈጣሪም ሆነ በሰው ዘንድ የተጠላውን የጥፋትን መንገድ ተከተሉ።

የተከበራችሁ የኢትዮጵያ ሕዝቦች፡-

ሀገር በተስፋና በደስታ ዘመናት ብቻ ሳይሆን በመከራና በችግር ዘመናትም ውስጥ እንደምታልፍ ከታሪክ ብቻ ሳይሆን ከመኖርም የምንረዳው ሐቅ ነው። ምንም እንኳ ሀሳበ ስንኩላን ሲነገራቸው ባይሰሙም፤ ሲመክሩ ባያደምጡም፤ ምሕረትና ይቅርታ ባይገባቸውም፣ የሀገራችን ጠላቶች ደግመው ደጋግመው መገንዘብ የሚኖርባቸው አንድ ዘለዓለማዊ እውነት አለ።ሀገራችን አእላፋት ዘመናትን አልፋ አሁን ከምትገኝበት ታሪክ ምዕራፍ የደረሰችው፣ ጉዞዋ በፀጥታና በሰላም ውስጥ ብቻ ስለነበር አይደለም። ጨለማውን እየገለጠች፤ ጉድባውን እየተሻገረች፤ ማዕበሉን እያለፈች፤ አቀበቱን እየዳኸች በእሳትና በአውሎ ነፋስ መካከል እየሰነጠቀች በመጓዝ ጭምር ነው።

በተመሳሳይ መንገድ እየሄድን የተለየ ውጤት አናመጣም ብለን አመንን። ከመግደልና ከመጨፍጨፍ፣ ከማሰርና ከማሳደድ የተለየ መንገድ እንከተል ብለን ወሰንን። አግላይና ዝግ የነበረውን የፖለቲካ ምኅዳር አፋን፤ ክፍትና አካታች በማድረግ፣ አቃፊና ደጋፊነቱን ለማረጋገጥ ጥረት አደረግን። የወኅኒ በሮቻችን ተከፍተው አእላፍ እስረኞች የነፃነትን አየር ተነፈሱ፤ በሀገር ቤትና በዳያስፖራ መካከል ያለውን ድልድይ ሰርተን ሺዎች ወደ ሀገራቸው ገቡ፤ ብረት አንግበው የትጥቅ ትግል ያካሂዱ የነበሩ የፖለቲካ ቡድኖች ወደ ሀገር ገብተው ሰላማዊ የፖለቲካ ትግልን ተቀላቀሉ።

የለውጥ እርምጃችን ኢትዮጵያን አዲሲቱ የተስፋ አድማስ፣ የአፍሪካ ፈርጥና ተምሳሌት ማድረግ እንጂ ኢትዮጵያን የኀዘን ማቅ ማልበስ አይደለም። ሀገርን ወደ ተሻለ ምዕራፍ ለማሸጋገር እስከተነሳን ድረስ እየመረረንም ቢሆን የምንቀበለው ሐሳብ ይኖራል። በሀገር አንድነት፣ ሉዓላዊነት፣ ዘላቂ ጥቅምና ክብር ላይ ግን ድርድር ሆነ ትዕግስት ፈፅሞ አይኖረንም። ከኢትዮጵያ የሚበልጥ፣ ከሕዝባችን የሚቀድም ምንም ነገር የለም። ለዴሞክራሲና ለሰላም ስንል እንታገላለን፤ ለሀገርና ለሕዝብ ስንል ደግሞ መራር ውሳኔን እንወስናለን።

እያለቀስን ብንቀጥል የጓዶቻችንን ዓላማ አናሳካም። ተስፋ ብንቆርጥ የጓዶቻችንን ሰንደቅ ከፍ አናደርገውም። ለምን እንዲህ ሆነ? ድክመታችን ምን ነበር? ምንስ ማድረግ ነበረብን? የሚሉትን በትክክለኛ ጥናት እንለያለን። ካጋጣመን ፈተና እንማራለን፤ ጥፋቱ እንዳይደገም አድርገን የሕገ - ወጥነት ቢሮዎቻችንን ሁሉ እንዘጋለን። ለአፍታም ግን ከጉዟችን አንገታም። ከዓላማችን አንዛነፍም። መንገዳችንንም አንቀይርም።

በመጨረሻም በፈተናችን ወቅት ከጎናችን በመቆም ድጋፋችሁና ማጽናናታችሁ ላልተለየን ወዳጅ ሀገራት በራሴና በኢፌድሪ መንግሥት ስም ምስጋናዬን አቀርባለሁ። ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝቦች፣ ለመከላከያ ሠራዊታችን፣ ለሟቾች የሥራ አጋሮችና ለሟች ቤተሰቦች ፈጣሪ መጽጽናትን እንዲሰጥ እመኛለሁ።

***ኢትዮጵያ ታፍራና ተከብራ ለዘላለም ትኑር!***

***ፈጣሪ ሀገራችንን ይባርክ!***







# "ለለውጡ ሲሉ ቤተሰባቸውን፤የግል ሕይወታቸውን የረሱ ጀግኖችን አጥተናል"

## ም/ጠ/ሚ/ር ደመቀ መኮንን

የተከበራችሁ የሟች ጓደኞቻችንና የቤተሰቦቻችን የቅርብ ወዳጆች፣ ከሩቅም ከቅርብም የተገኛችሁ የሀዘኑ ተካፋዮች፣ ወገን የሀገሬ ልጆች!! ዛሬ እጅግ መሪር ሞት ነው የገጠመን፡፡ ልጅነታቸውን ሳይጨርሱ ለተሰው፣ ህይወታቸውን ሀገራዊ መስተገብራቸውን የሰጡ ለለውጡ ከባድ ዋጋ ከፍለው ለብዙዎች ነፃነትን ካወጁና ለመጪው ዘመን ብርቱ ክንድ ሆነው የተሰለፉ የለውጥ ዘዋሪዎች ላይ እንዲህ አይነት ድርጊት መፈጸም እጅግ ከባድ ነው!! እጅግ ውስጥን የሚያደማ ጉዳት ነው፡፡ ባለፈው የሰኔ ወር እኩሌታ ለሥራ ጉዳይ ወደ ውጭ አገር ባቀናሁበት አጋጣሚ ከመድረሴ በመጀመሪያ የተቀበልኩት የስልክ ጥሪ ለማመን የሚከብድ፣ ሰውነትን በድንጋጤ የሚያርድ እንዲሁም ልብን በሐዘን የሚሰብር እኩይ መልዕክት የያዘ ነበር!!

ዛሬ ያጣናቸው ወንድሞቻችን፣ ጓዶቻችንን ወደ ውጭ ከመውጣቴ ከሰዓታት በፊት ከሦስቱም ጋር በተከታታይ ስለመጪው ስራዎቻችን፣ እኔ በምሄድበት ጉዞ ልሰራቸው ስለሚገቡ ጉዳዮች ምክረ ሀሳቦቻችንን በስልክ ተወያይተን ነበር፡፡ ሰው ባስበው አይሆንምና ያልተጠበቀው ሆነ፡፡ ውድ ያገሬ ሰው ‹‹ይሄን ምን ይሉታል? ›› ከተባለ እጅግ አሳዛኝ ትራጄዲ፣ እጅግ ጨካኝነት የተሞላበት ድርጊት ነው፡፡ ሞት ለሰው ልጅ ተፈጥሮአዊ ክስተት የሆነ አዲስ ነገር ባይሆንም በእንዲህ ዓይነት ክህደትን በተላበሰና በከፋ ጭካኔ ሲፈፀም፤ እጅግ መሪርና ከአዲስም አዲስ ነው፡፡ በህዝቡ ባለቤትና በአዴፓ መሪነት ለለውጡ ነፃነትን ለለውጡ ምክንያት ከሆኑት ዋና ዋና አጀንዳዎች ነፃነትን ለማስፈንና ሰብዓዊ መብትን ጥሰትን ለማረም በግንባር ቀደምትነት የታጋሉ ጓዶቻችን "በእስር ቤት ያሉ ዜጎቻችን ተስፋቸው ጨልሟል፡፡ አካላቸው ጎሏል፤ የህሊና እስረኛ ሆኗል" ብለው በግልፅ ለታገሉ መሪዎች ምላሹ ጥይት መሆኑ ምን አይነት በረዶ፣ ምን አይነት እንቆቅልሽ፣ ከክህደትና ከእናት ጡት ነካሽነት ውጭ ሌላ ምንስ ሊባል ይችላል?

በዚህ አጋጣሚ በአገር አቀፍና በክልል ዓቀፍ ከተሞች ተልዕኮዎቻችን መሳካት በተሰለፉበት አውድ ውስጥ ሆነው ከልጅነት እስከ ህይወተ እልፈት ደቂቃቸው በስራ ላይ እያሉ ሰሞኑን ህይወታቸው ላለፈው፣ የመከላከያ የጦር መኮንኖችና ለድርጅታችን ከፍተኛ አመራሮች የተሰማኝን ጥልቅ ሀዘን በራሴና በመንግስት ስም ለመግለጽ እወዳለሁ፡፡

ውድ የሀዘኑ ተካፋዮች የክልሉን ዘርፈ ብዙ ጥያቄዎች በዘላቂነት ለመስራት በጋራ ዓላማ ተጋምደው፣ በአመራር ቋንቋ ተላምደው በጓዳዊ አስተሳሰብ ተራምደው፣ በሙሉ ተስፋ ▶

# "ሠራዊታችንን በብሄርና በጎሳ ለመከፋፈል የተወሰደ ዕርምጃ ነው"



## አቶ ለማ መገርሳ

ቅዳሜ ሰኔ 15/2011 በአማራ ክልል በባህር ዳር ከተማ በዶክተር አምባቸው መኮንንና ባልደረቦቹ፣ እንዲሁም በአዲስ አበባ በመከላከያ ኤታማጆር ሹም ጀነራል ሰዓረ መኮንንና ሌላው ባልደረባችን ሜጀር ጀነራል ገዛኢ አበራ ላይ የተፈፀመው የግድያ ወንጀል፣ እጅግ አሳዛኝና አሰቃቂ ነው፡፡ እነዚህ ወገኖች ላገራቸው ደከመኝ፣ ሰለቸኝ ሳይሉ አገራቸውን ሲያገለግሉ የኖሩና ብዙ ዋጋ የከፈሉ ከመሆናቸው አንፃር ይህ ለነሱ የሚገባ አልነበረም፡፡ በጣም ያሳዝናል፤ ያማልም፡፡ በተለይም ጀነራል ሰዓረ ጠንካራ፣ ጀግና፣ ጠንካራ የጦር መሪ፣ ዕድሜ ልኩን ለአገሩ እስከ ትናንትናዋ ቀን ድረስ ከፍተኛ መስዋዕትነትን ሲከፍል የኖረ፣ በወታደራዊ ዕውቀት የደረጀ ሲሆን፣ እሱን ማጣት ጉዳትና ትልቅ ሀብት ማጣት ጉዳትና ትልቅ ሀብት ማጣት ነው፡፡ በተለይም በቅርብ አብሬ መሥራት ከጀመርኩ ወዲህ ባየሁባቸው ጊዜያቶች ለአገሩ ያለው ፍቅር እና በወታደራዊ ሳይንስ ረገድ ያለው እውቀት፣ በእውነት አገራችን በዚህ ወቅት እንዲህ ዓይነት ዕንቁና ጀግና ሰው ማጣቷ ለቤተሰቦቻቸው ብቻ ሳይሆን ለአገራቸውም ትልቅ ጉዳት ነው፡፡ ትልቅ ሀብት እንደ ማጣት ነው፡፡

ይሄ የተፈጠረው ድርጊት የሚያሳዝነው ወንድም በወንድሙ ላይ (ከውጭ የመጣ ወራሪ አይደለም)፤ ትናንት አብሮ ታግሎ ለአንድ ዓላማ ሲባል፣ አገራችንን ለመለወጥ አብረናቸው ስንሰራ የነበርን ወንድሞቻችን ያልናቸው ሰዎች ናቸው በወንድሞቻቸው ላይ ዛሬ ነፍጥ መዘው፣ ለዚህ አሰቃቂ ድርጊት የዳረጓቸው፡፡ ይህ ጉዳይ በእነኚህ ጀግኖቻችን ላይ የተፈፀመ ጥቃት ብቻ ሳይሆን በአጠቃላይ አገራችን፣ በተለይም በኢትዮጵያ ሉዓላዊነት ላይ የተፈፀመ ጥቃት ነው ብለን ነው የምናስበው፡፡ ስለዚህ አሁንም ቢሆን በተለይ የአገር መከላከያ ሠራዊታችን፣ ካሁን ቀደምም ቢሆን የአገሩን ዳር ድንበር በማስከበር በርካታ ገድሎችን ሲያስመዘግብ የኖረ፤ ኢትዮጵያን ሳያሳፍራት ሲያስከብር የነበረ መከታችን አለኝታነታችን ነው፤ መከላከያ ሀይላችን፡፡ ለዚህም ውድ ህይወቱን የሰዋ ኃይላችን ነው፡፡ ከዛም አልፎ ድንበር ማስከበር ብቻም ሳይሆን ውስጣዊ ሰላማችንን ለማስጠበቅ እስከዛሬም ድረስ የህይወትና የደም ዋጋ እየከፈለ ያለ ሀይላችን ነው፤ መከላከያ ሠራዊታችን፡፡

ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ የመከላከያ ሀይላችን ማወቅና መገንዘብ ያለበት፣ ይህ ሀይል የዚህች አገር የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት የማንም ብሔር፣ የማንም ጎሳ፣ የማንም ቡድን ሀይል አይደለም፡፡ የዚህች አገር ጠንካራ ሉዓላዊነቷን፣ ውስጣዊ ሰላሟን የሚያስከብር ሀይል ነው፡፡ የመላ ኢትዮጵያ ሕዝቦች መከታና አለኝታ ነው፤ ሠራዊታችን፡፡ በተለይም እየመረጡ ወታደራዊ መኮንኖቻችንና አዛዦቻችን ላይ የሚፈፀሙ የግድያ እርምጃዎችስ ሆን ተብሎ፣ ይሄንን ጠንካራ ምሽጋችንን ለመናድና ለማፍረስ፣ በብሔርና በጎሳ ለመከፋፈል እና ሠራዊታችን እንዲከፋፈል ለማድረግ ታስቦ እየተደረገ ያለ እኩይ ተግባር ስለሆነ፣ ከምንም በላይ መከላከያ ሀይላችን ይሄንን በሚገባ መገንዘብ ይኖርበታል፡፡

ከአሁን ቀደም ያላየነው ፈተና አይደለም፡፡ ሲገጥሙን የነበሩ፤ ነገር ግን በቁርጠኝነትና በትዕግስት ስንወጣና ስናልፋቸው የነበሩ በርካታ ፈተናዎች ነበሩ፡፡ አሁንም ቢሆን ፈተና ገጥሞናል፡፡ ፈተናን ደግሞ በመጋፈጥና በመሥራት፣ በመተባበር ማለፍና መታለፍ እንደሚችል ጥርጥር የለውም፡፡ በመሆኑም የመከላከያ ሀይላችን እንደ ትናንቱ ዛሬም ነገም ለአገሩ አንድነት፣ ለአገሩ ክብር፣ ለአገሩ ሰላምና ሉዓላዊነት ዛሬም ዘብ መቆም አለበት፡፡ ተጠናክሮ አንድና አንድ ሆኖ መሥራት አለበት፡፡

ስለዚህ ከመቼውም ጊዜ በላይ ይሄ ወቅት ጥንቃቄ የሚያስፈልግበት ወቅት፤ ትዕግስት የሚያስፈልግበት ወቅት በመሆኑ መላው የአገራችን ሕዝቦች በተረጋጋ መንፈስ ከወዲያም ከወዲህም ከሚናፈሱ ወሬዎችና አሉባልታዎች በመታቀብና በመደማመጥ ከመንግስታችን ጎን በመቆም ለአገራችን ሰላምና አንድነት በጋራ ተባብረን መሥራት አለብን እላለሁ፡፡ እንደ መከላከያ ሀይል፤ እንደ አገሪቱ የፀጥታ ሀይልም ይሄንን የተፈጠረውን ሁኔታ ለመቀልበስ ሌት ተቀን ሁሉ እየሰራ ነው ያለው፡፡ ይሄ ሥራ ወደፊትም ተጠናክሮ ይቀጥላል፡፡ ባጭር ጊዜ ውስጥም ይሄንን እንቀለብሳለን ብለን ነው የምናስበው፡፡ ስለዚህ ህዝባችንም ሳይወናበድ፤ ሳይሸበር ተረጋግቶ ከመንግስት ጎን ሆኖ ይህ ሠላም እንዲጠበቅ ወደ ቀድሞው ቦታ ሠላማችን እንድንመልስ የበኩሉን ጥረት ማድረግ አለበት እላለሁ፡፡ አመሰግናለሁ፡፡



◀የተሰለፉትን የቁርጥ ቀን ጀግኖች በእንዲህ ዓይነት ጭካኔ ማጣት ለሁላችንም የላቀው ፈተናና ፀፀት ነው!!

ጥቃቱ በህይወትና በማህበራዊ ገጽታው ለተጎጂዎችና ለቤተሰቦቻው፣ ለትግል አጋሮቻቸው እጅግ የከበደ ቢሆንም እንደምታው ግን ከዚህ የጠለቀ ነው፡፡ እንድምታው የህዝባችንን ታሪክ የማይመጥን በጭካኔ የታጀበ አረመኔ ድርጊት ነው፡፡ ድርጊቱ በሀገራችን ከስልጣንና ተያያዥነት ጉዳዮች ጋር የነበሩ የመጠፋፋት ባህሎች ዳግም ላይደገሙ የተሻገርነውን ወደ ኋላ የመለሰ አደገኛ ክስተት በመሆኑ ሁሉም በነቂስ ሊያወግዘውና በጽናት ሊታገለው ይገባል!! ከዚህ አኳያ መንግስትና መሪ ድርጅቱ ከህዝቡ ጋር በመሆን ድርጊቱን ማውገዝ ብቻ ሳይሆን እነዚህ ብርቅዬ ጀግኖቻችን ዛሬ በህይወት ቢያልፉም በዘመን የማያልፍ አበርክቶአቸውንና ፈለጋቸውን ዳር እንዲደርስ ሁላችንም በጽናት መንዝ መራመድና ማሳካት ይኖርብናል፡፡

የተከበራችሁ የሀገራችን ህዝቦች፣የተከበራችሁ የአማራ ክልል ህዝቦች፣ በሀገርና በክልል የተያዘውን የለውጥ አጀንዳ አጠናክሮ ለመቀጠል ዋነኛ ስራችን የህግ የበላይነት በማስከበር ሰላምን መገንባትና የኢኮኖሚ ማነቆዎችን በመፍታት ልማታችን ማፋጠን ነው፡፡ በዚህ ዘመን እነዚህን ወሳኝ ሥራዎችና ሌሎች አጀንዳዎችን ለመፈፀም ብዙ እድሎች እያሉ በተግባር ከእድሎቹ እና ከበጎ ተግባር እየራቅን የችግራችንን እድሜ እያራዘምን እንገኛለን፡፡ ከዚህ አዙሪት ለመውጣት ከስሜታዊነት፣ ከጀብደኝነት፣ ከግለኝነት እና እራስን ብቻ ከማዳመጥ ወጥተን ወደ ከፍታ የሚወስደውን ጥበቦች መከተል ማለትም፣ ምክንያታዊነትን፣ ህግና ስርዓት ማክበርን አርቆ ተመልካችነትን፣ መላበስ ይኖርብናል፡፤

ከዚህ አኳያ የክልላችን ህዝብ ታሪኩን የሚጠብቅ ጉዳይ ላይ በመሳተፍ አቃፊነቱን በመላው አለም ላይ ተከባብሮ ሰፍቶና ሞልቶ የመኖር ባህሉን አጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል፡፡ ከዚህ ውጭ የሚራመዱ ሀሳቦችና አስተምሮዎች ህዝባችንን ከከፍታው የሚያወርዱት መሆኑን አውቆ በጥንቃቄ ሊያያቸውና ሊመክታቸው ይገባል፡፡ በመጨረሻም በሰሞኑ ከወንድሞቻችን ህልፈተ ህይወት ጋር በተያያዘ በባህርዳር ከተማና አካባቢዋ የባሰ ጉዳት እንዳይደርስና ሂደቱም በቁጥጥር ስር እንዲውል ብርቱ ጥረት ላደረገው ህዝባችን የፀጥታ አካላትና ልዩ ልዩ የመንግስት አካላት ምስጋናዬን በአክብሮት እየገለፅኩ፤ ይኽ ተጠናክሮ እንዲቀጥል፣ ህግና ስርዓት እንዲነግስ በድጋሚ ጥሪዬን እያቀረብኩ፤ ለሀገራችን ህዝቦች፣ ለክልሉ ህዝብ ለድርጅታችን አባላት በተለይ ለቤተሰቦቻቸውና ለቅርብ ወዳጆቻቸው መጽናትን እመኛለሁ፡ ፡ ውድ የሀዘናችን ተካፋዮች እነዚህ ዛሬ ያጣናቸው ወንድሞቻችን ጀግኖቹ ለቤተሰቦቻቸው ተገቢ ጊዜ ሳይሰጡ ስለመጪው የግል ህይወታቸው ሳያስቡ፣ የለውጥ አጀንዳው ውስጥ ሆነው በድንገት ወድቀዋል፡፡ በዚህ ምክንያት እነርሱን ወንድሞችንን ዳግም ባናገኛቸውም የልጆቻቸውና የቤተሰባቸው ተስፋ ከቶም ቢሆን ሊጨልም አይገባም!! መንግስትና የለውጥ አጋሮች፣ የክልላችን ሕዝብ፣ መንግስትና የለውጥ አጋሮች ከጎናችሁ መሆናችንን ላረጋግጥላችሁ እወዳለሁ፡፡ ክብር ለጀግኖቹ ሰማዕታት አመሰግናለሁ፡፡

# “ቤተሰቤ ይበተናል እንጂ ኢትዮጵያዊነቴን አሳልፌ አልሰጥም በማለቱ ከህዲ ተብሏል”

## ጄነራል አበባው ታደሰ



በኢህአዴግ ዘመን ስማቸው ገንኖ ከሚጠሩ ደፋር ልበ ሙሉ የጦር መኮንኖች መሀል ስማቸው በግንባር ቀደምነት የሚጠሩት ጄነራል አበባው ታደሰ በጄነራሎቹ አስከሬን የሽኝት ፕሮግራም ላይ ተገኝተው ስለ ኹሉቱ የትግል አጋሮቻቸው አስገራሚ አስተያየትን ሰጥተዋል፡፡

በእድሜ ወጣት የሆኑት ጄነራል ታደሰ በጀግንነታቸው፣ በድንቅ የጦር ሜዳ ተጋድሏቸው በሠራዊቱ ዘንድ በእጅጉ የሚ ወደዱ፣ የአገር መከላከያ ሠራዊትን በበላይነት መምራት የሚችሉ ቢሆንም በአምባገነኑ መንግስት ከዓመታት በፊት ነበር ያለጊዜያቸው በጡረታ እንዲሰናበቱ የተደረጉት፡፡

ክብርት ወ/ሮ ሳህለወርቅ የኢፌድሪ ፕሬዝዳንት፣ ክቡር ዶ/ር ዐቢይ አሕመድ የኢፌድሪ ጠ/ሚኒስትርና የጦር ኃይሎች ጠቅላይ አዛዥ፣ የጀግኖች ሰማዕታት ቤተሰቦች በሙሉ፣ በዚህ የተዘበራረቀ አጋጣሚ ስለ ወንድሞቼ ትንሽ እንድናገር ስለተፈቀደልኝ በጣም አመሰግናለሁ፡፡

ጄነራል ሰዓረ ከእኔ በፊት የተናገረው ወንድሜ ብርሃኑ ምን ዓይነት ሰው እንደሆነ በደንብ ገልፆታል፡፡ ግን እኔ የማውቃቸውን የተወሰኑ ነገሮችን ላንሳ፡፡ ጄነራል ሰዓረ በአላማው ፅኑ የሆነ፣ ለሕዝብ ጥቅም ራሱን አሳልፎ የሰጠ፣ ራሱን ከሕዝብ በላይ አድርጎ አይቶ የማያቅ፣ ከልጅነቱ ጀምሮ አንድ ቀን ሳይንቀባረር፣ ሕይወቱን ሙሉ ለትግል የሰጠ ጄነራል ነበር፡ ፡ ጄነራል ሰዓረ በስራው ምስጉን፣ ጦርነትን በሚገባ የሚያውቅ ጦርነትን በሚገባ የሚያዘጋጅ፤ ብልህ፣ ጠንቃቃ፣ ጀግና፣ የጀግና ጀግና ሞዴል ነበር፡፡

ሰዓረ ራሱ ብቻ ጀግና አልነበረም፡፡ ጀግና ማፍራት የሚችል ግለሰብ ብቻ ሳይሆን ኤሊቶችን መፍጠር የሚችል የጀግና ሞዴል ነበር፡፡ እውነቱን ለመናገር አሁን ባለችው ኢትዮጵያ ምርጥ ኮማንደር ነው፡፡ ሰዓረ ባለበት ሁሉ ድል አለ፤ ጦርነት ለሰዓረ ቀላል ነው፡፡ የተረጋጋ ነው፡፡ ችግር መፍታት የሚችል ሰው ነው፡፡ ሰዓረ ዛሬ ሚሊየን እሱን ሊተኩ የሚችሉ ብዙ ጀግኖች ልጆችን አፍርቷል፡፡ ጄነራል ሰዓረ እጅግ ሲበዛ ኢትዮጵያዊ ነው፡፡ ኃይማኖት የማይለይ ብሔርን የማይለይ፣ በኢትዮጵያዊነቱ የማይደራደር፣ ፍፁም ኢትዮጵያዊ ነበር፡፡

እዚህ ላይ አንድ ነገር ልንገራችሁ፣ የፈለገው ይፈንዳ፡፡ ይሄ ለውጥ ከመጣ በኋላ ሰዓረ እንደ ከሀዲ ተቆጠረ በጥቂት ቡድኖች፡፡ ኢትዮጵያዊነቱን አሳልፎ እንዲሰጥ ከባድ ተፅዕኖ ደረሰበት........ (ረዥም ለቅሶ) ..... እሱ ግን አላደረገውም፡፡ ‹‹ ቤተሰቤ ይበተናል እንጂ ኢትዮጵያን ለጥፋት አሳልፌ አልሰጥም ›› አለ፡፡ ‹‹ ማንም ይምጣ ማን የእኔ መሪዬ ነው፡፡ እስከምሞት ድረስ በኢትዮጵያዊነቴ ሳልደራደር ለአገሬ እሰራለሁ ›› ነው ያለው ወንድሜ ቤተሰቦቹን አክባሪ፤ ጓደኞቹን ወዳጅ የተበተነ ሰብሳቢ፣ ቀልድ አዋቂ፣ እጅግ ሳቂታ ነው የማውቀው ሰዓረ፡፡

ጄነራል ገዛኢ የዓላማ ፅናቱ እንደተጠበቀ ሆኖ ኢትዮጵያ ውስጥ በተለይም ደግሞ አንድን ጦርነት ከሚያሸንፉና ወሳኝ ተብለው ከሚታወቁ ዋነኛ ስራዎች አንዱ ከኋላ የሚሰራው የሎጅስቲክስ ስራ ነው፡፡ ምናልባት የኢትዮጵያ ሠራዊት አሁን ባለው ሁኔታም ሆነ ትንሽ ወደ ኋላ ከሄድን ጄነራል ገዛኢን የሚያህል ሎጀስቲክስ አለ ብዬ አላምንም፡፡

ጄነራል ገዛኢ መ/ቤቱ በነበረበት ወቅት፣ ጥሩ ጭንቅላት አለው፡፡ ሀሳብ ያመነጫል፣ አርቆ ያስባል፣ አስተዋይ ነው፡፡ ስሜት አያጠቃውም፡ ፡ ከፍተኛ የሰላም አስከባሪ ኃላፊነትን መንግስት ሲሰጥ፣ ከራሳችን ሰላም አልፈን የወንድሞቻችን ሰላም ለመጠበቅ በምንሰራበት ወቅት ከፍተኛውን ሚና የተጫወተ፣ አሁን ላለው ሰላም አስከባሪ ምሳሌ የሚሆን ሰው ነው፡፡ በተጨማሪም ጄነራል ገዛኢ ቤተሰብን ወዳጅ፣ ጠንቃቃ፣ ብልህ፣ አስተዋይ መሪ ነበር፡፡

እኔ የሚገርመኝ ራሳቸውን ከልጅነታቸው ጀምረው ለሞት ያዘጋጁ እነዚህ ወንድሞቻችን፣ ምናልባትም ሞትን አሸትተው፣ ግማሽ መንገድ ሄደው፣ የተለማመዱ ሰዎች፣ እኔ እስከማውቃቸው ድረስ ግን ሕይወታችን ያልፋል ብለው የሚያስቡት፣ ጥይት በግንባራቸው እንጂ በጀርባችን ይመጣል ወይም እንመታለን ብለው አያስቡም ነበር፡፡

የሁላችንም ልብ የሰበረው ሕይወታቸው ማለፉ አይደለም፣ የሞቱበት አግባብ ሁለተኛ ሞት በመሆኑ ነው፡፡ እኔ እንደሚታየኝ ከዚህ በኋላ ቆም ብንል፣ እንደ ሕዝብ ቆመን ብናይ፣ ጣት ባንቀሳሰር፣ ከሀሳብ መማር ካልቻልን በደም እንማር፡፡ እኔ ላስተላልፍ የምፈልገው የኢትዮጵያ ሕዝብ ኢትዮጵያ ውስጥ ያለውም ይሁን፣ ከአገር ውጪ ያለው አንድነትን ነው የሚወደው፡፡ ሰላምን ነው የሚወደው ፍቅርን፣ መቻቻልን፣ ብልፅግናን ነው የሚወደው፡፡ ከዛ ውጭ ምንም ዓይነት ፍላጎት የለውም፡፡

መሪዎቻችን እባካችሁ ይሄን ተረድታችሁ ምሩን፡፡ እኛም መሪዎቻችንን ተከትለን ባለንበት ቦታ አንዳንድ ጠጠር ወርውረን አገራችንን ትልቅ እናድርግ፡፡ በአገሪቱ ውስጥ ያላችሁ የፀጥታ ሠራተኞች በሙሉ፣ አገሪቱ ከባድ ፈተና ውስጥ ነው ያለችው፡፡ በእጃችሁ ያለ እሳት በየትኛውም መለኪያ ከሕዝባችሁና ከአገራችሁ በታች እንጂ ከሕዝብና አገራችሁ በላይ አይደለም፡፡ ለመልዮአችሁና ለምትወዷት ሰንደቅ ዓላማችሁ ስትሉ፣ በፍፁም ታማኝነት መንግስታችሁንና አገራችሁን እንድታገለግሉ ነው አደራ የምላችሁ፡፡

ለኢትዮጵያ መንግሥት ለጀግኖች ቤተሰብና ለኢትዮጵያ ሕዝብ መጽናናትን እየተመኘሁ የማይታለፍ ነገር እንደሌለ እንዲታወቅልኝ መልዕክቴን አስተላልፋለሁ፡፡ እናልፈዋለን፡፡ አንበታተንም፡፡



ልዩ ዕትም



# “ስዓረ ለአገር በለፋ፣ ምን በድሎ ነው የሚገደለው?”

## ጀነራል ብርሃኑ ጁላ

የተከበራችሁ የሚች ቤተሰቦች፣ ወዳጅ ዘመዶች፣ እንዲሁም ክቡራንና ክቡራት፣ የጦር ኃይሎች ኢታማዦር ሹም ጀነራል ሰዓረ መኮንን የነበራቸው አጠቃላይ የትግል እንቅስቃሴ፣ ሰራዊታችንን ለመገንባት እንደሞዴል የተጠቀምንበት ታሪክ ነው፡፡ በሰራዊት ግንባታ፣ በውጊያ ዝግጅት፣ በውጊያ አመራር፣ በጀግንነት፣ ችግሮችን ጥሶ በማለፍ ፅናት የተላበሰ ጀነራል መኮንን ነው- ሰዓረ፡፡

እንደዚህ ዓይነት ወታደራዊ አመራሮች የሚያንፀባርቁት፣ የሚያሳዩት፣ የሚውሉት ውሎ ትውልድ ይቀርፃል፡፡ እሱም ትውልድን ይቀርፅ ስለነበር ጀነራል ሰዓረነረ እንደሞዴል እየወሰድን፣ ሰራዊታችንን በእነዛ መንገድ እየገነባን፣ በአገር ደረጃ የታወቀ፣ አገሩን መከላከል የሚችል ፣ ሌሎች የሚተርፍ ጀግና ሰራዊት እንዲፈጠር ከፍተኛ የሞዴልነት ሚና የነበረው ጄነራል ነው፡፡

ከሁሉ የማስታውሰው እኔም ስታገል የተገነባሁበት አንዱ ሞዴል ስራቸው፣ የሰርዶ ውጊያ ነው፡፡ የሰርዶ ውጊያ 50 ዲግሪ ሴንቲግሬድ፣ ውሃ በኮዳ ብትይዝ ውሃው ፈልቶ ለመጠጣት የማትችልበት የዐየር ፀባይ፣ ጓዶችን ይዞ የተሰጠውን የድርጅቱን ግዳጅ ለመፈፀም፣ ፀረ ሕዝብ የሆነውን ሀይል ግብዓተ መሬት እንዲገባ ለማድረግ በሰርዶ በተደረገው ግዳጅ ፣ጓዶች ግዳጅ ለመፈፀም ተንቀሳቅሰው ውሃ ፈልቶ አልቆ በረሃብ ተቃጥለው በውሃ ጥም ያለቁበት፣ የታፈኑ ጥቂት ጥይቶች ግዳጃቸውን ጨርሰው የተመለሱበትን ይህንን ዓይነት መከራ የበዛበት ውጊያን በፅናት የመራ ሰው መሆኑ ተነግሮን፣ እኛ ለሌሎች እየነገርን፣ ሰራዊታችንን እንድንገነባ ሞዴል የሆኑን የጦር መሪ ናቸው፡፡ ይህቺ አንዷ ዘለላ ናት፡፡ እንደዚህ ዓይነት ተመሳሳይ በርካታ ውጣ ውረዶችን እንዳለፈ ነው የተረዳነው፡፡

ይሄ የትጥቅ ትግል ጊዜ፣ የመከራ ጊዜ፣ የችግር ጊዜ፣ ፅናት የሚፈልግ ጊዜ፣ ጥቅም የሌለበት ጊዜ ራሱን ለህዝብ ሉዓላዊነትና ዴሞክራሲ ፣ ለህዝብ ነፃ መውጣት አሳልፎ የመስጠት ጊዜ፣ የነበረን የጄነራል ሰዓረ ፅናት ነው፡፡ ያ የሰዓረ ሰራዊት እኛ የገነባነው ሰራዊት እንደ ሞዴል ወስደን ስንገነባ፣ አሁን ያለን ሰራዊት ጀግና ሰራዊት ነው፡፡ጀግና ሰራዊት ብቻም ሳይሆን መሰረቱ፣ እርሾው ስለተጣለ የእርሱን አርአያ ተከትሎ ጀግንነቱን ተከትሎ የሚሄድ ሰራዊት አገራችን ይኖራታል ብዬ አስባለሁ፡፡

ከደርግ ውድቀት በኂላ ጄነራል ሰዓረ በርካታ ግዳጆችን ተቀብለው በጣም ትላልቅ የሰራዊት ክፍሎችን ሲመራ ነው የነበረው፡፡ ኮሮች መርቷል፣ ዕዞች መርቷል፡፡ የመራቸው ኮሮችና ዕዞች በእርሱ አምሳያ እንዲቀረፁ አድርጓል፡፡ የኢትዮ - ኤርትራን ጦርነት አገራችን ጦርነቱን በድል እንድትወጣ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አድርጓል፡፡ በትጥቅ ትግሉ ጊዜ የነበረ ጀግንነት በኢትዮ ኤርትራ ጦነትም ጊዜ አሳይቷል፡፡ አገራችን በእውነቱ እንደዚህ ዓይነት መሪ ስለነበራትና ስላላት ልትኮራ ይገባታል፡፡

ወደ ግል ባህሪው ስመጣ እኔ ከጀነራል ሰዓረ ጋር በቅርብ አልሰራሁም፡፡ ግን ጀነራል ሰዓረ ሰሜን ዕዝ አመራር ሆኖ፣ እኔ ማዕከላዊ ዕዝ ሆኜ፣ ጀነራል ሰዓረ ሰሜን ወይም ሌላ ዕዝ ሆኖ ሁላችን የሰራዊት አመራሮች እንተዋወቃለን፡፡ አንዳችንን እናውቃለን፡፡ ደካማ ጎናችንንም ሆነ ጠንካራ ጎናችንን እንተዋወቃለን፡፡ ስለዚህ በዚህ አጋጣሚ ልክ አጠገቡ እንዳለ ሰው አውቀዋለሁ፡፡ በጣም የተረጋጋ ሰው ነው፡፡ የተረጋጋ ሰው ነው፣ ሌላውንም መረጋጋት ይችላል፡፡ ሰው አክባሪ ነው፡፡ ሰዓረ ጓደኛ አይመርጥም፤ ከሁሉም ነው የሚግባባው፡፡ ከታናሹም ፣በጣም መስመራዊ ደረጃ ካለ ኦፊሰርም፣ ከተራ ወታደርም፣ ከሚኒስትርም ፣ከአገር መሪም ከሁሉም መቅረብ የሚችል፣ ቀለል ያለ ሰው መሆኑን መመስከር እችላለሁ፡፡

ጀነራል ሰዓረ እኔ እራሴ ከእርሱ የወሰድኳቸው ልምዶች አሉ፡፡ በጣም የተረጋጋ ከመሆኑ የተነሳ ነገሮችን ለመፍታት የሚሄድበት ጥበብ በጣም ለሰራዊታችን ሞዴል ነው ብዬ መውሰድ እችላለሁና እንደዚህ ዓይነት በ35 እና በ40 ዓመት የሚፈጠሩ የሰራዊትም ይሁን፣ የሀገር መሪዎችን ማጣት በጣም ያማል፡፡ እኔ ጦርነት ኖሮ ጦርነቱን እያዘዙ ቢሞቱ “የተፈጥሮ ነው፣ ያጋጥማል” ብለህ ትወስዳለህ፡፡ ወይንም ከእኩያቸው ጋር ተጣልተው እርስ በርስ ከእኩያቸው ጋር ቢገዳደሉ “የሰው ልጅ ባህሪ ነው፣ ንዴትን መቋቋም ስላልቻሉ ተፈጥሮ ነው” ብለህ ታልፈዋለህ፡፡ ለአገር እየሰራ፣ ሁሉንም እያቻቻለና ሁሉንም እያገለገለ፣ ሁሉንም እያስተናገደ፣ ባለበት ወቅት ምን በድሎ ነው?

“ምን በድሎ ነው የሚገደለው?” የሚል ጥያቄ ሳነሳ፣ እኔን እንደ አንድ ሰው በግል ያመኛል!! በጣም ትክክል አይደለም!! ጀነራሉ የሥልጣን ሩጫም የላቸውም፡፡ ሰው እንዳይሞት፣ ሰው ከተፈናቀለ እንዲመለስ ከማድረግ ውጭ ሌላ አላማ የላቸውም፡፡ አብረን ነው የምንሰራው፡፡ ምንም የሚያስገድላቸው ነገር የላቸውም፡፡ እኛ የሆነው ነገር ቆጭቶናል፣ አናዶናል፡፡ ግን ጀነራል ሰዓረ ይሰራ የነበረውን፣ ጀነራል ሰዓረ የሚሰራለትን ዓላማ በማሳካት፣ የጀነራል ሰዓረ ገዳዮችን ለማሳሰር፣ የእነርሱ ፍላጎት እንዳይሳካ ለማድረግ፣ ቆርጠን እንታገላለን፡፡ ሰራዊታችን አንድነቱን ጠብቆ፣የጀነራል ሰዓረን ዓርማ ይዞ፣ የጀነራል ሰዓረን ፕላን ይዞ፣ ኢትዮጵያ ሀገሩን ለመጠበቅ በጽናት እንዲቆም እጠይቃለሁ፡፡

ግድያው እኔ የሚመስለኝ መበተን ነው፡፡ እኛን መበተን ነው ፍላጎታቸው፡፡ በዘር ተከፋፍለን እንድንባላ፣ መንግስት እንዳይረጋጋ፣ እንዲፈርስ፤ ሳይረጋጋ ሲቀር ደግሞ በሽግግር መንግስት ስም ወደ ስልጣን ለማምጣት የሚዳረግ ሩጫ ነው፡፡ ግን አይሳካም እንታጋላለን፡፡ (ከፍተኛ ጭብጨባ)

ጀነራል ገዛኢን በተመለከተ፤ በጣም ለዚህ አገር የለፉና የደከሙ ናቸው፡፡ በትጥቅ ትግሉ ቅድም እንደገለፅኩት ከሰዓረ ባልተናነሰ ሁኔታ ያለፉ ሰው ናቸው፡፡ ከህገ - መንግስት ምስረታ በኂላ የኢፌድሪ መከላከያ ሰራዊት አባል ሆነው፣ በጣም ትላልቅ ሥራ ሰርተዋል፡፡ “የኢትዮጵያ የመከላከያ ሰራዊት የሎጀስቲክስ መሀንዲስ” ብለን ነው የምንጠራቸው፡፡ “የሎጀስቲክስ” ባህሉን ማነው የገነባው? ከተባለ እርሱ ነው ፡፡ ቀድሞ መዘጋጀት የሚችል፣ ከፍተኛ ኃይል በአንድ ጊዜ “ሞባላይዝድ” ማድረግ የሚችል፣ እውነትም ለሎጀስቲክስ የተፈጠረ፣ በጣም በሳል መሪ ነበር የነበረወ፡፡

እርሱም ምንም አላደረገም!! ጓደኛው ቤት ሻይ ሊጠጣ ሄዶ መገደል አልነበረበትም፡፡ ምን አደረገ? አሁን የግል ሥራ ነው የሚሰራው፡፡ ከፖለቲካም በጣም የራቀ ነው፡፡ ለአገሪቷ ሰርቶ፣ አገሪቷን ህገ - መንግስት እንዲኖራት፣ አገሪቷ ሳትፈርስ አንድነቷ ተጠብቆ እዚህ እንድትደርስ ወሳኝ ሚና ያለው ሰው ነውና፡፡

በኦሮምኛ አንድ ተረት አለ፣ “የማይረባ ሰው ጀግና ያበላሻል” እንደማለት ነው፣ ትርጓሜው ወደ አማርኛ ሲመለስ፡፡ እኛም እንደዚህ አይነት ሁኔታ ነው ያጋጠመን፡፡ ስለሆነም አሁን ከፍተኛ ችግር ውስጥ ገብተናል፡፡ የክልል አመራር ፣ የክልል ካቢኔ ቤት ውስጥ (የስብሰባ አዳራሽ ውስጥ) የሚረሽኑ የስልጣን ጥመኞች፣ ስድ አደጎች፣ ችግር ፈጥረውብናል፡፡ ዕንቁ መሪዎቻችንን አጥተናል፣ ከፍተኛ የሀዘን ድባብ ውስጥ እንገኛለን፣ ግን ደግሞ እናሸንፋለን!! አመሰግናለሁ፡፡

ልዩ ዕትም



# የኛ ስልጣኔ ካልሰማኸኝ እንካ ጥይት



ሁሴን ከድር

በኢትዮጵያ የፖለቲካ ሂደት ፖለቲከኞች በሃሳብ፣በርእዮተ ዓለም እና በፍላጎት መለያየት ምክንያት ሹሞች ሲገዳደሉ የሰኔ 15ቱ የባሕርዳር ግድያ የመጀመርያ አይደለም፡፡ በ1953ት ሁለቱ ወንድማማቾች መንግሥቱ ንዋይና ግርማሜ ንዋይ፣ “የአጼ ኃይለሥላሴ ሥርዓትና ሹማምንቶች ሀገሪቷን ከዘፈቁበት የችግርና የመከራ ማጥ ለማውጣት ሰንኮፎቹን መንቀል ያስፈልጋል” በሚል በገነተ ልዑል ቤተ-መንግሥት 21 መሳፍንትና መኳንንትን ረሽነዋል፡፡ በርግጥ ሦስቱ ተርፈዋል፡፡ በ1967 ደርግ የአሮጌው ሥርዓት በዝባዥና አቆርቋዥ ያላቸውን 17ጄኔራል መኮንኖች ጄኔራል አማን አንዶምንና 42 ሚኒስትሮችና በከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊነት ላይ የነበሩ፤ በአጠቃላይ 60 የንጉሱ ሹማምንትን አስሮ ረሽኗል፡፡ በግንቦት 8ቀን 1981 መፈንቅለ መንግሥት ሊያደርጉ ሲሉ ተደርሶባቸዋል በተባሉ12ጄኔራል መኮንኖች ሞት፣15ቱ ላይ ጽኑ እስራት ተፈረደባቸው፡፡ በኢትዮጵያ ታላላቅ ጄኔራሎች ላይ ደርግ ርሽና በማካሄድ ሀገሪቱን ለከፍተኛ ኪሳራና ውድቀት ዳርጓታል፡፡

በኢትዮጵያ ለሥልጣን ሲባል፣በሴራ ፖለቲካ፣በምቀኝነት፣በክፋት፣በቅናት ፖለቲከኞች ሲገዳደሉ በታሪክ አንብበናል፡፡ ከ1953 እስከ 2011 ባሉት 58 ዓመታት ከአራት ጊዜ በላይ የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ ከአራት ጊዜ በላይ የመንግሥት ለውጥ፣ በርካታ ጊዜ ለሥልጣን የተደረገ ሽኩቻ አጋጥሞናል፡፡ ታሪካዊ እልቂት የተከሰተበት የኢህአፓና የደርግ መገዳደል የትውልድ እልቂት ያስከተለ እነደነበር የማይረሳ፤ ታሪክ መዝግቦት ያለፈ እውነታ ነው፡፡

በቀደሙ ዘመናትም አጼዎቹ ሥልጣንን የሚረካከቡት በዲሞክራሲያዊና በይሁንታ ተፈቃቅደው አልነበረም፡፡ አንዱ በሌላው ላይ አሲሮ ጦር መዝዞ ተፋልሞ ተሸናንፎ፣ተሸናፊ ተዋርዶ ጭምር ነበር፡፡ በመባላት፣በመፋጀት፣በመተላለቅ፣ በጉልበት፣ በመመቀኛኘት፣ በተንኮል ጭምር ነው፡፡ ንግሥናን ለመቆጣጠር አይደለም በአንድ የዘር ሐረግ ውስጥ ይቅርና በቤተሰብ መካከል፣ከቶም በወንድማማቾች መካከል መገዳደል ተከስቶ አልፏል፡፡ በራሳቸው ፍላጎት ወይም በሹመት አመቻቾቹ ሴራ ነበር የኢትዮጵያ የፖለቲካ ሥርዓት ዛሬ ላይ የደረሰው፡፡ መለስ ብለን የቀደሙ የአጼው ሥርዓት ታሪኮችን ካነበብን እውነታውን እናገኛለን፡፡ በይፋትና በሸዋ ሱልጣኔት ታሪክም ይህ ክስተት አልፏል፡፡ የሴራ ፖለቲካ የኢትዮጵያም የዓለምም የፖለቲካ እኩይ ገጽታ ሆኖ ይኸው የ21ኛው ክፍለ ዘመን ድረስ እስከመምጣት ደርሷል፡፡

## ጀብድ ወይስ መፈንቅለ መንግሥት

ይህ በእንዲህ እንዳለ ባሳለፍነው ሳምንት ብርጋዲየር ጀኔራል አሳምነው ጽጌ በአማራ ክልል ርዕሰ መስተዳድር ላይ ያደረገው ግድያ የመፈንቅለ መንግሥት ባሕሪ አለው ለማለት ቸግሮኛል፡፡ ለመሆኑ አሳምነው ጽጌ የዘውጌ ፖለቲካ አራማጅ ሆኖ ዶክተር አምባቸውንና ባልደረቦቻቸውን ገድሎ በአማራ ክልል ለምን ያህል ጊዜ ሥልጣን ላይ እቆያለሁ ብሎ ነው “ድርጊቱ መፈንቅለ መንግሥት ነው” የሚባለው፡፡ አንድ መፈንቅለ መንግሥት ለማድረግ የሚያቅድ ጀነራል የክልል መሥተዳድር በመግደል ብቻ ሥልጣን ይገኙ እቆያለሁ ብሎ ያስባል? ቁልፍ የክልሉ ተቋማት የሆኑትን እንደ መገናኛ ቢሮ ያሉትን አይዙም ኖሯል?

የአማራ ክልልን በመምራት ኢትዮጵያን እንደመራ ሊቆጥር ነው መፈንቅለ መንግሥት ያደረገው? በዚህ የቃላት ውኹርንብር ውስጥ ገብቶ መቧቸርም ሆነ መሟገት ብዙም የሚያስፈልግ አይመስለኝም፡፡ በእውነት ላይ መከራከር ጉንጭ ማልፋት ነው፡፡

በቅርቡ ብርጋዲየር ጀነራል አሳምነው ጽጌ የአማራ ክልል ልዩ ሃይሎችን ባስመረቁበት ወቅት “በታሪካችን ወደኋላ ሄደን ከ500 ዓመት በፊት እንደዚህ ዓይነት ትልቅ ፈተና ገጥሞን ነበር፡፡ እሱን ፈተና አልፈን እዚህ ደርሰናል፡፡ አሁን ከሱ ትንሽ ጠንከር ያለ የመከበብ ስሜት በየትኛውም ቦታ ላይ፣ በዘራችን ብቻ የመጠቃት ስሜቶች አሉ፡፡ ይሄን የመቀልበስ የዚህ ትውልድ ኃላፊነት ነው፡፡ የዚህ ኃይል ኃላፊነት ነው፡፡ ስለዚህ ልዩ ኃይሎች ግዴታችሁን እንድትወጡ አደራ እላለሁ፡፡” ይህ ማለት የተደገሰ ጦርነት እንዳለ በግልጽ የሚያሳይ ጥቁምታ ነበር፡፡ ሆኖም ድግሱ ወደ አመራሮች መሆኑን አይጠቁምም እንጂ፡፡ ለመሆኑ ከ500 ዓመታት በፊት በተለይ እሳቸው እንደጠቀሱት “በዘራችን ብቻ የመጠቃት ስሜት..” የተባለው ምን ይሆን? የኢትዮጵያ ሕዝብ ከ500 ዓመታት በፊት አንተ አማራ፣አንተ ጉራጌ፣አንተ ትግሬ አንተ ኦሮሞ.... ይባባል ነበርን? ሰዎች በዘውጌ አስተሳሰብ ሲታጠሩ ከእውነታው እስከመውጣት ርቀው ይሄዳሉ፡፡ ተከታዮቻቸውን ለማሳመን ታሪክን እስከመፍጠርም ይደርሳሉ፡፡

የጀነራሉ ንግግር በአስቸኳይ ሊታረም የሚገባው ነበር፡፡ የክልሉ መስተዳድር በይደር ያሳለፈው ነገር ዋጋ አስከፍሎታል፡፡ ባይሆን በእልህ ተነሳስቶ፣ ብርጌድ ጦር አሰልፎ “ተቀናቃኜ ነው” ያሉትን ኃይል ለማጥፋት ይሄን ያክል ርቀት መሄድ ከጀመርን እድገታችን ምኑ ላይ ነው? ጉልበት አለኝ፣ለሴራዬ ማስፈጸሚያ የሚያገለግሉ ጀሌዎቼን አሰልፊያለሁ፣በቂ መሳርያ ታጥቂያለሁ ብሎ ያሰበ አንድ የተከበረ የጦር ጀነራል፤ በሃሳብ አልተግባቡኝም፣ለምን የኔን ሃሳብ አልተቀበሉም? በሚል ራሳቸውን መከላከል በማይችሉበት ሁኔታ በመሳርያ ካነጋገሯቸው ምኑ ላይ ነው የዕድሜ ልዩነታችን? ምኑ ላይ ነው የወታደራዊ ዕውቀት ልዩነታችን? ምኑ ላይ ነው ይህንን ሁሉ ደረጃ የመምጣት ጥረታችን?

ለኔ ብርጋዲየር ጀነራል አሳምነውንም ሆነ ዶክተር አምባቸውንና ሌሎች የስራ ባልደረቦቻቸውን ማጣት ትልቅ ኪሳራ ነው፡፡ አገሪቷ ላለፉት አርባ ዓመታት ከፍተኛ ወጪ አውጥታ፣ ጊዜ ሰጥታ፣ በተሰጥኦዋቸው ላይ እሴት ጨምራ፤በእውቀታቸው፣በልምዳቸው፣በብቃታቸው ጫፍ ደርሰውልኛል ብላ በተደሰተችበት ወቅት የሀዘን ማቅ እንድትለብስ መገደዷ ከቤተሰብም በላይ ሃዘኑ የኢትዮጵያ ነው፡፡

## የከሸፈው የንግግር ልማድ

ያዳበርነው ተነጋግሮ የመተማመን ባሕል የለንም፡፡ እንዲያም ሆኖ “የውይይት ባሕላችን” ሲባል ሁሌም ከየት ያመጣነው? በማለት እጠይቃለሁ፡፡ በርግጥ ከአፋር ማኅበረሰብ ያልወረስነው ድንቅ የመደማመጥና መረጃ የመለዋወጥ ባሕል ነበር፡፡ ከጉራጌ፣ከስልጤ ፣ከወለኔ ያልወረስነው ምርጥ የሴራ(የሽምግልና) ባሕል ነበር፣ የሙርሲዎችን ያህል የውይይት ባሕል የከተሜ ፖለቲከኞች አላዳበርንም፡፡ከአባቶቻችን ያልወረስነው ምርጥ “የበላ ልበልሃ”፣ “የተጠየቅ ልጠየቅ” ባሕል ነበረን፡፡ የተጣላን ማስታረቂያ ጎሚን ማርከሻ ቂምን ማፍረሻ ባሕል ነበረን፡፡ ልናዳብረው ልናሳድገው ሲገባ በቸልታ አከሸፍነው፡፡ አናወርስ ብለን አደበዘዝነው፡፡ ስለባሕላችን እናወራለን ግን በባሕላችን አንኖርም፡፡ በፖለቲካ ስንናቆር፣ በዘር ስንቧደን፣በክልል ስንጠብ ባሕላችንን ያስቀመጥንበት ጠፋን፡፡

“የንባብ ባሕላችን፣የውይይት ባሕላችን፣የመደማመጥ ባሕላችን....” በሚል በሚዲያዎች የሚገለጸው የአፍ ልማድ ቢሆን እንጂ አንዳችም ውርስ የለንም፡፡ ውርሱን ሙት ፋይል ውስጥ ከተነዋልና፡፡ እንዲጠፋ አድርገነው የነበረው ባሕላችን የመገዳደል፣ደም የመቃባት፣የቂም በቀል፣ የኩርፊያ፣ የመለገም፣ ጠላታችንን የማዋረጃ ቀን የመቁጠር፣ በክፉ የመጠራጠርና የማድባት አቧራ አራግፎ እንዲነሳ እያመቻቸን ነው፡፡ በለው በለው፣ “ገዳይ ገዳይ ያልሽው አባትሽ አይገድል፣ አርሶ ▶



ልዩ ዕትም

ያብላሽ እንጂ ሆድሽ እንዳይጎድል” እያልን ገበሬን ንቀን ገዳይን የማወደስ ባሕል እያዳበርን የመጣነው፡፡ ትናንት በአማራ ክልል የተደረገው ግድያ ከባሕላችን አንዱ በሆነው በቂም ማድባት በቀል ነው፡፡

ከሰሞኑ በሚደረጉ የመገናኛ ብዙሃን ዝግጅቶች እውነቱን የማውጣት ሥራ በተሰራ ቁጥር የምናገኘው የባሕላችን ውጤትን ነው፡፡ የክልሉ መሥተዳድር በተደጋጋሚ ከአሳምነው ጽጌ ጋር በቃላት የሚያጋጨው የማኅበረሰቡ ደህንነት በክልሉ የጸጥታና ደህንነት ቢሮ በኩል እየተጠበቀ አይደለም፡፡ “ዜጎች በመስተዳደሩ አመኔታ እንዳያገኙ ያደረገው ያንተ ቢሮ ሥራ ነው፡፡ ልዩ ኃይል ማሰልጠኑ ምን ይጠቅማል? ከአጎራባች ክልሎች የምናደርገው ጸብ አጫሪነት አይጠቅመንም፣” የመሳሰሉት ጉዳዮች ከአሳምነው ፍላጎትና እቅድ ጋ አለመሄዱ ጸቡን ማክረሩን ነው የሰማነው፡፡ መተማመን፣መደማመጥ፣ መከባበር ቢኖር የሰይጣን መፈንጫ ባልሆንን ነበር፡፡

## ነገስ


ዛሬ የታየው እልቂት በፊልም ተመልካቾች ቋንቋ ለነገው አለመግባባታችን ማሳያ “ፕሮቫ” ነው፡፡ ከስህተታችን መታረም ካልቻልን በአማራ ክልል የፈነዳው፣በሌላው ክልል ላለመቀጠሉ ምንም ዋስትና የለም፡፡ ዋስትና እንዳይኖር ማሳያው ምንም ማስተንፈሻ ጫፍ አለመሰራቱ ነው፡፡ አሁን ጫፍ ላይ ነው ያለነው፡፡ በሃይል እንጂ በጥበብ አይደለም ሀገራችን የቆመችው፡፡ የጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ መንግሥት የማስጠንቀቂያ ደውል አቃጭሎበታል፡፡ በአስቸኳይ መንቃት ይገባዋል፡፡

ከሁሉም በፊት ኢትዮጵያችን ትቀድማለች፡፡ ኢትዮጵያን እንመራለን የምትሉ ሹማምንት ሃሳባችሁን በጠረጴዛ ዙርያ አስቀምጣችሁ፣ከዘራችሁ በፊት ሀገራችሁን አይታችሁ እንጂ የብሄርና የሆታ ድምጸት ሊያታልላችሁ አይገባም፡፡በባሕላችን፣በልማዳችን ያሉ የመነጋገር እሴቶችን (የተጠየቀ ልጠየቅ፣የበላ ልበልሃ) ወደዘመናዊ የውይይት ልማድ ማምጣት ይኖርብናል፡፡ እንደቆሎ የተበተኑ ከአፋቸው ሞት እንጂ አበባ የማያወጣ የጦር መሳርያዎች ከየቦታው ሊሰበሰቡ ይገባል፡፡ ሁላችንም ትክክል ልንሆን አንችልም፡፡ ትክክል አይደለህም የተባለ አካል ሃሳቡን ማረም እንጂ በግድ ሃሳቤን ካልተቀበላችሁኝ በሚል እምቧ ከረዩ ማለት ሥልጣኔን አያሳይም፡፡ ጽንፈኛ ብሄርተኝነት አውዳሚ የጦር መሳርያ ነው፡፡ ሀገርን የማዳን ኃላፊነት ሁላችንም ላይ የተጣለ ነው፡፡ በየማኅበራዊ መገናኛ ብዙኃን ስሜታዊ ደጋፊን ለመሰብሰብ ጸብ አጫሪ ጽሁፎችን መለጠፍ ሀገርን ለማፍረስ ከማሴር ተለይቶ መታየት የለበትም፡፡

በጋራ፣በፍቅር በመተሳሰብ እንድንኗኗር ከተፈለገ ልብ አበጦች ተንፈስ ማለት አለባቸው፡፡ መሳርያ አስቀምጠን ወደኋላ ሄደን ከባህላችን እንማር፡፡ የአያቶቻችንን የንግግር ባሕል ምን እንደሚመስል እንፈትሽ በአራቱም አቅጣጫ በመመልከት እንደገና ሀ ብለን እንማር፡፡ በድርጊታችን ልናፍር ይገባል፡፡ ብርጋዴር ጀነራል አሳምነው ማሳያ ሆኑ እንጂ ሁላችንም ውስጣችን ቢፈተሽ ጠላታችን ያልነውን በንግግር ከማሳመን ይልቅ በኃይል ማጥፋትን ነው የምንፈልገው፡፡ ለኛ ለኢትዮጵያውያን የሚያዋጣን አንድነት ሕብረት እንጂ በጎጥ፣ በዘር መፋጀት አይደለም፡፡ ዘረኝነት ቆሻሻ ተግባር ነው፡፡ ‹ኢትዮጵያውያን የሚባሉ ሕዝቦች እዚህ ምድርና እዚህ አካባቢ ነበሩ፣ እርስ በርስ ተባልተው ተላለቁ› እንድንባል የማንፈልግ እስከሆንን ድረስ በዘር፣በጎጥ መከፋፈል ይብቃን፡፡ ዛሬውኑ እንንቃ!!!

*መልካም ሳምንት*

# ሽንቁሮች



ፍቅርተ ተሾመ

## ዝናቡ

በአንድ ሽንቁሮቹ በበዙበት ቤት ውስጥ በበጋ የሚያስገቡት የፀሃይ ጨረር እንደማማሩ ሁሉ በክረምትም የሚያስገባው ዝናብ ቤቱን ማመሳቀሉ የማይቀር ነው፡፡ እንደ ሽንቁሩ መጥበብም ሳይሆን የሚያመጣው ጣጣ ብዙ ነው፤ እቃውን ያበሰብሳል፣ ወለሉንም በውሃ ያጥለቀልቃል፡፡ ዝናቡ ካላቆመ ቢወለውሉት አይደርቅም እቃውን ቢያነሱት አያመልጥም፡፡ የቸገረው ላስቲክ ከላዩ ያስርበታል ያለው ደግሞ ፕላስተር ይለጥፍበታል እርሱም ቢሆን ሽንቁሮቹ ካልበዙ ነው፡፡ ይህች ያረጀ ጣሪያዋን ያልቀየረች ሽንቁሮቹ የበዛባት ሃገር በዚህ የፖለቲካው ዝናቡ አላቆም ቢላት በዚያ ፀሃይ እና ዝናቡ እየተፈራረቀበት ጣሪያው ሽንቁሩን እያበዛ ህዝቡን ከአመት እስከ አመት ቤት በተባለች ሃገር ውስጥ እንደ በረንዳ አዳሪ መድረሻ አጥቷል፡፡ ሽንቁሮቹ ቤተሰብን እረፍት፣ ሰላም እና መረጋጋትን ይነሳሉ፡፡ የምሬትና የብሶት እንዲሁም የንጭንጭ ምክንያት ይሆናል፡፡ ሚዛን የማይደፉ የድለላ እና ማረጋጊያ የመሰሉ ሆኖም ፖለቲካዊ ጉንጉናቸው የጎላ ሃሳቦች የወረዱ ባንዲራዎች ከመሰቀላቸው ማብላላት መጀመሩ አይቀሬ ነው፡፡ ህዝብ ለክልከላው አመርቂ ምክንያት እንዳልተሰጠው ህፃን ልጅ አሁንም አሁንም መጠየቁ አይቀርም አልያም በጉልበት እና በቁጣ ዝም እንዲል ማስጠንቀቂያ እስካልተሰጠው ድረስ ጥያቄው ጥያቄ ሆኖ መቀጠሉ አይቀሬ ነው፡፡ ህዝብ አዲስ መሪ አዲስ ስርዓትን የሚሻው ካለበት አዘቅት ቢቻለው በተአምር የሚያወጣው ካልተቻለው መንገዱን የሚያሲዘውን ለማየት እንጂ በሻገተው ጣራ ስር በሽንቁሮቹ ወጋገን እየተዝናና ኋላ የሚያመጣውን እዳ ተኝቶ ከሚጠብቀው እና ሽንቁሮቹን እያሰፋ የሚጃጃልን አይሻም፡፡

> በአለም ላይ በሰላም ማስከበር ሚናዋ የገነነችዋ ኢትዮጵያ ለራሷ መሆን ያቃታት ለምንድነው? ጥል፣ ተንኮል፣ ሸኩቻ እና አመፅ ሁልጊዜም ራሳቸውን አዋቂ ነኝ ባሉ ምሁራን አነሳሽነት ወይም በባለስልጣናት መካከል እና ምክንያትነት ህዝብ ያልቃል የሰው ልጅ ደም በከንቱ በግፍ ይፈሳል

## መፈንቅለ መንግሥት

ይሄ የአመት የደም ግብር የመሰለ ግድያ አመቱን ሙሉ ከነበረው አደጋ የሚለየው በፖለቲካዊ ይዘቱ ቋሚ ተሰላፊዎቹን ሰለባ ያደረገ በመሆኑ ነው፡፡ አንድን በባስልጣኖች ላይ የደረሰን አደጋ ግን ምክንያቱ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ውስጥ መፈንቅለ መንግስት ብሎ መሰየም አግባብነት ያለው አይሆንም፡፡ ይሄ የአንድ ክልል ባለስልጣናት ላይ ያተኮረ ጥቃት መሆኑ አንድ እውነት ነው፤ በወታደሮች የተፈፀመ መሆኑ ሌላ እውነት ነው ከዚህ ባለፈ የሚሰጡትን ቅጥያዎች መቀበል ግን ሚዛን አይደፋም፡፡ ምክንያት አንድ ግድያውን የፈፀሙት አካላት አላማቸው ከዚህ ያላለፈ ሊሆን እንደሚችል የተሰጠ ምንም መረጃ የለም፡፡ በእውነቱ ከሆነ አንድን ክልል ብቻውን ለመያዝ የሚሞክር አካል ካለ ከፌደራሉ መንግስት ጋር ተጣጥሞ በምን ሂሳብ ብቻውን ሊያስተዳደር እንዳሰበ ማወቅ በጣሙን አጓጊ ያደርገዋል፡፡ ምክንያቱም ይሄ ትልቅ አቅም እና አጀንዳ ወይም ተቃርኖ ያዘለ ለመሆኑ ማሳያ ስለሚሆን ጥያቄን ያጭራል፡፡ ሌላኛው እሳቤ ሊሆን የሚችለው የግድያው የመጨረሻ ግብ ግድያ ከሆነስ? በዚህ በሴራ በተሞላ ፖለቲካ ውስጥ እነኚህ በአደባባይ ሊነገሩ የማይደፈሩ ሃሳቦች ቢሆኑም እውነት ግን ከነዚህ ውስጥ ነው፡፡ መንግስት የህብረተሰቡን ሃሳብ ከዘረኝነት ሃሳብ ገሸሽ በማድረግ የመፈንቅለ መንግሥት ሃሳብን ሲያጎላ ሌላኛው አሻሚ የሆነው የተገፋው የገዳይ እና ሟችን ታሪክ ማዳፈኑ ለምን ይሆን? ይህ በቀደሙት የኢህአዴግ አመራሮች አገልግሎት ላይ የዋለ አካሄድ አሁንም ለጥቅም መዋሉ ቢወቅጡት እንቦጭ አይነት ያስመስለዋል፡፡



ልዩ ዕትም

## ነፃነት እና ሰላም ምን እና ምን ናቸው

ነፃነት፣ ፍትህ፣ ፍቅር፣ መቻቻል፣ መከባበር፣ መነጋገር ለሚባሉት ቃላት ፍቺ በትምህርትዊ መንገድ የቃሉን ትርጉም መስጠት የሚያስፈልግበት ጊዜ ላይ እየደረስን መሆኑን የሚያሳይ ብዙ እውነቶችን ለትዝብት ተሰጥተዋል። ምክንያቱም መብቴ ነው፣ ምናገባኝና የራሳቸው ጉዳይ የሚሉ ቃላትን እንደ ቀልድ ‹‹መብት›› ሆነው እንዳረፉት ሁሉ፤ ይህን የሚል ሁሉ ትክክል እንደሆነና ተጠያቂ የሚሆኑበት አጋጣሚ የተፈጠረ እንደሆነም እንደተበደሉ እየተቆጠረ ይኸውም አድጎ የግድያ ሃሳብ ወደ መሆን ሲያድግ መሰረቱ ከዚህ የግዴለሽነት እና የሃላፊነት መግፋት እየተንከባለለ እንደነበረ ይዘነጋል፡፡ ኢትዮጵያ ድህነቷ የምግብ ብቻ አይደለም ዋስትና የሚያስፈልገው እየደረሰብን ላለው ማህበራዊና ምሁራዊ መዋቅር መንገራገጭ እንዲሁም የአስተሳሰብ መዝቀጥ ራሱ ድህነቷ ነው ፤ለሁሉም ውድቀት ምክንያት መሆኑ አጠያያቂ ሊሆን አይገባልም። ስንት ዜጋ መንገድ ላይ የወደቀን ሰብአዊ ፍጡር አልፎ መሄድ የህግ ተጠያቂነት እንዳለው ያውቃል፤ አንድ ሰው የሌላኛውን ከራስ ሌላ የሆነ አካል ህይወት ላይ የማጥፋትና የማኖር መብት ሊኖረው ይቅርና የራሱን ህይወት እንኳን ለማጥፋት መሞከር በራሱ የህግ ተጠያቂነት እንዳለው የማያውቁ ዜጎች መበራከት ለሃገር፣ ለመንግስት መልካም አስተዳደር እና ለህብረተሰብ ሰላማዊ አኗኗር እድገት እና ብልጽግና አንዱ የዝናቡ አንጠባጣቢ ሽንቁር ነው።

በአለም ላይ በሰላም ማስከበር ሚናዋ የገነነችዋ ኢትዮጵያ ለራሷ መሆን ያቃታት ለምንድነው? ጥል፣ ተንኮል፣ ሽኩቻ እና አመፅ ሁልጊዜም ራሳቸውን አዋቂ ነኝ ባሉ ምሁራን አነሳሽነት ወይም በባለስልጣናት መካከል እና ምክንያትነት ህዝብ ያልቃል የሰው ልጅ ደም በከንቱ በግፍ ይፈሳል። ሰላም ማጣት ችግሩ ለሌላ ምስቅልቅል መትረፉ ነው። ዘወትር የሚጠየቀው በዜጎቿ መካከል ፍትህን ማስፈንና ፍትሃዊ የሆነ የሃብት ክፍፍል እንዲኖር የማድረግን ዋስትና የሚሰጥ ብቻም ሳይሆን ሰሚም ተግባሪም እንዳይኖር ያደርገዋል። የስልጣን ሽኩቻው እና የኢኮኖሚ አቅሟ ዝቅተኛ በሆነበት ሃገር ውስጥ ሰላም ምንድነው? ሰላም ዋጋው ከደም ግብር በኃላ ‹‹አሃ›› በሚባልበት ሃገር ሰላም ዋጋ እና ክብር ይኖራታል የሚለው አሳሳቢ ነው። ዴሞክራሲስ ምንድነው ህዝብን በጭንቀት እና በሰቀቀን ማኖር፤ የስልጣንን ወንበር ለማግኘት አልያ የፖለቲካ ቁርሾን ለመወጣት የህዝብ ስሜት እና ኑሮ ላይ ተጨማሪ እዳ የሞት ዜናና፣ የመንግስት ግልበጣ ወሬን መስማት? ምዕራባውያን አፍሪካን ለመቀራመት አንድ ስብሰባን አድርገው ሙሉ አፍሪካን በአጭር ጊዜ ለአንድም ጊዜ በአፍሪካ ጉዳይ ሳይጣሉ ተከፋፍለው መቶ አመታትን ገዝተዋል። ለአፍሪካ ያደሉት የሴራ የእርስበእርስ ግንኙነት የቤት ስራ እስር አህጉሪቷ ሰርታ መጨረስ እና ወደ ቀጣይ ምዕራፍ ማለፍ አቅቷት ሌላ መቶ አመታትን ትዳክራለች፤ ትታትራለች፤ ትደክማለች ወይ ፍንክች መልስ የለም። ኢትዮጵያም የዚሁ ገፈት ቀማሽ ሆና አለች። መፅናኛ እንዲሆን በአለም ላይ የሰላም ሃሳቡ እንዳላት ከሌላው ጎልታ በሰላም ማስከበሩ ስራ ራሷን ለሞት አሳልፋ የፊቱን መስመር ይዛለች። እንደ ህዝብ በወል የቀረ የጋራ ማንነት ቢኖር ለሌሎች ለባዕዳን ማዘን እና ስለባዕዳን ሲሆን ያለ ሴራ እና ተንኮል በትጋት እና በትህትና ማሰብ ይመስል በሌሎች ሃገሮች ተሰደው ከሚኖሩ ዜጎች ውስጥ ኢትዮጵያውያን በስኬታማነት እስራኤላዊያንን አስቀድማ የሚበለፅጉ ዜጎች ያሏት ግን ድሃ ሀገር ነች፡፡ ይህ ደግሞ ህዝብ አቅም ቢኖረውም እንኳን ስርዓቶች ሁሉ ምቹ ስላልሆኑ እራሱን እና ሃገሩን ለማሳደግ መስራት አዳጋች ሆኖበታል።

## ስርዓት ሲባል

የህዝብ ንቃተ ህሊና ላይ የሚሰራው ስራ ትኩረት እየተሰጠው እስካልሆነ ድረስ ግን አሁንም ቢሆን ወታደሮችና ባለስልጣናት መምህራና ተማሪዎች ሁሉም አካላት ለድርጊቶቻችው ያለባቸውን ማህበራዊ እና ህጋዊ ተጠያቂነት ካለው ነባራዊ የመረጃ ብዝሃነት አንፃር የጠራ አይሆንም። በመሆኑም እንደ ሃገር ሌሎች ሃገሮች እንደሚያደርጉት ስለ ሃገር ማሳወቅ፣ ማንቃት እና የመሰረታዊ ግንዛቤዎችን ደረጃ በመደበኛው ነዋሪ የህብረተሰብ አካል ውስጥ ተቀራራቢ ማድረግ እስካልተቻለ ድረስ አሁንም ቢሆን በጠረጴዛ ዙሪያ ተቀምጦ የመወያየት አጋጣሚን መስጠት ጉንጭ አልፋ ልፋት ይሆናል፡፡ የቆጡን አወርድ ብላ እንዲሉ አንዱን ጉዳይ ከግብ ለማድረስ እና ለማግኘት ዋጋ ከሚፍለውን ሌላውኛውን ጉዳይ ጋር ሚዛን ላይ አስቀምጦ የሚበልጠውን ቀድሞ ማስተዋል ብሎም ሁለቱንም ደግሞ ላለማጣት ማመዛን ይገባል። ዴሞክራሲ ህዝቡ ራሱ ዲሞክራት ሆኖ ከማምጣት ይልቅ በጉልበት የብዙሃንን ደም በማፍሰስ የሚመጣ ከሆነ ምኑ ላይ ነው ዋጋው? ህዝብ በአግባቡ የሚተዳደርበትን ስርዓት ለማግኘት ብዙ አመታትን ከባዕዳን እና ከራሱ እኩራን አካላቱ ጋር ሲታገል ሲሞት ኖረ አሁንም ይሄው የሞት እና እንግልት ጉዞ ማብቂያ ያጣ ይመስላል። አሁንም ደም መመለስ፣ አሁንም ስልጣንን በሽፍትነት አልያም ሃሳብን በግድያ እንዲቀበሉ የማድረግ ሂደት አልቆመም ማቆሚያውም ጭላንጭል የለውም!

> ዶሮው ወይስ እንቁላሉ እያሉ መልስ የሌለው ጥያቄን እየተጠያዩቁ ጊዜን አላግባብ ከማሳለፍ ባሉት በቂ የሆነ የሰው ሃይል፣ የምሁራን እውቀት እና የተፈጥሮ ሃብት ላይ በመመርኮዝ ለጊዜው እንዳይሆን አንዱን በእጅ ላይ ያለውን አቅም መጠቀም የማያዳግም ውሳኔን ይፈልጋል

ምሁራኑ በራሳቸው አማራሪ ሆነው ያልተማረው ህብረተሰብ ቀድሟቸው እጅጉን የተረጋጋ ሆኗል። በአሁኑ ወቅት ሁኔታዎችን እያጮሁ እና እያግለበለቡ አልያም እያነሳሱም ጭምር የአመፅ እና የብጥብጥ ምክንያት መሆናቸው ሃቅ ነው። ምንም እንኳን ምሁራን ሁሉ ይህን ባያደርጉ አበጣባጮቹ ግን በአብዛኛው ምሁራን ናቸው። ይህች ሃገር የዘቀጠችበት በርካታ ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊና ስነልቦናዊ ችግሮችን መውጫ መንገድ ከመጠቆም ይልቅ አመፁ የሚባባስበት እና ብሶት፣ ቂም በቀል እና የጨለማ መንገድን በመጠቆም እና በመምራት ፊት አውራሪ ሆነዋል። ያልሆኑትም ደግሞ ያላቸውን የእውቀት ማህደር የግል ህይወትን ማበልፀጊያና የስልጣን መወጣጫ መንገድ ከማድረግ ባለፈ ያለውን የአላዋቂነት እና የመሃይምነት ጥላ ገልጠው ለማሳወቅ ያላቸው ቸልተኝነት የተለየ ክብርም ሆነ ተፅዕኖን የመፍጠር አቅም ነስቷቸው ተሰሚነትን አጥተዋል። ይሄን ደግሞ መስበር እና በእውቀት እና ምክንያታዊነት ላይ የተመሰረተ የውይይት እና የሃሳብ ልዕልናን ዋጋ የሚሰጥ ህብረተሰብ መፍጠር ይገባል ይቻላልም።

ሃገሪቷ ፖለቲካዋ በሴራ እና በመጠላለፍ ላይ የተመሰረተ መሆኑን ተቃዋሚውም ይሁን ባለስልጣኑ በተለያዩ ጊዜያት ያመኑት ሃቅ ነው። ሁሉም ነገር ቀጥታ ተሳታፊነትን እስካልጠየቀ ድረስ በግዴለሽነት የሚተገበርበት ሁኔታ ብዙ ነው። ለዚህም ምሳሌ የሚሆነው የሚድያዎቻችን ትጋት ነው። ሶስት ቀናትን ሁሉ መዝናኛ በሚሆኑ የመሳሪያ ሙዚቃዎችና የበለው በለው ዘፈኖች ባዕድ ጠላት እንደወረረ የሚያስመስል ድባብ ፈጥረዋል። ህዝብ ሰዎች በመሞታቸው ማዘኑ አይቀሬ ነው ሆኖም ደግሞ ፖለቲካውንም ደግሞ እየኖረው ስለሆነ አካሄዱ ለመገመት አይከብደውም። በተለይም ደግሞ የመፈንቅለ መንግስትነቱን ነገር!

ዶሮው ወይስ እንቁላሉ እያሉ መልስ የሌለው ጥያቄን እየተጠያዩቁ ጊዜን አላግባብ ከማሳለፍ ባሉት በቂ የሆነ የሰው ሃይል፣ የምሁራን እውቀት እና የተፈጥሮ ሃብት ላይ በመመርኮዝ ለጊዜው እንዳይሆን አንዱን በእጅ ላይ ያለውን አቅም መጠቀም የማያዳግም ውሳኔን ይፈልጋል። ማን ይህን ሽንቁራም ጣሪያ ይቀይረዋል በመባባል እርሱ እነርሱ እነእርሷ ላይ ከተሆነ ግን ከብሄራዊ ሃዘን ቀናት በኃላ የቀደመው ድህነት፤ የቀደመው እንዝልሃልነት፤ የቀደመው ሞት የመለማመድ ሂደት የቀደመው ምናገባኝ ይቀጥላል፡፡ ጣሪያው በትብብር ሲቀየር ግን የቤቱ መሰረት ቤቱን ለምፅአት የሚያቆየው በመሆኑ በትብብር ብቻ ሁሉም ቀላል ይሆናል። ሃገሪቷ ቅጥ ያለው የፍትህ ሥርዓት፣ ተጠያቂነት እና የሃገር ወዳድነት ስሜት ያለው በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ መኩሪያ የግብር ስርዓት፣ በህብረተሰቡ ውስጥ መጠነ ሰፊ የንቃተ ህሊና ስራ ቀዳዶቹን በድህነት ወቅት ይደፍናሉ ይሄ ደግሞ በጊዜ ሂደት መበስበሱ እየባሰበት የሚሄደውን ለመድፈን መንግስታዊ ስርዓትን መቀየር ያሻል።





# መፈንቅለ መንግስት ወይስ!?



ተስፉ (ኢትዮጵያ) አልታሰብ

በቅርብ ዓመታት ውስጥ ያስተዋልነው የኢትዮጵያ ዴሞክራሲ ሂደት ውስጥ ዴሞክራሲ፤ ህግ፤ እና ቅርቅ ፍቺ ማድረጋቸውን ነው። ዴሞክራሲ በምንም ሁኔታ ብቻውን መቆም አይችልም ህግና ርትእ ያስፈልገዋል፡ ፡ የዴሞክራሲ ልክና ልጓም ሊበጅለት ይገባል፡ ፡ የለውጡ መንግስት አዲስ መንገድ ቀይሶ ለተበደሉ ዜጎች የፖለቲካና የመናገር ነፃነት ምህዳር አስፍቶ መክፈቱ ሊመሰገን ይገባል፡ ፡ እስረኞች መፈታታቸውም፤ፖለቲከኞች ወደ አገራቸው ገብተው እንዲታገሉ መደረጉም እሰይ የሚያስብል መልካም ድርጊት ነው። ዛሬም በአገራችን በተለያየ ፖለቲካዊም ይሁን ህጋዊ ምክንያት የታሰሩት ወንድሞቻችን በእርቅ ከእስር ነፃ ሆነው ቢወጡ ሁላችንንም የሚያስደስት፤እንደ ሩዋንዳና ደቡብ አፍሪካ ህዝብ እርቅና ፍትህ አድርገን ሁላችን ለሀገራችን እንድንሰራ ቢደረግ አገር ተጠቃሚ ትሆናለች። የሰው ልጅ በመታሰሩ፤በመሰደዱ ማንም ኢትዮጵያዊ ደስተኛ አይሆንም። ሰዎች ተሳስተው ህግ ተላልፈው ሊሆን ይችላል። የማይሰራ አይሳሳትም። የሚሰራ ሰው ሲሰራ ስህተት መስራቱ አይቀርም።

በቅርቡ በባህርዳርና በአዲስ አበባ የተካሄደው የመፈንቅለ መንግስት ሂደት ሲታይ መፈንቅለ መንግስት ብሎ ብያኔ ለመስጠት ከሙያ አንፃር ሲታይ የሚከብድ ቢሆንም፤ ድርጊቱ ሲፈፀም እዛው ባህርዳር ከተማ ነበርኩ። ከፍተኛ የሆነ ቶክስ ከተማዋን አናወጠ። ዛሬ በአማራ ክልል ገንዘብ ያላቸውና የጦር መሳሪያ መግዛት የሚፈልጉ ሁሉ ሸምተዋል። ስለዚህ የባህርዳር ከተማ ነዋሪ የመፈንቅለ መንግስት የጦር መሳሪያ ድምፅ እንደ ወትሮው በንቀት ዝም ብሎት አለፈ። ምክንያቱም ማታ ማታ ባህርዳር የጦር መሳሪያ ድምፅ መስማት የተለመደ በመሆኑ ሁሉም ሰው የገመተው እነዚያ በገንዘባቸው መሳሪያ የገዙ ግለሰቦች መሳሪያቸውን እየፈተሹ ነው ብሎ አናናቀው። ሶስት የክልሉ ጉምቱ መሪዎቹ እየተሰዉ መሆኑን አላወቅም፡ ፡ በዚህም በዚያም የተሰለፉት ወታደሮች እርስ በርሳቸው እየተጫረሱ መሆኑን አልተረዳም፡ ፡ የአማራ ቴሌቪዥን ሰበር ዜናውን አስከተለ፡ ፡ ህዝብ ተደናገጠ። የአማራን ቴሌቪዥን ተጠ ራጥሮ ሌላውን ከፈተ፤ ተመሳሳይ ሰበር ዜና ነው። ለማንም ማመን የማይቻል ዜና ሆነ።

በሀገራችን መፈንቅለ መንግስት ያሁኑን ጨምሮ አራት ጊዜ ተካሂዷል። በአፄ ሀይለስላሴ ታህሳስ 1953 ዓ.ም ሁለቱ ወንድማማቾች መንግስቱ ንዋይና ገርማሜ ንዋይ ያስተባበሩት ሲሆን፤ በደርግ ዘመን በግንቦት 1981 ዓ.ም በአዲስ አበባና በአስመራ የተካሄደው በአዲስ አበባ ጄነራል መርእድ ንጉሴና ጓደኞቻቸው፤በአስመራ ደግሞ ጄነራል ደምሴ ቡልቱ እና ሌሎች ጓደኞቻቸው ያስባበሩት ፤ሶስተኛው በኢህአዴግ ጄነራል ተፈራ ማሞ እና ጄነራል አሳምነው ፅጌ ያስባበሩት የተባለው መፈንቅለ መንግስት ሲሆን፤ የመጨረሻው ደግሞ ሰኔ 15 ቀን 2011 በክልሉ የፀጥታ ሀላፊ በጄኔራል አሳምነው ፅጌ በባህርዳር የተካሄደውን ያካትታል። በታሪክ እነዚህ አራቱ መፈንቅለ መንግስት ሙከራዎች ሁሉ ያለ ውጤት በሰብአዊና ኢኮኖሚያዊ ኪሳራ የተጠናቀቁ ከንቱ ሙከራዎች ብሎ ታሪክ በደማቅ ቀለም መዝግቧቸዋል።

ከሁሉም መፈንቅለ መንግስት ሙከራዎች የተሻሉ እና ቢያንስ ለመፈንቅለ መንግስት መደረግ ምቹ ሁኔታዎች ነበሩዋቸው የሚባሉት፤በአፄ ሀይለስላሴ ታህሳስ 1953 ዓ.ም እና በደርግ ዘመን በግንቦት 1981 ዓ.ም በአዲስ አበባና በአስመራ የተካሄዱት ናቸው። ምክንያቱም በወቅቱ የነበረው የህዝብ ብሶት እና የመንግስታቱ ፀረ- ዴሞክራት ከመሆናቸው አንፃር መንግስታቱን ለመለወጥ የምርጫ አማራጭ ስላልነበራቸው መፈንቅለ መንግስት ባይሳካም ሞክረዋል። ሌሎቹ በኢህአዴግ ዘመን የተካሄዱት ሁለቱ፤ ለስም ካልሆነ የመፈንቅለ መንግስት ሙከራ ለማለት ብዙም የማያስደፍሩ አካሄዶች ናቸው።

የአሁኑ የሰኔ 15 ቀን 2011 ዓ.ም ተካሄደ የተባለው መፈንቅለ መንግስት አጠቃላይ ሂደቱ ሲታይ በአንድ ሀገር እውነተኛና ስልጡን ዴሞክራሲ ጅምር በሚታይበት ወቅት ፤በአንድ ክልል ላይ ብቻ ታጥሮ የሚደረግ መፈንቅለ መንግስት ፈፅሞ ሊኖር አይችልም። ከሆነም ለትርምስና ለብጥብጥ በር የሚከፍት እንጂ የመንግስት ለውጥ ለማምጣት የሚያስችል አይደለም። የመፈንቅለ መንግስት ሙከራ የሚል ስያሜ ያገኘው ድርጊት በተመለከተ እዛው ባህርዳር ላይ ከተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎች ጋር በጉዳዩ ላይ ውይይት አድርጌበት ነበር። አብዛኞቹ መፈንቅለ መንግስት እስከ ማድረግ ድረስ የተሄደበት ምክንያት የባህርዳር ነዋሪዎች የጠቀሱልኝ በሀገራችን አሁን ያለው ጫፍ የረገጠ ብሄርተኝነት መሆኑና ብሄርተኝነት ከሚገባው በላይ በመለጠጡ ምክንያት የመጣ ነው ብለዋል። ነገም ይላሉ የባህርዳር ነዋሪዎች ይህ ጫፍ ረገጥ የሆነውን ብሄርተኝነት ከፖለቲካችን እስካላራቅነው ድረስ ወይም በሂደት ማርገብ ካልተቻለ በሌሎችም ክልሎች ላይ ተመሳሳይ ድርጊት ሊቀጥል እንደሚችል ጠቁመዋል።

በተጨማሪም የባህርዳር ነዋሪዎቹ እንደሚሉት ከሆነ መንግስት ህዝቡንና ሀገሩን የመጠበቅ ግዴታ አለበት። መሪዎቹን መጠበቅ ሀላፊነቱ ነው። መሪዎች ያለ ስጋት በነፃነት ስራቸውን እንዲሰሩ የስለላ ተቋሙ ወትሮ ዝግጁ ሆኖ፤ በጀርባ በህዝብና በሀገር ላይ ሊደርስ የተቃጣውን አደጋ ቀድሞ አውቆ የሰው ህይወት ሳይጣፋ ድርጊቱን በማክሸፍ ሊጠብቃቸው ይገባ ነበር ብለዋል።

ለመሆኑ አንድ የስለላ ተቋም ሲደራጅ ዋነኛ አላማው በድንገት የሀገርን ደህንነተ እና የሀገር ፀጥታ እንዳይናጋ ቆቅ ሆኖ በመጠበቅ፤በሀገርና በህዝብ ላይ ሊደርስ የነበረውን አደጋ ቀድሞ በማሸተት ለመከላከል የሚያስችል መረጃና ማስረጃ በማሰባሰብ ለውሳኔ ሰጪ አካላት አደራጅቶ ማቅረብ ነው። የመረጃ ተቋሙ መንግስታዊ ካልሆኑ ወንጀልና ከሽብር ድርጅቶች የሚመጣው ስጋት ጨምሮ መጠነ-ሰፊ የኮንትሮባንድ፣ የሙስና፣ የገንዘብ አጠባ (money laundering)፣ የድንበር-ዘለል ሽብር፣ የሐይማኖታዊ አክራሪነት፣ የሕገ ወጥ የገንዘብ ፍሰት፣ የድንበር ተሻጋሪ ወንጀል፣ የበይነ-መረብ ወይም የኮምፒውተር ወንጀል ወዘተ ጉዳዮች ላይ ጥብቅ ክትትል የሚያደርግ ተቋም ነው።

▶

**የሰኔ 15 ቀን 2011 ዓ.ም ተካሄደ የተባለው መፈንቅለ መንግስት አጠቃላይ ሂደቱ ሲታይ በአንድ ሀገር እውነተኛና ስልጡን ዴሞክራሲ ጅምር በሚታይበት ወቅት ፤በአንድ ክልል ላይ ብቻ ታጥሮ የሚደረግ መፈንቅለ መንግስት ፈፅሞ ሊኖር አይችልም። ከሆነም ለትርምስና ለብጥብጥ በር የሚከፍት እንጂ የመንግስት ለውጥ ለማምጣት የሚያስችል አይደለም**

# ልዩ ዕትም



የአንድ ሀገር የስለላ ተቋም በሀገርና በህዝብ ላይ በድንገት ችግሮች ከተከሰቱ፣ ከምንም በፊት በሙያው ተጠያቂ የሚሆነው ድንገቴን (Surprise) ያስተናገደው የስለላ ተቋም ሀላፊነቱን መውሰድ ግዴታው ስለሚሆን ነው። ምክንያቱም በኢንተሊጀንስ መዝገበ ቃላት (Dictionary) ውስጥ ድንገተኝነት (Surprise) የሚል ቃል ስለሌለ ሀገሩን ከድንገተኛ ጥቃት አስቀድሞ መከላከል ያልቻለ የስለላ ተቋም የስለላ ተቋም ሊባል አይችልም። ይህን ባለማድረጉም ቅድሚያ ተጠያቂነት ወደ ተቋሙ ይመጣል። ብዙ ጊዜ የተለያዩ የስለላ ተቋም የሚመሩ ሀላፊዎች እነርሱ ሳያውቁት በድንገት  በሀገር ላይ አደጋ ከደረሰ በራሳቸው ፈቃድ ስልጣናቸው ሲለቁ እንመለከታለን። ይህ የሚያሳየው የስለላ ተቋም የድንገተኝነት አደጋ ዝም ብሎ በፀጋ የሚቀበል ተቋም ስላልሆነ ነው። ታድያ የሀገራችን የስለላ ተቋም ይህን ተራ ከፕሮፌሽናል ውጪ ሆኖ የተደረገውን መፈንቅለ መንግስት መረጃ ነበረው? ወይስ እንደ ማንኛውም ህዝብ በሚድያ በድንገት አዳመጠ? መልስ እንጠብቃለን።

ዛሬ በሀገራችን እንደ ከተማችን የመንደር እድሮች ቁጥራቸው የበዙት 108 ፓርቲዎች (ካልጨመሩ) አንዱ ፓርቲ ካንዱ የሚለየው በያዙት የብሄር ታርጋ እና ስያሜ እንጂ ለህዝብ እናመጣዋለን በሚሉት ዴሞክራሲ አይደለም። ማንም ያምጣው የሚመጣው ዴሞክራሲ ምንም ልዩነት የለውም። ዴሞክራሲ አንድ ነው። በህገ-መንግሥቱ አንቀፅ 29 ‹የአመለካከት እና ሀሳብን በነፃ የመያዝና የመግለፅ መብት›› ከአንቀፅ አንድ እስከ ሰባት ድረስ ያለው መሠረታዊ ዴሞክራሲዊ መብቶች ውስጥ ማንኛውም ሰው የመሰላውን አመለካከት የመያዝ፣ ሃሳቡን የመግለፅ በቃልም ሆነ በጽሁፍ  ወይም በህትመት ፣ በሥነ ጥበብ መልክ ወይም በማንኛውም ማሰራጫ ዘዴ፣ ማንኛውንም ዓይነት መረጃና ሀሳብ የመሰብሰብ፣ የመቀበልና የማሰራጨት ነፃነቶች  መብት እንዳለው ይገልፃል። በቃ የዴሞክራሲ መገለጫዎች እነዚህ ናቸው። ፓርቲዎች ቢበዙ ከዚህ በላይ ስለ ዴሞክራሲ የሚጨምሩት የለም።

በዚህ ዘመን ማንንም ማሸነፍ የሚቻለው በሀሳብ እንጂ፣የጦር መሳሪያ ታጥቆ ሌሎችን በመግደል አስፈራርቶ ማሳመን አይደለም። ያሁኑ መፈንቅለ መንግስት ፈፃሚዎች የሚያሸንፍ ልእለ ሀሳብ እንዳጡ ያሳያል። ከአመት በኋላ በሚደረገው ምርጫ አሁን በጠመንጃ ያሸነፏቸውን ወንድሞቻቸውን ሊያሸንፉ የሚችሉበትን ጥበብና የአላማ ዝግጅት ቢያደርጉ መገዳደር ይችሉ አልነበር?

የሀገራችን ምርጫ ቦርድ እንደ ሩዋንዳ፣ደቡብ አፍሪካ እና ሌሎች አገሮች ካሁን በኋላ ፓርቲዎች በብሄርና በሀይማኖት ማደራጀት የሚከለክል ህግ ቢያወጣ ከመቶ በላይ ፓርቲዎች ከምዝገባ ይወጡ ነበር። አገርና ህዝብ እውቀትና ሙያ ባላቸው የመምራት፣ የአስተዳደር ሙያ ብስለት ባላቸው መሪዎች መመራትም ትችል ነበር። አሁን ግን ከእውቀት እና ከሙያ በላይ በብሄር ተዋፅኦ አገርን ለመምራት የሚያስፈስፍ ሀይል ባለበት ሁኔታ፣ አገር እውቀት ባለውና በህዝብ በተመረጠ ሳይሆን የብሄር ውክልና ብቻ የፖለቲካ ስልጣን የመጨረሻው አማራጭ ሆኖ የሚያገለግል ከሆነ ሰነባበተ፣

በብሄር መደራጀት ሞራላቸው ያልፈቀደ በርካታ የሀገሬ ምሁራን ለሀገራቸው ማበርከት የሚገባቸውን እንዳያበረክቱ ከመድረኩ ርቀው ተቀምጠዋል። ተገልለዋል። በዚህም አገር ወደ ድህነት እና ወደ ጉስቁልና የውርደት ቁልቁለት ስትወርድ፣በሀሳብ ሳይሆን በመሳሪያ አፈሙዝ የሚመካ ሀይል ስልጣን ሲይዝ ፣በወገኑና በወንድሙ ለስልጣን ሲል ብቻ ቃታ ስቦ ሲገድል ማየት ወዴት እየሄድን ነው ያስብላል። ጠመንጃ እንጂ ምሉእ ሀሳብ የሌላቸው ግለሰቦች፣ አገርና ህዝብ ከዴሞክራሲ ብልፅግና ማማ ወደ ላይ ከፍ ብሎ ሲመነደግ ማየት አልወደዱም።

ሀገራችን ፖለቲካ መጫወት ከጀመረች ቆየች፣ ቅን ፖለቲካው ግን ገና ወደ ውስጣችን አልዘለቀም። ወደ ፊት መሄድ ትተን ቀኝ ኋላ ዙር ተብለን ወደ ከፋው መንገድ ተመልሰናል። የንጉሱ ስርዓት ማብቂያ ላይ ብቅ ብቅ ማለት የጀመሩት ብሄር የሌላቸው ህብረ ብሄር የፖለቲካ አቀንቃኝ ድርጅቶች፣ለአንድ ብሄር ሳይሆን ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብ ፖለቲካዊ፣ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ጥቅም ለመታገል የተደራጁና አስተሳሰባቸው አላማቸው ብሄር ዘለል ፓርቲዎች ነበሩ። ፖለቲካ ፓርቲዎቹ ብሄር ስላልነበራቸውም በቁጥር አነስተኛ በአላማም ብዙ የማይራራቁ ነበሩ። ዛሬ ግን በአገራችን በብሄራችን ልክ የፖለቲካ ፓርቲ ካባ እያሰፋን፣ለጦርነት ውረድ እንውረድ ተባብለን ቁልቁል ወረድን። በወገናችን ላይ አረመንያዊ ድርጊት ለመፈፀም እየተንደረደርን የምንጓዝ አስገራሚ ዜጎች ሆንን። ሁሉም ነገር ከኛ መፈጠር በኋላ በተጣበቀን የመግባቢያ ቋንቋችንን ብሄር የሚባል መለያያ ፈጥረንበት ፣የግጭትም ምንጭ አደረግነው፣

የዛሬ 45 አመት በ1960ዎቹ በኢትዮጵያ ፖለቲካ እንቅስቃሴ ላይ የነበሩ የኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲዎች እንቅስቃሴ በጥልቀት ስንመረምር ፓርቲዎቹ የትግላቸው መነሻ የብሔር ጥያቄ ሳይሆን የመሬት ላራሹ ፣የዴሞክራሲያና የመደብ ጥያቄ ነበር። እነዚያ ፓርቲዎች ራሳቸውን በጭራሽ በብሄር አላደራጁም። የመሰረቱት ፓርቲም ዴሞክራሲያዊ የሚል ቅድመ ቅጥያ በጭራሽ አልጨመሩም ነበር። ከዚያ ይልቅ ሕብረተሰባዊ፣ አብዮታዊ፣ ወ.ዘ.ተ የሚሉ ቃላትን ተመራጭ ያደርጉ ነበሩ። የዋና ዋናዎቹ ፖለቲካ ፓርቲዎች ስያሜ ብንመለከት፣ የመላው ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ (መኢሶን)፣ አብዮታዊ ሰደድ፣ የወዛደር ሊግ (ወዝሊግ)፣ የኢትዮጵያ ጭቁኖች አብዮታዊ ትግል (ኢጭአት) እና ማርክሳዊ ሌኒናዊ ሪቮሊሽናዊ ድርጅትን (ማሌሪድ)፣ እንዲሁም እነዚህ አምስት ድርጅቶች በጋራ የመሰረቱትን የኢትዮጵያ ማርክሳዊ ሌኒናዊ ድርጅቶች ህብረት (ኢማሌዲህ) እና የኢትዮጵያ ህዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲን (ኢህአፓ)  እናገኛለን።

በአሁኑ ሰአት በሀገራችን ያለው ሕገ-መንግስቱ መሰረት “የሕዝብ ሉዓላዊነት” የሚለው መርህ በተግባር ሲታይ “የብሔር ሉዓላዊነት” ነው ያለው። ምክንያቱም፣ የኢትዮጲያ ሉዓላዊ ስልጣን ባለቤቶች “የኢትዮጲያ ብሔሮች፥ ብሔረሰቦች፥ ሕዝቦች” እንጂ የሀገሪቱ ዜጎች አይደሉም። ዜጎች በፈለጉበት ቦታ ተንቀሳቅሰው መስራትና መኖር ያልቻሉት፣አሁን ያሉት ክልሎች የዜጎች ሳይሆኑ የብሄሮች ስለሆኑ ነው። ኦሮሞ ከሶማሌ የተፈናቀለው የህዝብ ሉአላዊነት ባለመከበሩ ነው። ትግራይ ከአማራ የተፈናቀለው ከህዝብ ሉአላዊነት ይልቅ የብሄር ሉአላዊነት አስተሳሰብ በጣም ስለገዘፈ ነው። በሌሎችም የሆነው የብሄር ሉአላዊነት ያመጣው ጦስ ነው። ይህ መርህ እና አካሄድ ፓርቲዎች በብሄራቸው ተደራጅተው እንዲታገሉ በር የከፈተም ነው። ከተቀሩት የሕገ-መንግስቱ መሰረታዊ መርሆች ጋርም ይጋጫል የሚል እምነት አለኝ። በመሆኑም፣ ባለፉት አመታት ከሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብት፣ ከመንግስት አሰራርና ተጠያቂነት፣ ከሕገ-መንግስቱ የበላይነት አንፃር ለተፈጠሩ መሰረታዊ ፖለቲካዊና አስተዳደራዊ ችግሮች ዋና መነሻ ምክንያት ነው የሚል ድምዳሜ መስጠት ያስችለናል። በኢትዮጵያ ሥጋት ከሆኑትና የአገሪቱን አንድነት እየተፈታተኑ ከሚገኙ ዋና ዋና ጉዳዮች አንዱና የመጀመሪያው የብሔር ማንነት ከሚገባው በላይ እንዲለጠጥ በመደረጉ ነው። በባህርዳር የተደረገው መፈንቅለ መንግስት ብሄርተኝነት ከሚገባው በላይ ለጥጠው የተመለከቱ የፈፀሙት ድርጊት ነው። ምክንያቱም መፈንቅለ መንግስቱ በምን ሂሳብ ነው በአንድ ክልል ተካሂዶ ሊሳካ የሚችለው? የመፈንቅለ መንግስት ፈፃሚዎች አላማቸው ቢሳካ ክልላቸውን ምን ሊያደርጉት ነበር? ከሌሎች አጎራባች ክልሎች ጋር ምን ሊያደርጉ አስበው ነበር? ፌደራል መንግስት ዝም ብሎ ይመለከት ነበር ወይ? ወይስ እንደ ሶሪያና የመን ህዝብ እዚያ እዚህ ሆነን ወደ ጦርነት ልንገባ ነበር? ጉዳዩ በጣም ከሚባለው በላይ አሳሳቢ ነው።

ከዚህ ቀደም የኢትዮጵያ ፖለቲካና ዴሞክራሲዊ አካሄድ ለምን ወደ ኋላ ተጎተተ ብሎ መጠየቅ የአባት ነው። ማንኛውም ነገር በሂደት እየተሻሻለ ሲመጣ እንጂ በሂደት እየተበላሸ ሲሄድ ማየት ባህሪያዊ አይደለም። እኛ አገር ዴሞክራሲውም፣ፖለቲካውም ንቃተ ህሊናውም የተገላቢጦሽ በሂደት ሊለወጥ የሚገባው ሳይለወጥ፣ይቅርታ የተደረገለት መልሶ ወደ ክፋትና ወደ አዘቅት መንገድ ሲኖግድ፣ምህረትን በሀጥያት ሲቀይር፣ፍቅርን በሀዘን ሲመልስ በተደጋጋሚ እያየን ነው።

ዛሬ ለአገራችን ሥጋት ከሆኑትና አንድነታችን ሊፈታተኑ ከሚችሉ ነገሮች አንዱ ምንድነው ብለን ብንነሳ በየቦታው ዜጎችን የሚያፈናቅል፣ ኢትዮጵያዊ ኢትዮጵያዊን የሚያፈናቅልበት፣ ግጭቶች የሚፈጠሩበት፣ አልፎ ተርፎም ሞትም ጭምር የሚከሰትበት ዋነኛ አጀንዳ ምንድነው ብንል ከማንነቶች ሁሉ የብሔር ማንነት ነው። ይህ የማንነትና የብሄር ጉዳይ ከፖለቲካዊ እንቅስቃሴአችን ቀስ በቀስ በሂደት ገሸሽ ማድረግና መለወጥ የኛ የኢትዮጵያውያን የቤት ስራ ሊሆን ይገባል። በባህርዳርና በአዲስ አበባ የተካሄደው መፈንቅለ መንግስት ጫፍ የረገጠ ብሄርተኝነት ወይስ የስልጣን ጥማት?  የሚለውን በቀጣይ በስፋት እንመለከተዋለን።

***ኢትዮጵያ በክብር ለዘላለም ትኑር***





# የተሰዉት የአዴፓ ጀግኖችና የማህበራዊ ሚድያው መዘጋት



ጃፈር ሰዩም

ጀግኖቹ ሳይነቁ አሸልበዋል፡፡ ሳይመለሱ ሄደዋል፡፡ የአማራ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ(አዴፓ) 4 ጠንካራ የማዕከላዊ ኮሚቴ አባላትን አጥቷል፡፡ የሀገር መከላከያ ሚንስቴርም ኤታማዦር ሹሙንና አንድ በጡረታ የተገለሉ አባሉን ተነጥቋል፡፡ ለሀገራቸው ያላቸው ገደብ የሌለው ፍቅር፣ ለአስርት አመታት የዳበረው የካበተ ልምዳቸው፣ በእሳት ውስጥ ተፈትኖ ያለፈው የአመራር ብቃታቸው እና ሀገራቸውን ለመለወጥ ያላቸው ጉጉት አብሯቸው ወደ መቃብር ወርዷል፡፡ ሀገራችን በአንድ ሌሊት ኤታማዦር ሹሟን፣ አንድ ትልቅ ክልልን እያስተዳደረ ያለ ዶክተርዋን፣ ህግ አዋቂ አቃቤ ህጓን፣ የክልል ጸጥታና ደህንነት ሀላፊ ከፍተኛ አመራር ጀነራሏን፣ የአደረጃጀት አማካሪ ካድሬዋን፣ ከረዥም አገልግሎት በኋላ በጡረታ የተገለለ የመከላከያ ባልደረባዋን እና በርካታ ዘብ የቆሙ ወታደሮችዋን አጥታለች፡፡ ሀገራችን እነዚህን ምሁራን፣ መኮንኖች፣ ካድሬዎችና ወታደሮች ለማስተማርና ለዚህ ታላቅ አመራርነት እንዲበቁ ሚልዮን ብሮችን አውጥታለች፡፡ ሞትም አሸንፏል!!

## የአዴፓ ነገር?!

በግልጽ እውነት መነጋገር መጀመር አለብን፡፡ ቀድሞውኑም "የአማራን ህዝብ የሚመጥን ቁመና የለውም" ተብሎ በአማራ ብሄርተኞች በብርቱ የሚተቸው አዴፓ "እንዲያውም ይለይላችሁ" ብሎ ቁልፍ ቁልፍ ሰዎቹን በሞትና በእስር አስረክቦ የበለጠ ተሽመድምዶና በድን መሆኑ ከታሪክ ተጠያቂነት የማያድነው ታሪካዊ ስህተት ነው፡፡ ላለፉት ወራት አማራ ክልል ላይ የታዩት የእርስ በርስ ፍጥጫዎች ወደ ጥሩ አቅጣጫ የሚመሩ ባይሆኑም በዚህ ፍጥነትና ሁኔታ ይደመደማል ብሎ የገመተ አልነበረም፡፡ ነገሮች እንዳልታሰቡ ሆኑና በብሄር ለሚታመሰው የኢትዮጵያ ፖለቲካ ከፍተኛ ቁጥር ላለው የአማራ ህዝብ ለውጡን ተከትሎ ጠንካራ አማራጭ ይሆናል ተብሎ የነበረው አዴፓ ተሰንጥቆ ተፍረከረከ፡፡ የአዴፓ መዳከም ክልሉ በፌደራሉ የመንግስት ስልጣን ላይ የሚኖረውን ሀይል ገደል ይከተዋል፡፡ የአዴፓ ካድሬዎች በየሚዲያው እየዛቱ ያለበትን መንገድ ለተመለከተ ሰው የአዴፓ መዳከም የት እንደደረሰ ግልጽ ይሆንለታል፡፡

የብሄር ፖለቲካ ከሚያንገሸግሻቸው ወገኖች ውስጥ ብሆንም የብሄር ፊደራሊዝሙ በስራ ላይ እስካለ ድረስ ሁሉም ድርጅቶች ጠንካራ አቅም ፈጥረው በሀገሪቷ መጻኢ እድልና እጣ ፈንታ ላይ የመወሰን ሚና ሊኖራቸው ይገባል ብዬ በጽኑ አምናለሁ፡፡ በተለይም የሀገሪቷ ትላልቅ ብሄሮች ውስጥ የሆኑት የኦሮሞና የአማራ ህዝብ ድርጅቶች ጠንካራ መሆንና በፌደራል መንግስቱ ውስጥ ጠንካራ ውክልና መኖር ለሀገሪቷ ሰላምና አንድነት እጅግ ወሳኝ ነው፡፡ አንዱ ባንዱ ላይ በድርጅትም ይሁን በሌላ መንገድ ሊፈጥር የሚሞክረው የበላይነት እንደ ሀገር ትልቅ ዋጋን እንደሚያስከፍለን ጥርጥር የለውም፡፡ በመከባበርና በመፈቃቀር ላይ የተመሰረተ እውነተኛ አንድነት ሀገራችንን ያጠነክራታል፡፡ በሴራ፣ በምቀኝነትና "በእኔ እበልጥ እኔ እበልጥ" ጨዋታ ውስጥ ከተገባ ግን አሸናፊ የሌለው ሁሉንም ተሸናፊ የሚያደርግ ጨዋታ ውስጥ መነከራችን አይቀሬ ነው፡፡

የኢህአፓ የሜዳ ትግል ወራሽ የነበረው ኢህዴን ፊቱን ወደ ብሄር ፖለቲካው አዙሮ እንደ አዲስ ፓርቲ ሲቋቋም ህወሃት ከማደራጀት ባለፈ የትግርኛ ስያሜን ጭምር እንደሸለመው ብዙዎች ልብ አላሉትም፡፡ "ብሔረ አማራ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ" ወይም በምህጻረ ቃል "ብአዴን" የሚለው ስሙን ለ2 አስርት አመታት ተጠርቶበት ነበር፡፡ ድርጅቱም ላለፉት አመታት የህወሃት ቀኝ እጅ በመሆን የአማራው ህዝብ እየደረሰበት ለነበረው ስቃይ ጀርባውን ሰጥቶ ለፈጠረው ህወሃት ማሸብሸብን መረጠ፡፡ ከአመራር አባሎቹ ውስጥ የተወሰኑት ከአማራው ጋር በብሄር አለመገናኘታቸው ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵያዊም ጭምር ያልሆኑ እንደነበሩበት የአደባባይ ምስጢር ነው፡፡ ህዝባዊ ግፊቱን ወደ ለውጥ ለመቀየር የብአዴን ከፍተኛ አመራሮች ሚና ቀላል አልነበረም፡፡ ህወሃትን ወደ መቀሌ በመመለሱ ሂደት ከኦህዴድ ጋር አብረው ግንባር ቀደም ሚናቸውን ከተወጡ በኋላ ከህወሃት ተጽዕኖ ተላቀው የአማራ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ(አዴፓ) ወደሚል ስም ቀይረው ለውጡን ወደፊት በመግፋት ላይ ነበሩ፡፡

## ፖለቲካዊ መፍትሄ-- ብቸኛው አማራጭ

የዛሬ ወር ገደማ የጠቅላይ ሚንስትሩ ጽ/ቤት መንግስት እየተካረረ የነበረውን የአማራ ክልል ፍጥጫ ለመፍታት የአዴፓና አብን አመራሮችን፣ የአማራ አክቲቪስቶችን እና ሌሎች ባለድርሻ አካላትን ያካተተ ውይይት ለማካሄድ ያደረገው ጥሪ ተቀባይነት አላገኘም ነበር፡፡ ሆኖም ከችግሩ አሳሳቢነት አንጻር ይሄ በቂ አልነበረም፡፡ የፌደራሉ መንግስት በአማራ ክልል ትጥቅ ለማስፈታት ያደረገው ተደጋጋሚ ሙከራ አለመሳካቱም በክልሉና በፌደራሉ መንግስት መካክል ያለውን ግንኙነት የማሻከር እድሉ ከፍተኛ ነው፡፡ የልዩ ሀይል ለማስልጠን በክልሎች መካከል የሚደረገው እሽቅድምድም ላይ ሰፊ ተሳትፎ እያደረገ የነበረው ክልሉ በፊደራል መንግስቱ ዘንድ በጥሩ እንዳልታየም ተመልክተናል፡፡

"በአዴፓ አመራሮች መካከል ፍጥጫን ያስከተለው ምንድነው?" የሚለውን መሰረታዊ ጥያቄ ከስር ከመሰረቱ ከመፍታት ይልቅ "የመፈንቅለ መንግስት ሙከራ"፣ "በመንግስት ምህረት የተፈቱ ሀገራቸውን የማይወዱ ሀይሎች የፈጸሙት ተግባር" ወዘተ እያሉ ስያሜ በመስጠት ለማለፍ መሞከር ለጊዜያዊ ፕሮፓጋንዳ ፍጆታ ይረዳ እንደሆን እንጂ በፍጹም መፍትሄ ሊሆን አይችልም፡፡ የፕሮፓጋንዳ ፖለቲካ ለደርግም አልጠቀመም፡፡ ለህወሃትም አልሆነም፡፡ አሁን በስልጣን ላይ ►

> የኢህአፓ የሜዳ ትግል ወራሽ የነበረው ኢህዴን ፊቱን ወደ ብሄር ፖለቲካው አዙሮ እንደ አዲስ ፓርቲ ሲቋቋም ህወሃት ከማደራጀት ባለፈ የትግርኛ ስያሜን ጭምር እንደሸለመው ብዙዎች ልብ አላሉትም፡፡ "ብሔረ አማራ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ" ወይም በምህጻረ ቃል "ብአዴን" የሚለው ስሙን ለ2 አስርት አመታት ተጠርቶበት ነበር



◀ ላለው ማዕከላዊ መንግስቱም አይጠቅምም። በአጠቃላይ ለሀገራችን ፈጽሞ አይጠቅምም፡፡ መፍትሄው አሁንም ውይይት ነው፡፡ በመነጋገር፣ በመመካከር በርካታ ችግሮች ሲፈቱ እያየን ነው። አሁንም በጦር መሳሪያ ከመነጋገር ይልቅ ቁጭ ብሎ በመነጋገር ፖለቲካዊ መፍትሄ መስጠት ብቸኛ አማራጭ ነው።

## ባልደራሱ

"የአዲስ አበባ ባላደራ ምክር ቤት" በሚል በባልደራስ የተቋቋመውን በአዲስ አበባ ጉዳይ የሚንቀሳቀስ የሲቪክ ማህበር አባላትን ጥያቄ ተቀብሎ ተወያይቶ ፖለቲካዊ መፍትሄ ከመስጠት ይልቅ የሰሞኑን አሳዛኝ ሁኔታ እንደመልካም አጋጣሚ በመቁጠር አባላቱን በጸረ ሽብር ህጉ መክሰስ መፍትሄ ሊሆን አይችልም። የአዲስ አበባን ጉዳይ በተመለከተ ጠቅላይ ሚንስትሩ ግልጽ ውይይት ማድረግ ያልፈለጉትስ ለምንድነው? የባልደራሱ አባላት "ውክልና አለን" የሚሉት ጉዳይ ላይ ብቻ ሁልጊዜ አወዛጋቢ አስተያየን ከመስጠት ይልቅ በሀገሪቷ ላይ እንደተነሱ ሌሎች ጥያቄዎች ሁሉ የባልደራሱም ጉዳይ ህዝብ በሚመለከተው መልኩ በግልጽ ውይይት እንዳይፈታ የተፈለገው ለምንድነው? ነገሮችን በሰከነ መልኩ በውይይት ከመፍታት ይልቅ እስርና ጸረ ሽብር ህጉን ያስታከከ ክስ የሄድንበትን መንገድ መድገም አይሆንብንም? ወይስ ልክ እንደ አማራ ክልል ፓርቲዎችና አክቲቪስቶች ጥሪ ተደርጎላቸው አሻፈረኝ ብለው ቀሩ? ብዬ እንደ አንድ ኢትዮጵያዊ እነዚህን ጥያቄዎች እጠይቃለሁ። አሁንም ቢሆን የእስር ቤት በሮች ተዘግተው የውይይት በሮች እስከመጨረሻው መከፈት አለባቸው፡፡ የለውጥ አመራሩን በህዝብ እንዲወደድ ያደረገውና በህዝብም እንዲከበር የሚያደርገው ይቅርታን፣ ፍቅርን፣ አንድነትን እና መደመርን መስበኩና በተግባርም ማሳየቱ እንጂ የቀድሞውን ስርአት በመድገም የተለየ ነገር ያነሳን ሰው ሁሉ አንገት እያነቀ ወደ ወህኒ መውሰድ አይደለምና ይህ አካሄድ ተጠናክሮ አመራሩንም ሆነ ሀገሪቷን ዋጋ ከማስከፈሉ በፊት በደምብ ይታሰብበት።

## ከግድያው በስተጀርባ

የከፍተኛ አመራሮቹን ግድያ ተከትሎ የሴራ ትንተና ውስጥ የተዘፈቀው ማህበራዊ ሚድያ በሰአታት ውስጥ የመቀጨት እድል አጋጥሞታል። ግድያውን አስመልክቶ ምንም አይነት የጠራ መረጃን ማግኘት አስቸጋሪ ነው፡፡ ጉዳዩን በቅርብ ርቀት የተከታተሉ ሰዎች እንኳ ግልጽ መረጃ የላቸውም። ባህርዳር ከፕሬዝዳንቱ ጽ/ቤት በቅርብ ርቀት ላይ የሚሰሩ ሰዎች እንኳ ስለጉዳዩ ያላቸው መረጃ ከአንድ ጥግ ወደ ሌላ ጥግ የሚጎተት ነው። ሁሉም እርግጠኛ ሆኖ የሚሰጠው መረጃ እርስ በርሱ የሚጣረስ ብቻ ሳይሆን አማካኝ ነገር የማይገኝበትም ጭምር ነው። ሁሉም የየራሱን ፍላጎት በሚያንጸባርቅ መልኩ መረጃን ይጎትታታል። እርግጠኛ ሆኖ ይተነትናል።

## የፌስቡክ መዘጋት

ፌስቡክ በርካታ ተንታኞች አሉት፡፡ ግድያውን ተከትሎ በርካታ መላምቶችን ከየአቅጣጫው ሲሰነዝሩ እየሰማን በነበረበት ወቅት መጀመርያ ማህበራዊ ሚድያው ተዘጋ፡፡ ወዲያውኑ ደግሞ የኢንተርኔት አገልግሎት በሀገሪቷ ሙሉ ለሙሉ ተቋረጠ። ተንታኞቹ የተወሰኑት ክመረጃና ማስረጃ የራቁ ብቻ ሳይሆን መያዣና መጨበጫ የሌላቸውም ጭምር ናቸው። እንደተለመደው ግጭትን የሚቀሰቅሱ ጽሁፎች፣ ጥላቻን የሚያበረታቱ ፖስቶቹ መለጠፍ ተጀመረው ነበር። ምንም እንኳ በማህበራዊ ሚድያው ሀላፊነት የማይሰማቸው ሰዎች ምክንያት የሀሰት ዜናዎችን(FAKE NEWS) በማሰራጨት ግንባር ቀደም እየሆነ በመምጣቱ ምክንያት ህዝብ ላይ እየፈጠረ የሚገኘው አለመረጋጋት ለመዘጋቱ ግንባር ቀደም ምክንያት መሆኑን መገመት ይቻላል። የማህበራዊ ሚዲያው መዘጋትም ህዝብ በቀላሉ መረጃ እንዳያገኝ አድርጓል። ሆኖም ብዙ ጊዜ ስለማህበራዊ ሚድያ ትኩረት የማይሰጠው ነገር የሀሰት መረጃዎችን በፍጥነት የማክሸፍ አቅሙን ነው፡፡ በርግጥ በተለያየ ዓለም የሀሰት መረጃዎች ከመክሸፋቸው በፊት በርካታ ጉዳቶች አድርሰው ተመልክተናል። በሀገራችንም ሀሰተኛ መረጃዎችን ተንተርሰው የደረሱ የተወሰኑ ጉዳቶችን መጥቀስ እንችላለን። የማህበራዊ ሚድያው መዘጋት ሀገሪቷን በማረጋጋት ላይ ቁልፍ ሚና ቢኖረውም ኢንተርኔትን ሙሉ ለሙሉ መዘጋት ግን ከኢትዮጵያችን ባይበልጥም ኢትዮጵያችንን ከባድ ዋጋ እንደሚያስከፍላት መረዳት ይኖርብናል።

ባለፈው ግንቦት ወር በ2ኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተና(ማትሪክ) ወቅት ማን እንደሆነ እና ለምን እንደሆነ ግልጽ ባልሆነ ምክንያት ኢንተርኔት ሙሉ ለሙሉ በመቋረጡ ሀገራችን በየዕለቱ 5 ሚልዮን የአሜሪካን ዶላር እያጣች መሆኗን ቢቢሲ የአማርኛው ድረ ገጽ አንድ ኢንተርኔት በተዘጋበት ወቅት ስታስቲክስ የሚሰራ ዓለም ዓቀፍ ተቋምን ጠቅሶ ዘግቧል። ገንዘቡ እጅግ ከፍተኛ ነው። በርካታ ስራን ያስተጓጉላል፡፡ ከሁሉም ከሁሉም በላይ ግን ስለሀገሪቷ የሚፈጥረው ምስል ከባድ ነው። በተለይም መዲናችን አዲስ አበባ የአፍሪካም መዲና እንደ መሆኗ በበርካታ ቱሪስቶች የመሳብ እድሏ ከፍተኛ ነው። በየቀኑ በሺ የሚቆጠሩ ቱሪስቶች ወደ ሀገራችን ይመጣሉ። ሌሎች በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች በተወዳጁ የኢትዮጵያ አየር መንገድም ሆነ በሌሎች ሀገራት አየር መንገዶች ተጠቅመው በሚጓዙበት ወቅት ለትራንዚት አዲስ አበባን ይረግጣሉ። እነዚህ ዜጎች በኤርፖርት ተርሚናል ውስጥ በመጀመርያ የዋይፋይ አገልግሎትን ይጠይቃሉ። በሀገሪቷ ኢንተርኔት እንደተቋረጠ ይነገራቸዋል፡፡ በዚህ ጊዜ መደናገጣቸው አይቀርም። ምን እንደተፈጠረም ይጠይቃሉ።

ነጮች አንድ ጊዜ በአዕምሯቸው የቀረጹትን ምስል ለዘመናት የማስቀረት ባህሪ አላቸው። በ77 ከተፈጠረው ድርቅ ጋር በተያያዘ ኢትዮጵያን አስመልክቶ የተሰራጩት ምስሎች በውጭ ዜጎች ዘንድ ዛሬም ድረስ ሀገሪቷን የድርቅ ሀገር እንድትመስል አድርጓት እንደነበር መረዳት እንችላለን፡፡ ስለሆነም ሀገሪቷ በእያንዳንዱ ምክንያት ኢንተርኔት ስታቋርጥ በአንድ የውጭ ዜጋ ዘንድ የተለየ ምስልን ፈጥሮ "ያቺ ኢንተርኔት የሌለባት ሀገር" የሚል መጥፎ ተቀጽላን ሊፈጥር ይችላል። በርካታ ምዕራባውያን የትኛውንም ሀገር ከጎበኙ በኋላ አስተያየት(review) የመጻፍ ልማድ አላቸው። ይህም የተመለከቱትን ለሌሎች ሰዎች አስተላልፈው ሌሎች ሰዎች አንድን ሀገር ከመጎበኛታቸው በፊት አንበው በተለያየ መልኩ እንዲዘጋጁም ያደርጋሉ። ስለሚሄዱበት ሀገር በሌሎች ሰዎች የተጻፉ ጽሁፎችን አንበው ሄደው የመጎብኘት ልማድም አላቸው። ስለሆነም ኢንተርኔትን የማቋረጥ ከባድ ውሳኔዎች በሚተላለፉበት ጊዜ የሀገሪቷን መልካም ገጽታ እንዳያበላሽ ጥንቃቄ ሊደረግበት ይገባል።

የሀገሪቷ ደህንነትና ጸጥታ ከዚህ የማይበልጥ ቢሆንም መልካም ገጽታችን ሳይበላሽ ማህበራዊ ሚድያን መዘጋት የሚቻልበትን መንገድ መቀየስ ይኖርብናል።

## ጥቂት መፍትሄዎች

መንግስት ኢንተርኔትን በፍጥነት መክፈት አለበት። ፌስቡክን ግን በኢትዮጵያ ምድር በአጭር ጊዜ ውስጥ መክፈት ፈጽሞ የማይታሰብ ነው። ሀገራችን በቋፍ ላይ ነች፡፡ ስለሆነም፦

1) ተጠያቂነት የሰፈነበት የማህበራዊ ሚድያ አጠቃቀም እንዲኖር ህብረተሰቡ ላይ የተለያዩ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችን መስራት። በፌስቡክ የሚለቀቁ መረጃዎችን ትክክለኛነት ማወቅ የሚቻልባቸውን መንገዶች፣ ሀሰተኛ መረጃዎችን እንዴት መለየት እንደሚቻል እንዲሁም በምን መልኩ ማስተላለፍ እንዳለበትና ተያያዥ ነገሮችን በተደራጀ መልኩ ተከታታይ ትምህርቶችን በሚድያዎች ያለማቋረጥ ህዝብን በማያሰለች መንገድ ማስተማር

2) ሀላፊነት የማይሰማቸውና ማንነታቸው የማይታወቁ (ፌክ አካውንቶችን) ኢትዮጵያ ውስጥ እንዳይከፈቱ ብሎክ ማድረግ፣ ከነዚህ ምንጮች የሚወጡ መረጃዎች ሀሰተኛ መሆናቸውን ህዝቡ እንዲያውቅ በተለያዩ መንገዶች ማሳወቅ፣ በተለይ ዘረኝነትን የሚሰብኩ አካውንት ባለቤቶችን በተለያዩ መንገዶች በማግኘት በህግ የሚጠየቁበትን መንገድ ማመቻቸትና በኢንተርፖልም ጭምር ተይዘው በህግ የሚጠየቁበትን መንገድ ላይ መስራት ((ያለምንም ማዳላትና የዘር ልዩነት))

3) የተለየ የኢንተርኔት ፕሮቶኮል(IP) ለድርጅቶች፣ ለዓለም ዓቀፍ ተቋማት፣ ሆቴሎች፣ የአየር ማረፊያዎችና ለሚጎበኙ ቦታዎች በመስጠት ስራ ሳይስተጓጎል የሌሎች ሀገር ዜጎች እንግዶቻችንን ሳይ ተጽዕኖ ሳይፈጠር ሀገሪቷን ማረጋጋት ይቻላል፡፡ ባንኮች የራሳቸውን የውስጥ ሰርቨር(local server)ና IP እየተጠቀሙ ስለሆነ የATM አገልግሎታቸው ሳይቆራረጥ እየተሰጠን ነው።

የማህበራዊ ሚድያው እያደገ ባለበት ፍጥነት እኛም በዚያ ፍጥነት አጠቃቀማችን ባለማደጉ ራሳችንንም ሆነ ሀገራችንን ዋጋ እያስከፈላት ይገኛል። ይህንን ኋላቀር አጠቃቀማችንንና አመለካከታችንን ለመቀየር መጠነ ሰፊ ስራ በእያንዳንዳችን ላይ ይጠብቀብናል።

**ቸር እንሰንብት!**

# ፆታን መሰረት ያደረገን ጥቃት ለመከላከል ሁላችንም የየድርሻችንን ኃላፊነት መወጣት አለብን

**ከእሸቱ ደስታ**

በሀገራችን በዲሞክራሲና በመልካም አስተዳደር ግንባታ እንዲሁም በሰብአዊ መብት አያያዝ ላይ ብዙ መስራትን ይጠይቃል፡፡ ይህንንም በሀገሪቱ በስፋት ለመስራት የመንግስት ሚና ከፍተኛ ቢሆንም የሲቭል ማህበረሰብ ድርጅቶች አጋርነት ደግሞ ቀላል አይሆንም፡፡

በዚህም መነሻ እ.ኤ.አ በ2002 የተመሰረተው ሀገር በቀል ድርጅት የሆነው ኢንሽየቲቭ አፍሪካ የበኩሉን ድርሻ ለመወጣት በማሰብ “እንነጋገር- እንወያይ” የሚል ፕሮግራም ቀርፆ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል፡፡ ይህም ፕሮግራም የሚደገፈው በሲዊዲን ኤምባሲ ሲሆን ሥራው የሚከናወነው ከአጋር ድርጅቶችና ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ጋር በመተባበር ነው፡፡

ፕሮግራሙ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ማህበረሰብ አባላትን (ተማሪዎች፣ መምህራን እና የአስተዳደር ሠራተኞች) እንዲሁም በየአካባቢ የሚገኙ ሴክተር መ/ቤቶች፣ የሃይማኖት ተቋማት፣ የሀገር ሽማግሌዎች፣ ታዋቂ ግለሰቦች፣ ህዝባዊ ማህበራትና የዕድር አመራሮችን የሚያሳትፍ ነው፡፡ የዚህ ፕሮግራም ትኩረት ስለ ሀገሪቱ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊና የአካባቢ ጉዳዮች ላይ ግልጽ ውይይቶችን በማካሄድ የዳበረ አቋም ያለው ማህበረሰብ መገንባት ላይ ነው፡፡

ይከእነዚህ ፕሮግራሞች አንዱ ከሻሎም ሂዩማኒቴሪያን ዴቬሎፕመንት አሶሴሽንና በፍቼ ከተማ ከሚገኘው ስላሌ ዩኒቨርሲቲ ጋር በመተባበር “ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት” በሚል ርዕስ ሰኔ 7 ቀን 2011 ዓ.ም በዩኒቨርስቲው የመሰብሰቢያ አዳራሽ የመጀመሪያው የፓናል ውይይት ተካሂዷል፡፡

በውይይቱ የተሳተፉት የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ አባላትን ጨምሮ ከኦሮሚያ ክልል ሰሜን ሸዋ ዞንና ከፍቼ ከተማ የሴቶች፣ የህፃናትና የወጣቶች ጽ/ቤቶች ተወካዮችን ባካተተ መልኩ ነው፡፡ በፓናል ውይይቱ የመነሻ ጽሁፍ ያቀረቡት ከዩኒቨርሲቲው የሶስዮሎጆ ዲፓርትመንት አቶ ብርሃኑ ጉዲሳ እና ከሻሎም ሂዩማኒቴሪያን ዴቬሎፕመንት አሶሴሽን አቶ ፈየራ አበራ ናቸው፡፡

የመነሻ ጽሁፍ አቅራቢዎቹ በሀገራችን ህገመንግስት የሴቶች እኩልነት የተረጋገጠ ቢሆንም በተግባር ግን ብዙ ይቀረዋል ሲሉ እነኚህ ባለሙያዎች ጠቅሰዋል፡፡ በማያያዝም ፆታዊ ጥቃት በዘር፣ በአካባቢ፣ በፆታ ሳይገደብ የማንንም መብት የሚጋፋ መሰረታዊ የመብት ጥሰት መሆኑን ገልፀው የትኛውም አይነት ጥሰት አካላዊ፣ ሥነ--ልቦናዊ፣ ፆታዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳት ያደርሳል ሲሉ አፅንኦት ሰጥተው ተናግረዋል፡፡

የዓለም ባንክ እ.ኤ.አ በ2019 ባወጣው ሪፖርት በዓለም አቀፍ ደረጃ ከ3 ሴቶች አንዳቸው እንዲሁም 35 በመቶ የሚሆኑት ሴቶች ከቤተሰባቸው ወይም ከቅርብ ሰዎች የአካላዊና ፆታዊ ጥቃት እንደሚደርስባቸው እንዲሁም 38 በመቶው የሚሆኑት በፆታዊ ጥቃት እንደሚሞቱ ከባለሞያዎች ገለፃ መረዳት ተችሏል፡፡

ባለሙያዎቹ በሀገር አቀፍ ደረጃ ከሴቶች ህፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር እ.ኤ.አ በ2011 በተደረገው ጥናት የተገኘውን መረጃም ለተሳታፊዎቹ ሲገልፁ 4617 የሚሆኑ ከትዳር አጋራቸው ጋር የተፋቱ ሴቶች ከባለቤታቸው ጋር አብረው ያፈሩትን ንብረት ለመካፈል አልቻሉም፡፡ 8655 የሚሆኑ ሴቶች ድብደባ፣ አካል መጉደልና ጠለፋ ይደርስባቸዋል፡፡ ከ50-60 በመቶ የሚሆኑት በህይወታቸው ውስጥ ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት መድረሱን ገልፀዋል፡፡

በኦሮሚያ ሰሜን ሸዋ ዞን ፖሊስ መምሪያ ባለፉት 9 ወራት በዞኑ ስር በሚገኙ 13 ወረዳዎች እና አንድ ከተማ አስተዳደር ውስጥ ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች ላይ ያደረገውን ባለሙያዎቹ ሲጠቁሙ አስገድዶ መድፈር 68፣ ጠለፋ 14፣ ያለ ዕድሜ ጋብቻ 26 እና የነፍስ ግድያ 26 እንደሆኑ ተናግረዋል፡፡

በዚህ የፓናል ውይይት ከተሳተፉት መካከል ጥቂቶቹ ያላቸውን አስተያየት ጠይቀን ያሉንን እነሆ፡-

ዶ/ር የሽመቤት ቦጋለ ይባላሉ፡፡ በፍቼ ዩኒቨርሲቲ የህዝብና የውጭ ግንኙነት ዳይሬክተር ናቸው ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶችን እንዴት መከላከል እና መቀነስ ይቻላል የሚል ጥያቄ አንስተንላቸው የሚከተለውን ብለውናል፡፡

“ሌላው ቢቀር በዞናችን ጥቃቱ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ እንጂ እየቀነሰ አይደለም፡፡ ጥቃቱን ለመቀነስ ህጉ አለ፡፡ ይህም እያለ ለውጥ አልመጣም፡፡ መፍትሄው ሁላችንም የራሳችንን ድርሻ ባለመወጣታችን ስለሆነ በዚህ በኩል ሰፊ የግንዛቤ ሥራ መስራት አለበት፡፡”

ሌላው የፓናል ውይይቱ ተሳታፊ በዩኒቨርሲቲው የአስተዳደርና ተማሪዎች ጉዳይ ም/ፕሬዝደንት የሆኑት አቶ አዱኛ መኮንን ሲሆኑ ፆታ መሰረት ያደረጉ ጥቃቶችን እንዴት ይገልፁታልና መፍትሄውስ ምን ሊሆን ይችላል የሚል ጥያቄ አንስተንላቸው ምላሻቸው የሚከተለው ነው፡፡

“ሴት እናት፣ ሚስት፣ እህትና ልጅ መሆኗ እየታወቀ ሴቶችን በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚና ማህበራዊ ረገድ የምንሰጠው ቦታ ዝቅተኛ ነው፡፡ በሀገራችን በአንዳንድ ቦታዎች ጠለፋን ባህላችን የሚያደርጉ ሽማግሌዎች አይጠፉም፡፡ በዚህም ጠለፋ ተካሂዶ ወደ ህግ ከመሄድ ይልቅ በዚያው እዚያው በሽምግልና ተዳፍኖ የሚቀረው ማሳያ ነው፡፡ ይህን ለመቅረፍ ኢንሽየቲቭ አፍሪካ እና ሻሎም ሂዩማኒቴሪያን ዴቬሎፕመንት አሶሴሽን ይዞት የመጣው ፕሮግራም በሰዎች አስተሳሰብና አመለካከት ላይ የመስራት ሁኔታ ላይ ያተኮረ ስለሆነ ዩኒቨርሲቲው በዚህ ረገድ ተባብሮ ለውጥ ይመጣል፡፡”

በዕለቱ በፍቼ ዩኒቨርሲቲ የ2ኛ ዓመት ተማሪ የሆነችው ሲቲና አደምንም አነጋግረን ነበር፡፡ እሷም በዚህ ጉዳይ ላይ የሚከተለውን አለችን፡፡

“በአብዛኛው ሴት ተማሪዎች ከገጠር የሚመጡ ናቸው ወንዱ በሴቷ ተማሪ ላይ የበላይነት ያሳያል፡፡ ጥቃትም ያደርሳል፡፡ በዩኒቨርሲተው ግቢ ከጥበቃው ጀምሮ በአንዳንድ መምህራን ሳይቀር ለሴቷ ተማሪ የመደገፍ ሥራ ከመስራት ይልቅ አትችልም የሚል አመለካከት ይታያል፡፡ ሌላው ቀርቶ በዩኒቨርሲቲው የሚገኘው ቤተመፃህፍት 24 ሰዓት ክፍት ቢሆንም ለሴቶች ከለላ የሚያደርግ ባለመኖሩ ወንዶች ተማሪዎች 24 ሰዓት ሲጠቀሙ ሴቶች ግን ከ5፡00 ሰዓት ያልበጠ አይጠቀሙም እነኝህ ችግሮች እንዲቃለሉ የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ በጋራ ትኩረት አድርጎ መንቀሳቀስ አለበት፡፡”

በፓናል ውይይቱ ወቅት ሌላው አስተያየት የሰጡት የፍቼ ከተማ ሴቶች፣ ህፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ጽ/ቤት ተወካይ የሆኑት ወ/ሮ ጠይም ልኬ ሲሆኑ እሳቸውም እንዲህ ብለዋል፡፡

“የፆታ እኩልነት በሀገራችን ገና ብዙ ይቀረዋል፡፡ ለምሳሌ በቤት ሳይቀር እናትና አባት ወንድና ሴት ልጆቻቸውን እኩል አያዩም፡፡ ለምሳሌ ሴቶች ከት/ቤት ሲመለሱ በቤት ውስጥ የሥራ ጫና ይጠመዳሉ፡፡ በዚህም የጥናት ጊዜ የላቸውም፡፡ ብዙ ጊዜም የትምህርት ውጤታቸው ዝቅተኛ ከመሆን ባለፈ ትምህርት ወደማቋረጥ ይደርሳሉ፡፡

“ፆታዊ ጥቃት በተለይ በከተማ ላይ በት/ቤትም ሆነ ከት/ቤት ውጭ የአስገድዶ መድፈር ከዓመት ወደ ዓመት እየጨመረ መጥቷል፡፡ ሌላው አንዲት ሴት ፆታዊ ጥቃት ደርሶባት ህግ ፊት ስትመጣ እንባ ይቀድማታል፡፡ በህግ ደግሞ ተገቢው ድጋፍ አይደረግላትም፡፡ ድርጊቱም ከታወቀ በህብረተሰቡ ዘንድ መገለል ይደርስባታል፡፡

“በዞናችን ፆታዊ ጥቃትን ለመቀነስ ወይም ለመከላከል በየጊዜው ጥናት በማካሄድ መፍትሄው ጭምር መጠቆም አለበት፡፡ በዚህም ህብረተሰቡ ውስጥ የአመለካከት ለውጥ እንዲመጣ በስፋት መስራት ያስፈልጋል፡፡”

የመጨረሻ አስተያየታቸውን እንዲሰጡን በዩኒቨርሲቲው የገጠር ልማትና ግብርና ኤክስቴሽን ትምህርት ኃላፊ የሆኑትን ወ/ሮ ሸዋ ድንበር መኮንን ጋር አጠር ያለ ቆይታ አድርገን ነበር፡፡ እሳቸውም በፓናል ውይይቱ በቀረበው ርዕስ ዙሪያ የሚከተለውን ብለውናል፡፡

“ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃትን የመከላከል ፕሮግራም ሁሉም ወገን ኃላፊነት ወስዶ መስራት ሲገባው ለተወሰነ ሴክተር መ/ቤት ብቻ ስለሚሰጥ የሚፈለገው ውጤት አልመጣም፡፡ ፆታዊ ጥቃት በት/ቤት ብቻ ሳይሆን ከት/ቤት ውጭም ይደርሳል፡፡ በዚህም የአንድ ተማሪ ውሎ የት ነው? ከት/ቤት የሚባረሩ ተማሪዎች የት ናቸው? የሚለውን መከታተል ያስፈልጋል፡፡ በአጠቃላይም ችግሩ የጋራ ስለሆነ ዩኒቨርሲቲው በዞኑና በከተማው ከሚገኙ ሴክተር መ/ቤቶችና ከሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ጋር ትኩረት ሰጥቶ በጋራ መንቀሳቀስ ይገባዋል፡፡



## የጀርመን ድምጽ (ዶቼቬሌ)

ትናንት አመሻሹ ላይ የብርጋዴር ጀነራል አሳምነዉ ፅጌ አስክሬን ላሊበላ ከተማ አቅራብያ «ሺምሻ» አዉሮፕላን ማረፍያ ሲደርስ የአካባቢዉ ኅብረተሰብ በነቂስ ወጥቶ በሽለላና በፉከራ ተቀብሎ አስክሬኑን አጅቦ ላሊበላ ከተማ መነሃርያ ድረስ ማጀቡን የዶቼ ቬሌ «DW» ምንጮች ገለፁ:: ምሽቱን ላሊበላ አቅራብያ የሚገኙ የገጠር ቀበሌ ነዋሪዎችን ጨምሮ የላሊበላ ከተማ ነዋሪ በነቂስ አደባባይ ወጥቶ የሻማ መብራት መረሃ-ግብር አካሂደዋል:: አብዛኛው ሕዝብ የፀሎት መረሃ-ግብሩን በመከታተል እንዲሁም ወጣቱ በአደባባይ ተሰብስቦ ቆሞ ማደሩን የ«DW» ምንጮች ገልፀዋል:: የላሊበላ ደብር መነኩሴና የሰሜን ወሎ አገረ ስብከት ሊቀ-ጳጳስ አቡነ ኤርሚያስ ለአካባቢዉ ነዋሪ በተለይም ወጣቱ እንዲረጋጋ ለተደጋጋሚ ጊዜ ንግግር አድርገዋል:: ከተማዋም ከሞላ ጎደል በተረጋጋ መንፈስ እንደምትገኝም ታዉቋል:: እስካሁን የአካባቢዉ የመንግሥት ተጠሪዎች ንግግር ባያደርጉም ከለቀስተኛዉ ጋር ከኅብረተሰቡ ጋር በጋራ መሆናቸዉ ታዉቋል:: አደባባይ የወጣዉ የሟቾችን ሁሉ ፎቶ በባነር አስርቶ ፤ የብርጋዴር ጀነራል አሳምነዉ ፅጌ ሞት የኔም ነዉ፤ የዶክተር አምባቸዉ ሞት የኔም ነዉ፤ የጄኔራል ሳዕረ ሞት የኔም ነዉ ፤ አቶ ምግባሩ ሞት የኔ ነዉ ፤ በባህርዳር የተገደሉትን ሁሉ ስም እያነሳ በማስተጋባት ላይ መሆኑም ታዉቋል:: በየአደባባዩ እንደ ሃገሬዉ ባህል ለቀስተኛዉ የሟቾችን ስም እየጠቀሰ በፉከራና ሽለላ ብሎም በቅኔ ዘረፋ ሃዘኑን እየገለፀ መሆኑ ታዉቋል:: መገደላቸዉ ይፋ የሆነዉ ባለትዳርና የአራት ልጆች አባት የብርጋዴር ጀነራል አሳምነዉ ፅጌ ቀብር ሥነ-ስርዓት ከቀኑ ሰባት ሰአት፤ በላሊበላ ቤተ-ክርስትያን በቤተ-ማርያምና በቤተ- ሚካኤል ግቢ ዉስጥ ይፈፀማል ተብሎ መረሃ-ግብር ቢያዝም በዝግጅት መራዘም ምክንያት ቀብሩ ትንሽ ሊዘገይ እንደሚችል ተነግሮአል::

## አለምፀሐይ ወዳጆ

እያንዳንዱ ግለሰብ ለልጆቹ አባት ለወገኖቹ መመኪያ ለቤተሰቦቹ ጥላ ነው:: በማንም ሕይወት መቀጠፍ ልናዝን እንጂ የግል ፍርድ ለመስጠት አንችልም:: አገራችን አሁን ያለችበትን ችግርና መከራ በበቂ ያልተረዳን ከነገ ማዘንና መፀፀት ለመዳን እንቆጠብ:: ኢትዮጵያን የሚበጃትን መንገድ ለመምረጥ በስሜት መንጎድ ሳይሆን ረጋ ብሎ መመካከርና መደማመጥን ይጠይቃል:: መፍጠር የማንችላቸውን የጀግና ነፍሶች በአንድ ቀን እንደዘበት አጥተን ገና ሌሎች እንዲጠፉ እሳት እንጭራለን:: ኧረ ወገኖቼ በቃችሁ ይበለን! ለምን? ለማን እንዲበጅ? ምንድነው የምንፈልገው? ተደማምጠን ተቻችለን ተፈቃቅረን በአንድነትና በእኩልነት የምንኖርባትን ሃገር መፍጠር የለብንም?? ይህስ ውጤት በስሜታዊነት የሚገኝ ነው? ኢትዮጵያ አንዳንዶቻችን ከምናውቃት በላይ ታላቅ ሀገር ናት:: ከተፈጠርንባት ባላነሰ የሚያከብሯት ብዙ ናቸው:: ድንቅ ታሪኳና ክቡር ባሕሏ ልዩ ሥፍራ አሰጥቷታል:: ከምንም በላይ ደግሞ አምላኳ ከክፉ ነገር ሁሉ ሲከልላት ኖሮአል:: የልጆቿ የጀግንነትና የአብሮ መኖር ባሕል አንዱና ትልቁ እሴቷ ነው:: እባካችሁ በቀና መንፈስ በመከባበር የሚበጀንን እንመካከር!
እግዚአብሔር ኢትዮጵያንና ሕዝቧን ይጠብቅ!

## ግርማ ሰይፉ

“መፈንቅለ መንግስት” የሚለው ቃል አጠቃቀም ብዙ ስሜት አይሰጥም:: ቢሳካላቸው እና የሰው ህይወት አጥፍተው ሳይሆን አስረው በግድ ቢያነሷቸው:: ምን ሊያደርጉ ነበር? አዲስ አመራር መርጠናል ብለው ኢህአዴግ ስብሰባ ሊመጡ ነው? የአማራ ክልል እንደ ቦሪስ አሊሲን ሩሲያ ሊመሰርቱ? ከትግራይ ጋር ተከበናል ብለው ሊገጥሙ? ወይስ ምን ሊያደርጉ ነው? ሊያደርጉ የሚችሉት ነገር የገባው ካለ ቢያስረዳኝ? እኔ አንድ ነገር ገብቶኛል በክልል ደረጃ የሚደራጅ ሀይል መጨረሻው ይህ እንደሚሆን:: ሁሉም የፀጥታና የደህንነት መዋቅር አህዳዊ አደረጃጀት ይኑረው ለማለት ከበቂ በላይ ምክንያት ይኖራል::

## ተወልደ በየነ (ተቦርነ)

መስከረም 28 1982 ዓ ም ወያኔ የትውልድ ከተማችን ጋይንት አውራጃን ሲቆጣጠር ብ/ጀኔራል መላኩ ሽፈራው እና ዶ/ር አምባቸውን ጨምሮ በርካታ አብሮአደጎቻችን የያኔውን ኢህዴን የአሁኑን አዴፓ ተቀላቀሉ:: እኔና በህይወት የሌሉት ሁለት ጓደኞቼ ደግሞ ወያኔን ተቃውመን ከፈፀምነዉ ጥቃት ጋር በተያያዘ ለእስር ተዳረግን:: ከ29 ዓመት የአላማ ልዩነት በኃላ በኢትዮጵያ ለታየው አንፃራዊ የለውጥ ሂደት ከፍተኛውን ዋጋ ከከፈሉት አንዱ በነበረው ተስፋዬ ጌታቸው እና ጀኔራል መላኩ አማካኝነት ለመጀመሪያ ጊዜ ተገናኝተን በሰፊው ተጨዋወትን:: ይህ ግንኙነት ተጠናክሮ ዶ/ር አምባቸዉ ወደ ሰሜን አሜሪካ ባቀናበት ወቅት ላጭር ጊዜ ተገናኝተን ብዙ ተወያይተን ነበር:: ነበር ቅርብ ሆነና ሁሉም በነበር ቀረ :: ፈጣሪ ለመላ ቤተሰቡ መፅናናትን ይስጥ! ነፍስ ይማር!

